
# የሰባኪው ምሳሌ

## አንደኛ መጽሐፍ



1. ዶ/ሩ በተወለዱ በአራት ዓመታቸው ሞቱ።
2. የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዋሳ ይሁን።
3. አቶ ቃለ ሕይወት ጥሩ ሰው ነው።
4. ለሕይወትህ ዋጋ ስጥ
5. ሰውም አይደለሁም።
6. አባ ጎሬና አቡዬ።
7. እኔ መንፈስ ነኝ።

# ማውጫ


ክፍል አንድ ....................1

1. *ስለ እውነተኛ ፍቅር* ....................*1*

➡ የቤት ቀጋ ....................1

➡ ጃኬቴን ልደርብልሽ! ....................2

➡ አንቺን አላገባም ....................3

➡ ሚስት አጣሁ! ....................4

➡ በድሉ ያድጋል ....................5

➡ ወደ ጎንህ ተመልከት ....................6

➡ ጅቡ መጣብህ! ....................7

➡ አንድ ለአንድ ....................8

➡ የእኔ አንድ ዓይኔ ይጥፉ! ....................9

ክፍል ሁለት ....................10

*2. ስለ እግዚአብሔር ቃል* ....................*10*

➡ ያንጫርልሃ! ....................10

➡ የደራሲው ወዳጅ ....................11

➡ እሳቱ ሰባኪ ....................12

➡ ለሰይጣን ጊዜ የለኝም ....................14

➡ እኛ ቤት መሣሪያ አለ ....................15

➡ ከርሞ ጥጃ ....................16

➡ ማን ሊበላው ነው! ....................17

➡ ሰገባውና ማህደሩ ....................18

➡ ጅኒ ለማንጫጫት ....................19

➡ እኔ መንፈስ ነኝ ....................20

➡ እናቴንስ አላገባም! ....................21

➡ ይነሣሉና እንዳይቀበሩ ....................22

➡ የዱላ ቅብብሎሽ ....................23

➡ ግራ የተጋባው ሰባኪ ........ 24
ክፍል ሦስት ........ 25
3. *ስለ ጸሎት* ........ *25*
➡ ለእናቴም ደህና አማች ስጣት ........ 25
➡ የድሃው ሰው ጸሎት ........ 26
➡ ወይ ውረድ ወይ ፍረድ! ........ 27
➡ የትንሹ ልጅ ጸሎት ........ 28
➡ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዋሳ ይሁን! ........ 29
➡ የራብ አድማ ........ 30
➡ ጌታ ሆይ ቤታችን እንዳይጠፋህ! ........ 31
ክፍል አራት ........ 32
4. *እግዚአብሔርን ስለ ማስቀደም* ........ *32*
➡ የተዘቀዘቀው ስፒል ........ 32
➡ ማዳበሪያውና ጨው ........ 33
➡ ጭስ ማውጫ ........ 34
➡ በአፍንጫዬ ይውጣ ........ 35
➡ እሰይ ፈጀኝ ........ 36
➡ የምተኛው የት ነው? ........ 37
➡ አለች አትበላት ........ 38
➡ የቀለበት መንገድ ........ 39
➡ እርሳቸውን ትመስላለች ........ 40
➡ ስልሳ ሚሊዮን ........ 41
➡ ዓለምን አልክድም! ........ 42
➡ የፋሲካው በሬ ........ 43
➡ ወ/ሪት ብርጭቆ ........ 44
➡ አባዬ በላኸው! ........ 45
➡ ዓለም ሁሉ ገምቷል ለካ ........ 46

➡ የአይጥ መርዝ......47
➡ እግዚአብሔር የቱን ያክላል? ......48
ክፍል አምስት ......49
5. *እግዚአብሔርን ስለሚያስከብር ሥራ* ......*49*
➡ ምን አለበት ባትጮኹብኝ? ......49
➡ የዕለት ጉርሷን አጣች......50
➡ አጥር ገፊው ......51
➡ ዶክተሩ በተወለዱ በአራት ዓመታቸው ሞቱ......52
➡ ይፍቱ ሥራ......53
➡ ዝጊው ስልሹ፥ ዝጋው ስልህ ......54
➡ የእኛ ኑሮ ተሳትፎ ነው! ......55
➡ አቶ ቃለ ሕይወት ጥሩ ሰው ነው! ......56
➡ ከፉ ለራሱ፥ ደግ ለራሱ......57
➡ የታረደው በግ......58
ክፍል ስድስት ......59
6. *ስለ እግዚአብሔር ተስፋ* ......*59*
➡ አቤት! የገና አባት ጺም......59
➡ ካሮቱና አህያው ......60
➡ እግዚአብሔር ሆይ፥ ታዘብኩህ......61
➡ መነጽር የተሸከመው ጉንዳን ......62
ክፍል ሰባት ......63
7. *በእግዚአብሔር ስለ መታመን* ......*63*
➡ ቋጥኙን ልቀቅ! ......63
➡ ነፍሴን ለባለቤቱ ላስረክብ! ......64
➡ የሰይጣን ቀንበር ......65
➡ በኢየሱስ ስም አቃጥለኝ! ......66
➡ ጥቁሯ ደሮ ......67

➡ ከመቶ በላይ ቁጥር አለው ወይ? ........................ 68
➡ ለሕይወትህ ዋጋ ስጥ ........................ 69
ክፍል ስምንት ........................ 70
8. *ለእግዚአብሔር ስለ መስጠት* ........................ *70*
➡ የእግዚአብሔር ጥጃ ሞተችበት ........................ 70
➡ አባ ጎሴና አቡዬ ........................ 71
➡ የመባው ዕቃ ........................ 71
➡ ዘጠኝ ብር ከስረሃል ........................ 73
ክፍል ዘጠኝ ........................ 74
9. *እግዚአብሔርን ስለ ማገልገል* ........................ *74*
➡ ከራባት ታስራለህ ........................ 74
➡ ምን ነው ምን ነካዎት? ........................ 75
➡ የመንደር መገለጥ ........................ 76
➡ የተዋስኩት ነው! ........................ 77
➡ የጠፋው ፍየል ........................ 78
➡ ዝሆን ትልቅ ነው ........................ 79
➡ ሰውም አይደለሁም ........................ 80
➡ አራርቆ መውለድ ........................ 81
ክፍል አሥር ........................ 82
10. *እርስ በርስ ይቅር ስለ መባባል* ........................ *82*
➡ ካቆምንበት እንጀምራለን ........................ 82
➡ ወረቀት አፍ የለውም! ........................ 83
➡ አህያውን ይዛችሁ ከዚህ ቆዩ! ........................ 84
➡ የኢሠፓ አባል ነዎት? ........................ 85
ምሥጋና ........................ 86
ሥጦታ ........................ 86

# የሰባኪው ምሳሌ

## አንደኛ መጽሐፍ

በወንጌላዊ ደመወዝ አበበ

1994 ዓ.ም ታተመ

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት

ይህን መጽሐፍ ያለ ደራሲው ፈቃድ ማባዛት ወይም
መልሶ ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው።

Copyright ©Demewez Abebe
April 2002
All Rights Reserved

አሳታሚ

የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል

የፖ. ሣ. ቁጥር 127

አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ

**Printed by SIM Press**

# ማውጫ


ክፍል አንድ ....................1

1. *ስለ እውነተኛ ፍቅር*....................*1*

- ➡ የቤት ቀጋ ....................1
- ➡ ጃኬቴን ልደርብልሽ! ....................2
- ➡ አንቺን አላገባም....................3
- ➡ ሚስት አጣሁ! ....................4
- ➡ በድሉ ያድጋል ....................5
- ➡ ወደ ጎንህ ተመልከት ....................6
- ➡ ጅቡ መጣብህ! ....................7
- ➡ አንድ ለአንድ....................8
- ➡ የእኔ አንድ ዓይኔ ይጥፉ! ....................9

ክፍል ሁለት ....................10

*2. ስለ እግዚአብሔር ቃል* ....................*10*

- ➡ ያንጫርልሃ! ....................10
- ➡ የደራሲው ወዳጅ....................11
- ➡ እሳቱ ሰባኪ ....................12
- ➡ ለሰይጣን ጊዜ የለኝም....................14
- ➡ እኛ ቤት መሣሪያ አለ....................15
- ➡ ከርሞ ጥጃ ....................16
- ➡ ማን ሊበላው ነው! ....................17
- ➡ ሰገባውና ማህደሩ....................18
- ➡ ጅኒ ለማንጫጫት....................19
- ➡ እኔ መንፈስ ነኝ....................20
- ➡ እናቴንስ አላገባም! ....................21
- ➡ ይነሣሉና እንዳይቀበሩ....................22
- ➡ የጱላ ቅብብሎሽ....................23

➡ ግራ የተጋባው ሰባኪ ..... 24

**ክፍል ሦስት** ..... 25

3. *ስለ ጸሎት* ..... *25*

➡ ለእናቴም ደህና አማች ስጣት ..... 25

➡ የድሃው ሰው ጸሎት ..... 26

➡ ወይ ውረድ ወይ ፍረድ! ..... 27

➡ የትንሹ ልጅ ጸሎት ..... 28

➡ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዋሳ ይሁን! ..... 29

➡ የራብ አድማ ..... 30

➡ ጌታ ሆይ ቤታችን እንዳይጠፋህ! ..... 31

**ክፍል አራት** ..... 32

4. *እግዚአብሔርን ስለ ማስቀደም* ..... *32*

➡ የተዘቀዘቀው ስፒል ..... 32

➡ ማዳበሪያውና ጨው ..... 33

➡ ጭስ ማውጫ ..... 34

➡ በአፍንጫዬ ይውጣ ..... 35

➡ እሰይ ፈጀኝ ..... 36

➡ የምተኛው የት ነው? ..... 37

➡ አለች አትበላት ..... 38

➡ የቀለበት መንገድ ..... 39

➡ እርሳቸውን ትመስላለች ..... 40

➡ ስልሳ ሚሊዮን ..... 41

➡ ዓለምን አልከድም! ..... 42

➡ የፋሲካው በሬ ..... 43

➡ ወ/ሪት ብርጭቆ ..... 44

➡ አባዬ በላኸው! ..... 45

➡ ዓለም ሁሉ ገምቷል ለካ ..... 46

➡ የአይጥ መርዝ.....47
➡ እግዚአብሔር የቱን ያክላል? .....48
ክፍል አምስት .....49
5. *እግዚአብሔርን ስለሚያስከብር ሥራ* .....*49*
➡ ምን አለበት ባትጮኹብኝ? .....49
➡ የዕለት ጉርሷን አጣች.....50
➡ አጥር ገፊው .....51
➡ ዶክተሩ በተወለዱ በአራት ዓመታቸው ሞቱ.....52
➡ ይፍቱ ሥራ.....53
➡ ዝጊው ስልሽ፥ ዝጋው ስልህ .....54
➡ የእኛ ኑሮ ተሳትፎ ነው! .....55
➡ አቶ ቃለ ሕይወት ጥሩ ሰው ነው! .....56
➡ ከፉ ለራሱ፥ ደግ ለራሱ.....57
➡ የታረደው በግ.....58
ክፍል ስድስት .....59
6. *ስለ እግዚአብሔር ተስፋ* .....*59*
➡ አቤት! የገና አባት ጺም.....59
➡ ካሮቱና አህያው .....60
➡ እግዚአብሔር ሆይ፥ ታዘብኩህ.....61
➡ መነጽር የተሸከመው ጉንዳን .....62
ክፍል ሰባት.....63
7. *በእግዚአብሔር ስለ መታመን* .....*63*
➡ ቋጥኙን ልቀቅ! .....63
➡ ነፍሴን ለባለቤቱ ላስረክብ! .....64
➡ የሰይጣን ቀንበር .....65
➡ በኢየሱስ ስም አቃጥለኝ! .....66
➡ ጥቁሯ ደሮ .....67

➡ ከመቶ በላይ ቁጥር አለው ወይ? ..................... 68
➡ ለሕይወትህ ዋጋ ስጥ ..................... 69
ክፍል ስምንት ..................... 70
8. *ለእግዚአብሔር ስለ መስጠት* ..................... *70*
➡ የእግዚአብሔር ጥጃ ሞተችበት ..................... 70
➡ አባ ጎሴና አቡዬ ..................... 71
➡ የመባው ዕቃ ..................... 71
➡ ዘጠኝ ብር ከስረሃል ..................... 73
ክፍል ዘጠኝ ..................... 74
9. *እግዚአብሔርን ስለ ማገልገል* ..................... *74*
➡ ከራባት ታስራለህ ..................... 74
➡ ምን ነው ምን ነካዎት? ..................... 75
➡ የመንደር መገለጥ ..................... 76
➡ የተዋስኩት ነው! ..................... 77
➡ የጠፋው ፍየል ..................... 78
➡ ዝሆን ትልቅ ነው ..................... 79
➡ ሰውም አይደለሁም ..................... 80
➡ አራርቆ መውለድ ..................... 81
ክፍል አሥር ..................... 82
10. *እርስ በርስ ይቅር ስለ መባባል* ..................... *82*
➡ ካቆምንበት እንጀምራለን ..................... 82
➡ ወረቀት አፍ የለውም! ..................... 83
➡ አህያውን ይዛችሁ ከዚህ ቆዩ! ..................... 84
➡ የኢሠፓ አባል ነዎት? ..................... 85
*ምሥጋና* ..................... 86
*ሥጦታ* ..................... 86

# መግቢያ

ይህን «የሰባኪው ምሳሌ» የሚለውን መጽሐፍ ለመጻፍ ያነሣሣኝ ምክንያት ምን እንደ ሆነ ስገልጽ ደስ ይለኛል። ብዙ ጊዜ ከአእምሮአችን የማይጠፉ ነገሮች ምንድን ናቸው? ብንል በትምህርት ቤትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን በልጅነታችን የተማርናቸው በምሳሌ ተገልጸው የሰማናቸው ነገሮች ናቸው። ዛሬም ቢሆን በምሳሌ የምንሰማቸውና የምንናገራቸው መልእክቶች እንደምንወዳቸውና የሰው ልብም ውስጥ ገብተው እንደሚቀሩ፥ ሕይወትንም እንደሚለውጡ አሌ የማይባል ነው።

ታዲያ እውነቱ ይሄ ሆኖ ሳለ ብዙ ሰባኪዎችና የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ግን በሚሰብኩበት ወይም በሚያስተምሩበት ጊዜ እምብዛም ምሳሌ ሲጠቀሙ አላይም። ይህም በሁለት ምክንያት ሊሆን ይችላል። አንድም ምሳሌ ካለማግኘት ሊሆን ይችላል፥ አልያም ምሳሌ ለመጠቀም ካለመፈለግ ሊሆን ይችላል። ምሳሌ ተጠቅሞ ሕይወት የሚለውጠውን የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆነ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። የሃይማኖታችን ጀማሪና ፈጻሚ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኮ በምድር ላይ ሳለ በሚያስተምርበት ጊዜ ሁሉ ጥቂት ሳይሆን ብዙ ምሳሌዎችን እንደተጠቀመ መጽሐፍ ቅዱስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ቁጥር 34 እና 35 እንደዚህ ሲል ይነግረናል፤ «ኢየሱስም ለሕዝቡ ይህንን ሁሉ በምሳሌ ተናገረ፤ በነቢዩም በምሳሌ አፌን እከፍታለሁ፥ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውንም እናገራለሁ የተባለው ይፈጸም ዘንድ ያለ ምሳሌ አልተናገራቸውም።» ስለዚህ ስብከታችን ሁሉ በምሳሌ ቢታጀበ ውጤቱ ያማረና የጣፈጠ እንጂ የጎመዘዘ አይሆንም።

ሁላችንም እንደምናውቀው ስብከት ሦስት ክፍሎች አሉት– መግቢያ፥ ሐተታና መደምደሚያ። እነዚህን ሦስቱን በትክክል ተረድተንና በአንድ አሳብ አጠቃልለን ለማቅረብ የጥናት ጊዜ መውሰድና መጸለይ ያስፈልገናል። ስብከት መነሻና መድረሻ አለው። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ትኩረት ካለመስጠታችን የተነሣ ይሆናል፤ መነሻና መድረሻ ሳይኖረው ይቀርና የሕዝቡን ጊዜ ወስደንንና ሕዝቡን አሰልችተን መልእክታችን ራሱና እግሩ ሳይታወቅ ይቀራል። በአጭር ደቂቃ ከመልእክታችን ጋር የሚሄዱ ጥቂት ምሳሌዎችን በመጠቀም የሕዝቡን ልብ የሚያሳርፍና እግዚአብሔርን የሚያስከብር የጣፈጠ መልእክት ማስተላለፍ ስንችል፥ ከዘፍጥረት እንጀምርና ወደ ራእይ ሕዝቡን ይዘን ስንገስግስ ድንገት መሀል ላይ ድካምና እንቅልፍ ይተባበሩና አድማጮቻችንን መንገድ ላይ ያስቀሩብናል።

የግድ እኮ ከዘፍጥረት መጀመር የለብንም፤ ወይም ከዘፍጥረት የጀመረ ሰባኪ ዮሐንስ ራእይ ሳይደርስ እንዳያቆም ተብሎ አልተጻፈም። ይህን በተመለከተ አንድ የሰማሁት እውነታ አለ። አንድ ሰባኪ ከዘፍጥረት ጀምሮ እየሰበከ እየሰበከ እየሰበከ ትንቢተ ኢሳይያስ ደረሰና የኢሳይያስን መጽሐፍ ደግሞ እንማራለን፤ ሲል በጣም የደከመና ከዘፍጥረት ጀምሮ እየተሰላቸ የመጣ ሰሚ ተነሣና ጌታዬ እኔ ስለደከመኝ የቀጠሮዬ ሰዓትም ስላለፈ እሄዳለሁ፤ በእኔ ፈንታ ግን እራሱ ኢሳይያስ መጥቶ ይስማ ብሎት ጥሎት ሄደ።

በእርግጥ ሰባኪነት ስጦታ ነው፤ ቢሆንም የተሰጠው ሰው እንዴት ስጦታውን እንደሚገልጥ ሊተጋ ያስፈልገዋል። እንግዲህ ይህ መጽሐፍ ምንናአልባት ይህንና ሌሎችንም ችግሮች በትንሹ ሊያስቀር ይችል ይሆናል በማለት ያነበብኳቸውንና የሰማኋቸውን ምሳሌዎች ከቃሉ ጋር በሚያመች ሁኔታ በማስተካከል ሳቀርብ የእግዚአብሔርን ቃል ለምታስተምሩና ለምትማሩ፥ በአጠቃላይም ለሰው ልጆች ሁሉ የሚጠቅሙና ሕይወትን የሚለውጡ ስለሆኑ ለግል ሕይወታችሁና ለጋራ አገልግሎታችሁ እንደምትጠቀሙባቸው በማመን ነው።

# ክፍል አንድ

## ስለ እውነተኛ ፍቅር

### የቤት ቀጋ

ሰባኪው «ፍቅራችን የአደባባይ ብቻ ሳይሆን የቤትም ይሁን። እውነተኛ ፍቅር ከቤት ጀምሮ ወደ ውጪ ይወጣል የቤት ቀጋ የውጪ አልጋ አንሁን።» የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ለማስጨበጥ የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀመ።

አንድ ሰው በቤት ውስጥ ለቤተሰቡና ለሚስቱ ፍቅር የለውም። ውኃ ቀጠነ ብሎ የሚጣላና የሚጨቃጨቅ፥ በውጭ ግን መልአክ የመሰለ ፍቅርን የሚያሳይ ግብዝ ሰው ነበረ። እና አንድ ቀን የስብከት ተራው ደረሰና ቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ ቆሞ ከ1ኛ ቆሮ. ምዕ. 13 መስበክ ጀመረ፤ እንዲህ እያለ፥ «ፍቅር አይመካም፥ አይበሳጭም፥ አይጣላም፥ የራሱን አይፈልግም፥ በሁሉ ይታገሳል፥ ሁሉን ይወዳል. . .» በዚህ ጊዜ በጉባኤው መሀል ቁጭ ብላ የምትሰማው ባለቤቱ የቤቱን የፍቅር ሕይወት እና የመድረኩን እያነጻጸረች እየተደነቀችም ትሰማው ነበርና ስብከቱ አልቆ ፕሮግራሙ ሲፈጸም፥ ሚስቲቱ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ መጋቢ ሄደችና እንዲህ አለች፦ «ፓስተር ባለቤቴ በቤተ ክርስቲያን እውነተኛ ፍቅርን እንደዚህ ካሳየ ቤት ደግሞ በተቃራኒው ከሆነ ችግሩ ቤቱ ነውና አልጋችንን ቤተ ክርስቲያን ላምጣና እዚሁ እንኑር፤ ቤቱን ልጆቼ ይኑሩበት» አለች።

«ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን። ክፉውን ነገር ተጸየፉት፤ ከበጎ ነገር ጋር ተባበሩ።» (ሮሜ 12፡9)

ወገኖቼ፥ «እግዚአብሔር ፍቅር ነው»፥ እኛ ደግሞ የእርሱ ልጆች ነንና የአባታችንን ባሕርይ እንውረስ እንጂ የግብዝነት ፍቅር አይኑረን። ምን ያህል ዘመን እንደምንኖር ባናውቅም ቀሪውን ሕይወታችንን ጌታ በፍቅር ጎብኝቶ ለእርሱና ለሰዎች ሁሉ የምንመች የቤትም የውጭም አልጋ ያድርገን። አሜን!

# ጃኬቴን ልደርብልሽ!

ሰባኪው «እውነተኛ ፍቅር ጊዜና ሁኔታ አይለውጠውም። ዛሬ ወይም ባንድ ወቅት ነፍስ እስከማይቀርልን ድረስ የወደድናቸውን ሰዎች እጃችን ከገቡ በኋላ ፍቅራችን መቀዝቀዝ (መቀነስ) የለበትም፤ እውነተኛ ፍቅር ጊዜ አይለውጠውምና።» የሚለውን ስብከታቸውን ለማስጨበጥ ይህን ምሳሌ ተናገሩ።

በእጮኝነት ዘመናቸው በጣም የሚዋደዱ ፍቅረኛሞች ነበሩ፤ በተለይ ወንዱ ነፍሱ እስከትወጣ ይወዳታል። አብረው እየሄዱ ከበረዳት ጃኬቴን ልደርብልሽ ይልና ይደርብላታል፤ እንቅፋት ከመታትም እኔን ይድፋኝ ይላል፤ እንዲህ እንዲህ እያለ ተጋብተው አንድ አሥር ዓመት ከቆዩ በኋላ ሁኔታዎች እየተለወጡ መጡ። ያ የዱሮ እንስፍስፍነቱ ቀዘቀዘና ዛሬ ወዳጅ ዘመድ ለመጠየቅ አብረው ሲሄዱ በርዷት በረደኝ ብትለው በጎርናና ድምፁ «ደርበሽ አትወጪም ነበር» ይላታል፤ እንቅፋት ሲመታትም «እያየሽ አትሄጂም» ብሎ ይጮኽባታል። ለምን ቢባል የቀደመውን ፍቅር ትቷልና።

«ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና።» (ራዕይ 2፡4)።

አዎ ወገኖቼ፥ ባንድ ወቅት እንደዚያ ሰው እስኪታዘበን ድረስ ራሳችንን የሰጠንላት ባለቤታችን፥ ዛሬ ልጆች ወልዳ ለልጆቿ እያሰበች ራሷን ባትጠብቅና ውበቷም ቢረግፍ፥ እግዚአብሔር የሰጠን ሚስታችን ነችና በማይለወጥ ፍቅር ልንወዳት ይገባል። «ወዳጅ በዘመኑ ሁሉ ይወዳልና»። ዘመናችንን በእውነተኛ ፍቅር እንድንጨርሰው ፈጣሪ ይርዳን። አሚን!

# አንቺን አላገባም

ሰባኪው ለአቅመ አዳም የደረሱ ወጣቶችን ሁሉ ሰብስበው በቤተ ክርስቲያናቸው እንዲህ እያሉ የጋብቻ ትምህርት ማስተማር ጀመሩ «ወጣቶች ራሳችሁን በንጽሕናና በቅድስና ጠብቃችሁ እግዚአብሔር በሚፈቅደው መንገድ እጮኛ መርጣችሁ እንደ ቃሉ ክቡር የሆነውን ትዳር መመሥረት አለባችሁ። ታዲያ እጮኛ ስትመርጡ በውስጧ ወይም በውስጡ ፈሪሀ እግዚአብሔር መኖሩን አረጋግጡ እንጂ በሚረግፈውና በሚከዳው የውጭ ማንነት /መልክ/ ላይ ብቻ አታተኩሩ። በውስጥ ልብ ለልብ የተዋደደ እስከ ሕይወት ፍጻሜ ይዘልቃል፤ በውጭ በመልክ ብቻ የተዋደደ መልክና ውበት ሲከዳ እርሱም አብሮ ይከዳል፤ ፍቅሩ ውጫዊ ነውና።» እስቲ ይህን ምሳሌ ልንገራችሁ፦

አንድ ወጣት የአንዲትን ልጅ ዓይናን ወደደና ለትዳር ጠየቃት። እርሷም እሺ ብላው አብረው ቀጠሉ። አንድ ቀን ሽርሽር ቦታ ሄደው ዋና እየዋኙ ሳለ ውኃ ውስጥ የተደበቀ ብረት ዓይኗን ይመታውና አንድ ዓይኗ ይፈስሳል። በዚህ ጊዜ አንድ ቀን «የምነግርሽ ነገር አለኝና ቶሎ ብለሽ ነይ» ብሎ ይጠራታል። እርሷም መጥታ የሚነግራት ስለምን እንደሆነ ለማወቅ ጓጉታ ትጠይቀው ጀመር። ስለ ሰርጋችን ነው? ስለ እኔ ቬሎ ነው? ስለምንጋባበት ቀን ነው? የምትነግረኝ ምንድን ነው? እርሱም፥ «አይደለም የምነግርሽ ከዚህ በኋላ አብረን አንቀጥልም፥ አንቺንም አላገባም፤ ምክንያቱም የዚያች የዓይን ስውር ባለቤት መባል አልፈልግም።» አላት።

«ወዳጅ በዘመኑ ሁሉ ይወዳል» (ምሳሌ 17፥17)።

አዎ ወገኖቼ፥ ፍቅራችንን በእውነተኛ ፍቅር እንጂ በሚፈርሰውና በሚጠፋው አካል ብቻ አንመሥርት። የምናገባው ዓይናን፥ ፀጉሯን ወይም አፍንጫዋን አይደለም፤ የእግዚአብሔር አምሳል የሆነውን ክቡር የሰው ልጅን እንጂ። በእውነት እንዋደድ፤ ለዚህም አምላክ ይርዳን። አሜን!

# ሚስት አጣሁ!

ሰባኪው ትዳር ያልመሠረቱ ወጣቶችን ሰብስበው እጮኛ እንዴት መያዝ እንዳለባቸው ሲያስተምሩ «ወጣቶች እጮኛ ስትመርጡ መመዘኛ (ክራይቴሪያ) አታብዙ፤ እግዚአብሔር የሚያስቀምጠው የመጀመሪያው መመዘኛ ክርስቲያን ከክርስቲያን ጋር መጋባት አለበት ነው የሚለው። ደግሞ ልብ በሉ ፍጹም የሆነች ሚስት (ባል) አናገኝም፤ የምናገኘው አንዱ የአንዱን ጉድለት ለመሙላት ነውና ይህንንም አስቡበት፤ አለበለዚያ ፍጹም የሆነ እንከን የሌለው ጓደኛ እየፈለጋችሁ ስትኖሩ አታገኙም፤ ዕድሜአችሁ አልቆ ሳታገቡ ቆማችሁ ትቀራላችሁ እንጂ።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለማስጨበጥ የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንድ ወጣት ሳያገባ ዕድሜው ከወጣትነት ወደ ጎልማሳነት ገፋ። የቤተ ክርስቲያኑ መጋቢ ጠሩውና «ለምንድን ነው የማታገባው? ሥራ አለህ፥ ቤትም አለህ፥ ሁሉ ተሟልቷል፥ ምንድነው ችግርህ» ብለው ቢጠይቁት እንዲህ ብሎ መለሰላቸው። «ከሀ–ፐ ያለውን መመዘኛዬን (ክራይቴሪያ) የምታሟላ ሚስት አጣሁ አላቸው።» እርሳቸውም «እስቲ ለመሆኑ ምንድንነው? ይህን ከA-Z ያለውን መመዘኛህን ንገረኝ ልረዳው አሉት።» እርሱም «(A አክቲቭ፥ B ቢዩቲፉል፥ C ክሪኤቲቭ፥ D ዲሰንት፥ E ኤክሰለንት፥ F ፋንታስቲክ፥ G ጀይንት፥ H ሐምብል፥ I ኢኖሰንት፥ J ጀንትል፥ K ካይንድ . . .» እያለ ሲቀጥል መጋቢው አቋረጡትና «የእኔ ወንድም ይህን ሁሉ የምታሟላ ሚስት አታገኝም፥ ነገር ግን ጉድለትና እንከን የሌለበትን ክርስቶስን የምታመልክ ሴት እንድታገባ እመክርሃለሁ።» አሉት።

አዎ ወገኖቼ ሆይ፥ ባልና ሚስት የሚጋቡት ለመረዳዳት ነው፤ የሚረዳ ነገር የሌላቸው ምንም የማያስፈልጋቸው ከሆኑ መጋባትም አያስፈልጋቸውምና ከእውነቱ እንዳንርቅ ጌታ ይርዳን። አሜን!

# በዕድሉ ያድጋል

ሰባኪው በቤተ ክርስቲያናቸው ያሉትን ባለ ትዳሮች ሰብስበው ስለ ቤተሰብ አኗኗርና ስለ ልጆች እንዲህ ሲሉ አስተማሩ «ቤተሰብ በእግዚአብሔር የተመሠረተ ስለሆነ በደስታና በፍቅር በመተሳሰብ ልንኖር ይገባል። ልጆች ደግሞ የእግዚአብሔር ስጦታ ስለሆኑ ማሳደግ የምንችለውን ያህል ልጆች እንደ አቅማችን ወልደን ማሳደግ አለብን እንጂ በዕድሉ ያድጋል ብለን የመጀመሪያው ገና ሳይጠነክር በላይ በላዩ ላይ መጨመር የለብንም፤ አራርቀንና መጥነን መውለድ አለብን። ለዚህም እንዲረዳን ሳይንሳዊ የሆኑ መንገዶችን ሐኪም እያማከርን ብንጠቀም ኃጢአት አይደለም።» ለሚለው ትምህርታቸው የሚከተለውን ምሳሌ በመጠቀም አስረግጠው ተናገሩ።

«በሥነ መለኮት (በመጽሐፍ ቅዱስ) ትምህርት ቤት መምህሩ ልጆችን መጥና (አራርቆ) ስለመውለድ ሲያስተምሩ ለተማሪዎቻቸው እንዲህ እያሉ ማስተማር ጀመሩ «የእግዚአብሔር ስጦታ የሆኑትን ልጆችን በአግባቡ ባናሳድግ እግዚአብሔር ይጠይቀናል፤ ለዚህም እንዲረዳን መጥነን መውለድ አለብን እንጂ ማንጋጋት የለብንም።» እያሉ ሲያስተምሩ፥ አንድ ያልተዋጠለት ተማሪ ጥያቄ ጠየቀ «በዘፍ. 1፡28 ላይ «ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉዋት» ይላል የእርስዎ ትምህርት ግን ብዛትን ሳይሆን ቅነሳን ነውና የሚያሳየው ከቃሉ ጋራ አይጋጭም ወይ?» ቢላቸው፥ «ታዲያ እግዚአብሔር ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት፥ ቢል አንተ ብቻህን ምድርን ልትሞላ ትፈልጋለህ እንዴ?» ብለው ጥያቄውን በጥያቄ በመመለስ አሳረፉት!

አዎ ወገኖቼ፥ ዛሬ ጎዳናውን የሞሉትን ልጆች እያሰብንና እያዘንን እንጠንቀቅ፤ ነገ የእኛ ልጆች ተራ እንዳይሆን ማሳደግ የምንችለውን ልጆች ብቻ እንድንወልድ ጌታ ይርዳን። አሜን!

## ወደ ጎንህ ተመልከት

ሰባኪው «በዚህ ምድር ላይ ስንኖር ሕይወታችንን የሚመራ ብቸኛና እውነተኛ መሪ እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ በእርሱ ፊት በጸሎት ስንቀርብ እርሱ ፈቃዱን ያስታውቀናል፤ የትኛውን ሥራ መሥራት እንዳለብን፥ የት ሀገር መኖር እንዳለብን በየትኛው መንገድ መሄድ እንዳለብንና ማንን ማግባት እንዳለብን፤ ይህ ምሪት የሚሆነው ግን የእኛንም ድርሻ ስንወጣ ነው። ዳዊት ለጦርነት ሲወጣ ልውጣ ወይ ብሎ ይጸልያል፤ ውጣ ሲለው ይወጣል፥ አትውጣ ሲለው አይወጣም። አንድ ጊዜ የኮሽታ ድምፅ ስትሰማ ውጣ እኔ ከአንተ ጋር ነኝ አለው። መስማት የዳዊት ድርሻ ነበር። ሥራ የሌለው ሰው ወደ እግዚአብሔር ቢጸልይ ሥራ መስጠት የእግዚአብሔር ድርሻ ነው፤ ወጣ እያሉ የሥራ ማስታወቂያዎችን ማንበብ ደግሞ የግለሰቡ ድርሻ ነው፤ ልክ እንደዚሁ እጮኛ ለሌለው እጮኛ (ሚስት) መስጠት የእግዚአብሔር ድርሻ ነው፤ በፍቅር መጠየቅ ደግሞ የሰው ድርሻ ነው።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለማስጨበጥ የሚከተለውን ምሳሌ ተናገሩ።

አንድ ወጣት ሳያገባ ብዙ ጊዜ ቆየና ወንጌላዊው «ሚስት ለምን አታገባም?» ብሎ ጠየቀው፥ እርሱም «እየጸለይኩ ነው» አለው። ከዓመት በኋላም ጠየቀው፤ አሁንም «እየጸለይኩ ነው» አለው። አሁንም ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ «አሁንም እየጸለይክ ነው?» ብሎ ጠየቀው፤ «አዎን እየጸለይኩ ነው» አለው። «መቼ መቼ ነው የምትጸልየው እስቲ ንገረኝ» አለው። «ከሰኞ እስከ ሰኞ ወይም ከእሑድ እስከ እሑድ ነው» አለው። በዚህን ጊዜ ወንጌላዊው «ይሄማ የምትጠይቅበት ጊዜም የለህም ማለት ነው፤ እባክህ ከዚህ በኋላ ከሰኞ-አርብ ጸልይ፤ ቅዳሜና እሑድ ግን ወደ ጎንህ ዘወር ዘወር ብለህ ተመልከት።» አለው።

«እንዲህ ይሆናል፤ የምድርን ሁሉ ጌታ የእግዚአብሔርን ታቦት የተሸከሙ ካህናት እግር ጫማ በዮርዳኖስ ውኃ ውስጥ ሲቆም፥ ከላይ የሚወርደው የዮርዳኖስ ውኃ ይቋረጣል፤ እንደ ክምርም ሆኖ ይቆማል።» (ኢያሱ 3፡13)።

አዎ እግዚአብሔር የራሱን ድርሻ ይወጣል፤ እኛም በእምነትና በንቃት የራሳችንን ድርሻ እንድንወጣ ጌታ ይርዳን። አሜን!

# ጅቡ መጣብህ!

ሰባኪው ባለትዳሮችን ሁሉ ሰብስበው ልጆችን በእግዚአብሔር ቃል እውነት ስለማሳደግ ሲያስተምሩ «የነገውን ሀገርና ቤተ ክርስቲያን የሚረከቡት የዛሬ ልጆች እንደሆኑ በሁላችን ዘንድ ግልጽ ነው። ስለዚህም ልጆቻንን በእግዚአብሔር ቃል ኮትኩተን በየቤቶቻችን ልናሳድጋቸው ይገባል እንጂ በትንሽ በትልቁ እየደበደብን መራራ ልንሆንባቸው አይገባም። የልጆች አእምሮ ምንም ያልተጻፈበት ነጭ ወረቀትን ይመስላል፤ የሰጡትን ሁሉ ይቀበላል፤ ከዚያም አይለቅምና ገና ከመሠረቱ እውነቱን እውነት፥ ውሸቱንም ውሸት ነው እያልን በትክክለኛው መስመር ልናሳድጋቸው ይገባል እንጂ ባረጀ ባፈጀና በማይጠቅም «የጅቡ መጣብህ!» ባህል ውስጥ ልንዘፍቃቸው አይገባም። እውነትን ስተው በሐሰት ቢያድጉ ነገ የታሪክ ተጠያቂዎቹ እኛው ነን።» ለሚለው ትምህርታቸው ይህን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንድ እናት ልጁ እየዋሸ ስላስቸገራትና ወደፊትም በውሸቱ ይቀጥላል ብላ ስለ ፈራች እንዲህ ብላ አስጠነቀቀችው፤ «አንተ ልጅ ሁለተኛ የምትዋሽ ከሆነ ሆድህ ይቆነዘራል!» ልጁም መዋሸት ሆድን ያሳብጣል የሚለውን የውሸት ትምህርት ተቀብሎ ሲኖር ሳለ አንድ ቀን ወደ ቤታቸው ሆዱ ያበጠ እርጉዝ ሴት መጥታ ሲያይ ገረመውና ወደ እርሷ ጠጋ ብሎ፥ «አውቄብሻለሁ ሆድሽ እንደዚህ የተቆነዘረው ሁልጊዜ ስለምትዋሺ ነው።» ብሏት አረፈው።

ወገኖቼ ለልጆቻችን እውነትን እናስተምር፤ ዛሬውኑ ፊት ለፊት ነጩን ነጭ፥ ጥቁሩንም ጥቁር እንበላቸው እንጂ ነገ ሲገለጥ የሚያሳፍረንን እውነትና ተጨባጭነት የሌለውን እንቶ ፈንቶ ወሬ አናስተምራቸው። በፍቅርና በጥበብ የእግዚአብሔርን እውነተኛ ቃል እያስተማርን እንድናሳድጋቸው ጌታ ይርዳን። አሜን!

«ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።» (ምሳሌ 22፥6)።

# አንድ ለአንድ!

ሰባኪው ትዳር ያልያዙ ወጣቶችን ሰብስበው ስለ መጋባት የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን ምንም ሳያስቀሩ ግልጽ በሆነ ሁኔታ አስተማሩ። «ጋብቻ ክቡር ነው፤ ክቡር የሆነበትም ምክንያት የተጀመረው በእግዚአብሔር በመሆኑ ነው። እግዚአብሔር በመጀመሪያ አዳምና ሔዋንን በማጋባት ጋብቻን አስጀመረ። ሌላው ክቡር የሆነበት ምክንያት አንድ አዳም ለአንድ ሔዋን መሆኑ ነው። ከዚህ ውጪ ጋብቻ ክቡር ሳይሆን ርኩስ ነው የሚሆነው። ይህንን አንድ ለአንድ መወሰንን ትተንና ጥለን ብንሄድ ትርፉ ሞት ነው። ዛሬ በምድራችን ላይ ኤች. አይ. ቪ. ኤድስ እንኳ ከሚዛመትበት ዋናውና የመጀመሪያው መንገድ ሰዎች ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ በሆነ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ውስጥ (በዝሙት) ወድቀው ሲገኙ ነው። ከዚህ ደግሞ ሳንርቅ ኤድስ አይዘኝም ማለት አንችልም። ስለዚህ ወጣቶች ከዚህ ከሚርመሰመሰው የሰው ልጅ ውስጥ እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ ለአንተ (ለአንቺ) ሚስትን (ባልን) ይሰጣችኋልና በጸሎትና በፍርሃት ሕጉን ጠብቁ እንጂ ለወንድሜ ወይም ለእኅቴ ይጠቅማል በሚል በከንቱ ውዳሴ ከቃሉ ውጪ ሆናችሁ እንዳትገኙ ራሳችሁን ጠብቁ» ሲሉ ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ።»

አንዲት እኅት ለአንድ ወንድም፥ «እግዚአብሔር አንተን በትዳር አሳርፎሃል፥ ጥሩ ትዳርም ሰጥቶሃል፤ እኔን በዚህ ጉዳይ እንዲያሳርፈኝ ጸልይልኝ» አለችው። እርሱም «አይዞሽ ጌታ ይሰጥሻል» ብሎ አብረው መጸለይ ጀመሩ፤ ከ6 ዓመት በላይ ጸለዩ። እድሜዋም እየገፋ ሄደ። እርሱም በጌታ የሚወዳት ጥሩ እኅቱ ናትና ባለማግባትዋ ግራ ገባው። በመጨረሻም ላይ «ዘንድሮስ ማለፍ የለባትም» አለና እንዲህ ሲል አጥብቆ ጸለየ። «እግዚአብሔር ሆይ፥ ለዚች እኅቴ ባል ስጣት፤ አለበለዚያ ግን እኔ አገባታለሁ!» ብሎ እግዚአብሔርን አስፈራራ።

ቅዱሳኖች፥ ትዳርን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነውና እርሱን እንጠብቅ። የሰጠንንም ትዳር በቅድስናና በፍርሃት መያዝ ይገባናል፤ ክቡር ነውና። ዝሙት ኃጢአት ነውና ከዚህ እንድንሸሽ ጌታ ይርዳን። አሜን!

«ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት ግን ሽሽ፥. . . » (2ኛ ጢሞ. 2፥22)።

# የእኔ አንድ ዓይኔ ይጥፋ!

ሰባኪው ፈሪሀ እግዚአብሔር አለን ወይም በእውነት ክርስቲያኖች ነን ለሚሉት ሰዎች ሁሉ ጠላቶቻቸውን እንደ እግዚአብሔር ቃል እንዲወዱ ሲያስተምሩ ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንድ ቀን እግዚአብሔር አንዱን ሰው እንዲህ ብሎ ተናገረው። «ለአንተ ያደረግሁትን ነገር ሁሉ ለጠላትህ ደግሞ እጥፍ አድርጌ አደርግለታለሁና ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ አለው?» እርሱም እንዲህ ሲል አሰበ፥ «አንድ መኪና ለእኔ ብለው የጠላቴ ሁለት መኪና መሆኑ ነው። አንድ ቤት ለእኔ ብለው የጠላቴ ሁለት ቤት መሆኑ ነው» እያለ ማሰላሰሉን ቀጠለና በመጨረሻ እንዲህ አለ፥ «የጠላቴ ሁለት ዓይኑ እንዲጠፋ የእኔ አንድ ዓይኔ ይጥፋ!»

«ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፤ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረጉሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ።» (ማቴ. 5፡43–44)። «ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉ አትመልሱ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ።»

አዎ፥ መቼም ሆነ የትም ቦታ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን እንድናስብና እንድናደርግ እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን!

# ክፍል ሁለት

## ስለ እግዚአብሔር ቃል

## ያንጫርልሃ!

ሰባኪው የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎችንና ሰባኪዎችን ሲያስተምሩ «እኛ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ብቻ ለማለት ያለን ሰዎች ነን። ስለዚህ ለመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ታማኝ እንሁን፤ የምናውቀውን ብቻ እናስተምር፤ የማናውቀው ከሆነ አላውቅም ጠይቄ (አንብቤ) እመጣለሁ እንበል እንጂ ሁሉን አዋቂዎች አድርገን ራሳችንን አናቅርብ። ሁሉን የሚያውቅ ጌታ ብቻ ነው።» የሚለውን መልእክታቸውን ለማስጨበጥ የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ። አንድ አባት ወጣቶችን ሰብስበው ስለ ሲኦልና መንግሥተ ሰማይ ሲያስተምሩ «መንግሥተ ሰማይ ንጹሕ ቦታ ነው። ሁልጊዜ ብርሃን ነው፤ ሌሊት የለውም። ወደዚያ በክርስቶስ ለመግባት ትጉ። ሲኦል ግን ቆሻሻ ነው፤ የሚያቃጥል እሳት አለበት እያሉ ሲያስተምሩ፤» አንዱ ወጣት እንዲህ ሲል ጥያቄ ጠየቃቸው፥ መንግሥተ ሰማይ መምሸትና መንጋቱን በምን እናውቃለን?» እሳቸውም፥ «አውራ ዶሮ ይጮሃል» ብለው መለሱ። ወጣቱም በመቀጠል «መንግሥተ ሰማይ ንጹሕ ነው፥ ቆሻሻ የለበትም ብለዋል፥ አውራ ዶሮ ካለ ኩሱን ወዴት ይጥላል?» «ወደ ገሃነመ እሳት (ወደ ሲኦል) ዞሮ ይጥላል፥ ብለው መለሱ። ወጣቱም በመቀጠል «ገሃነመ እሳት የሚያንጫርር እሳት አለው ብለውናል፥ ታዲያ አያንጫርረውም?» ሲላቸው፥ «ያንጫርልሃ!» ብለው መለሱ።

«. . . ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ!» (1ኛ ቆሮ. 13፥12)

የእግዚአብሔር ሰዎች ሆይ፥ የማናውቀውን አላውቅም ማለት አለማወቅ አይደለምና እንዲህ እንድንል እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን።

# የደራሲው ወዳጅ

ሰባኪው «አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ ትኩረት የሚሰጡት ከቃሉ ውጪ በሆኑ መጻሕፍት ላይ ነው። በአብዛኛው ቤት መጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት መደርደሪያ ላይ አቧራ ጠግቦ ወይም በክብር በሳጥን ተቆልፎ ይገኛል። ይህ የሚሆነው ከመጽሐፉ ደራሲ ጋር የቀረበ ግንኙነት ስለሌለን ወይም የልባችን ወዳጅ ስላላደረግነው ነው። ይህ መሆን የለበትም።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለተማሪዎቻቸው ለማስጨበጥ በዚህ ምሳሌ አስረዱ።

ሁለት ወጣቶች ተዋደዱና ተፈቃቅደው አብረው የሕይወትን ጎዳና ለመጓዝ ወሰኑና አንድ ቀን አብረው ሻይ እየጠጡ ሲጫወቱ ጓደኛዋ እርሱ በሕዝብ ዘንድ የታወቀባቸውን ሥራዎቹን እያነሣ ይነግራት ጀመር። በተለይም ከገዛችው ሦስት ወር ያለፈውና ለማንበብ ጀምራ ሰልችቷት በአልጋዋ ፍራሽ ሥር ያስቀመጠችው መጽሐፍ ደራሲ እርሱ እንደሆነ ሲነግራት በጣም ተገረመች ደስም አላት፤ ከዚያም ማታ ሲለያዩ ወደ ቤቷ ተመልሳ ያንን ለሦስት ወር ዘግታ ያስቀመጠችውን መጽሐፍ በአንድ ሌሊት ጨረሰችው፤ እንዴት ቢባል ደራሲውን ወዳዋለቻ! መጽሐፉን ስታነብ ደራሲው በዓይነ ሕሊናዋ ይመጣላ!

«. . . የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል. . .» (ዮሐ. 14፡23)

አዎን ወገኖቼ፥ እግዚአብሔርን ስንከተለውና ስንወደው የዛን ጊዜ ቃሉን እንድናነብ የሚረዳን መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ይኖራል። እርሱም የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲ ነው። ቃሉን በማንበብ፥ በመኖርና በመታዘዝ ለጌታና ለመንግሥቱ መኖር እንድንችል በቸርነቱ ይርዳን። አሜን!

## እሳቱ ሰባኪ

ሰባኪው «የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ስትመጡ በቃሉ ምን ይለኝ ይሆን በሚል በቃሉ ላይ ብቻ ትኩረት አድርጉ እንጂ ቃሉን በሚያቀርቡት ሰዎች ላይ ትኩረት አታድርጉ። እከሌ ከሰበከ እሄዳለሁ፥ እከሌ ከሰበከ ግን አልሄድም፥ ማለት ጤናማ ሕይወት አይደለም።» ሲሉ የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

በአንድ መሥሪያ ቤት ውስጥ አንድ ጎስቋላ ሰው ነበር። እርሱም ከሰው በላይ ደመወዝ እያገኘ ከሰው በታች የሚኖር ሲሆን፥ ለዚህ ሰው ወገኖች ወንጌልን በተለያየ ጊዜና ሁኔታ ቢነግሩትም ለመቀበል (ለማመን) እምቢ አለ፤ ነገር ግን አንዲት እኅት አቀራረቧን ለውጣ ቀረበችውና እንዲህ አለችው። «የእኛ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሲሰብክ እሳት የላሰ ነው።» «ምን ማለትሽ ነው?» አላት። «በቃ የሚናገረው ቃል ልብ እንጂ መሬት አይወድቅም፤ የሚቆረቁር ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለህ ድንጋዩ መቆርቆሩ አይሰማህም።» አለችው። እርሱም በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ያያቸውንና የሰማቸውን የሚያውቃቸውን ቀልደኛ ሰዎች እየዘረዘረ «የአንቺ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ከእነዚህ ሁሉ ይበልጣሉ?» አላት። «አዎን» አለችው። እርሱም «እኚህን ሰው ለማየት እሄዳለሁ፥ ግን አማኝ አልሆንም» አለና በቀጣዩ እሁድ ተነሥተው አብረው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዱ። ከሕዝቡ መሀል ቁጭ አሉ። እርሱ እሳት የላሱት ሰባኪ የትኛው ይሆኑ እያለ መፈለግ ጀመረ፤ እርሷ ደግሞ የቤተ ክርስቲያኗን አንደበተ ርቱዕ መጋቢ የአገልጋዮች ወንበር ላይ ስትፈልግ አላየቻቸውም። «ምናልባት ቢሮ ይሆናሉ፥ ገና አልመጡም» አለች። እንዲህ እያለ መዝሙሮች ከተዘመሩ በኋላ ፕሮግራም መሪው «አሁን የእግዚአብሔርን ቃል የምንሰማበት ጊዜ ይሆናል» ብሎ ሲጨርስ አንዱ ዲያቆን ከፊት ወንበር ላይ ብድግ አለና መድረኩ ላይ ቆሞ ዘፍጥረት ምዕራፍ አምስትን ከፍቶ የአዳምን የትውልድ ሐረግ መስበክ ጀመረ። አዳም በዚህ ምድር ላይ ልጆችን ከወለደ በኋላ 930 ዓመት ኖሮ ሞተ። ሴትም እንደዚሁ 912 ዓመት ኖረና ሞተ። የሴትም ልጅ ሄኖስ 905 ዓመት ኖረ፤ የሄኖስም ልጅ ቃይንና ልጆችን ወልዶ 910 ዓመት ኖሮ ሞተ። በዚህ ጊዜ ከሰውየው ጎን የተቀመጠችው ልጅ ተበሳጨች «የዛሬው ሰባኪ ምን ዓይነት ሰው ነው፤ እኔ ከሞት የሚድን ሰው ጋብዤ አምጥቼ እርሱ ስለ ሞት ይሰብካል። ምን አለ ጌታ አልዓዛርን በአራተኛው ቀን ዓይኑ ሳይፈስ ሆዱ ሳይዘረገፍ ከሞት አስነሣው፤ 12 ዓመት ደም ሲፈሳት የነበረች ሴት ቀሚሱን ብቻ ነክታ ተፈወሰች፤ እያለ ቢሰብክ» እያለች ለዲያቆኑ ሰባኪ መልእክት መረጠችለት። እርሱ ግን ስብከቱን ቀጠለ። «ወገኖች ቃይናን መስላኤልና ያሬድ የሚባሉት

ሰዎች ሁሉ ከ910 –962 ዓመት ኖረው ሞቱ፤ የያሬድ ልጅ ሄኖክ ግን አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስለ አደረገ ጌታ ወሰደው፤ የመጨረሻውን ረጅም ዕድሜ የኖረው ማቱሳላ ነው። ማቱሳላም 969 ዓመት ኖረና ሞተ። የሰማነውን ቃል እግዚአብሔር ይባርክ» ብሎ ቁጭ አለ። የተጋበዘው ሰው ግን አሳቡን ሰብስቦ ትኩር ብሎ ይሰማ ነበር። እርሷ ግን እሳት የላሱት የቤተ ክርስቲያኗ መጋቢ ስላልሰበኩ ከዚህ ዲያቆን ስብከት ምንም አይገኝም ብላ በማፈር ዝም አለች። ፕሮግራሙ አልቆ ጉባኤው ተበተነ። ሰኞ ቀን መሥሪያ ቤት ስትገባ ጠዋት ያንን ትናንት እሑድ ቤተ ክርስቲያን ጋብዛው የነበረውን ሰውዬ አገኘችውና ስትፈራ ስትቸር «ትናንት እንዴት ነበር?» ብላ ጠየቀችው። እርሱም «ጥሩ ነበር» አለ። «እንዴት? ምን አገኘህ?» አለች። እርሱም «አዳም 930 ዓመት ከኖረ፥ ያሬድ 962 ዓመት ከኖረ፥ ያ ደግሞ ማን አላችሁት ማቱሳላ እርሱ ደግሞ 969 ዓመት ከኖረ፥ እኔም ይህን እድሜ የሚያረዝመውን አምላክ አምናለሁ» አለ።

«የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው. . .» (ዕብ. 4፡12)።

አዎ፥ እሳቱ ሰባኪ ባይገኝም «እሳቱ» መንፈስ ቅዱስ ተገኝቶ ነበርና ሰውዬውን በቃሉ ለወጠው። ስለዚህ ወገኖቼ፥ የእግዚአብሔር ቃል በራሱ ኃይል አለውና ትኩረታችን ቃሉን በሚያቀርቡት ሰዎች ላይ ሳይሆን በራሱ በእግዚአብሔር ቃል ላይ እንዲሆን ጌታ ይርዳን። አሜን!

# ለሰይጣን ጊዜ የለኝም

ሰባኪው «ለሰይጣንና ለአሳቡ አልፈን እንዳንሰጥ ዕለት በዕለት በመጸለይ የጌታን ቃል በማጥናትና በመኖር እንደ ጌታ ኢየሱስ ድል ልንነሳው ይገባል። ለእርሱ ሦስት ፈተናዎችን አቅርቦለት ሦስቱንም በቃሉ በመመለስ ሦስት ለዜሮ አሸንፎ ሸኘው። እኛ ግን ዛሬ ቃሉን ስለማናጠናና ስለማንታመን ከሰይጣን ጋር ሦስት እኩል እየወጣን ተቻችለን እየኖርን ነው። ይህ ግን ፈጽሞ መሆን የለበትም የሚለውን» ትምህርታቸውን ለማስረዳት ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ።

በሥነ መለኮት ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መምህሩ ለተማሪዎቻቸው እንዲህ በሚል ጥያቄ ፈተና ሰጡ በ30 ደቂቃ ውስጥ የእግዚአብሔርንና የሰይጣንን ባሕሪዎች ዘርዝረህ አስረዳ። አንድ ተማሪ ግን እግዚአብሔር ፍቅር ነው፥ እግዚአብሔር መሐሪ ነው፥ እግዚአብሔር አዳኝ ነው። . . . እንደዚህ እንደዚህ እያለ 30ውን ደቂቃ ጨረሰው፤ ሰዓቱ አለቀና ተደወለ። በዚህ ጊዜ የሰይጣን ባዶ ወረቀት አነሣና ከግርጌ እስከ ራስጌ በትልቁ «ለሰይጣን ጊዜ የለኝም» ብሎ በትልቁ ጻፈበት።

«አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ» [መዝ. 118(119)፥11]

አዎ፥ ጊዜን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው። መልሰን ጊዜውን ደግሞ የእርሱን ቃል በማጥናትና ለእርሱ ክብር በመሥራት እናውለዋለን እንጂ ከጠዋት እስከ ማታ የሰይጣንን አሳብ እያስተናገድንና ስለ እርሱ ብቻ እያወጅን ልናሳልፍ አይገባም። በቃሉና በመንፈሱ ሰይጣንን ድል እየነሣን እንድንዞር ጌታ ይርዳን። አሜን።

# እኛ ቤት መሣሪያ አለ

ሰባኪው «በዚህ ምድር ላይ ስንኖር ሕይወታችንን የምንመራበት ከጠላት የምንከላከልበት መንፈሳዊ መሣሪያችን የእግዚአብሔር ቃል ነውና ሁልጊዜ ልንማረውና ልንኖርበት ይገባል።» የሚለውን ትምህርታቸውን በዚህ ምሳሌ አስረዱ።

በደርግ ዘመን የሆነ ታሪክ ነው። መጋቢው «ብሞትም ብኖርም ለጌታ ክብር ነው» ብለው በመቁረጣቸው በዚያ አስጨናቂ ዘመን እያሉ ምንም ጭንቀትና ስጋት ሳይኖራቸው ጌታቸውን ያገለግሉ ነበር። ያለ ስጋትና ጭንቀት በተደላደለ ሁኔታ ወጥተው መግባታቸው ያሳሰባቸው የደርግ ባለሥልጣን ዙሪያቸውን ማጥናት ጀመሩ። «መሳሪያ ቢኖራቸው ነው እንጂ በምን ታምነው ነው እንዲህ ደረታቸውን ነፍተው የሚኖሩት» በማለት ወደ ቤታቸው ያለውን መሣሪያ ለመፈተሽ ሲሄዱ አንድ ትንሽ ልጅ ብቻ አገኙ። ደስ አላቸውና እንዲህ ብለው ጠየቁት «ማሙሽ እናንተ ቤት መሣሪያ አለ አይደል?» አሉት። ማሙሽም «አዎን፥ እኛ ቤት መሣሪያ አለ» አላቸው። «ጎሽ ማሙሽ ምራን አሳየን ከረሜላ እንገዛልሃለን» አሉት። እርሱም ወደ መኝታ ቤት እየመራ ወሰደና አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ከመሳቢያው አወጣና «ይኸው» አላቸው። እነርሱም በመቆጣት «ይኸማ መጽሐፍ ነው፤ እኛ የምንፈልገው ሽጉጥ (መሣሪያ) ነው ቢሉት፤ ልጁ፥ «አይ አባዬ ማታ ማታ የእኛ መሣሪያ ይኸ ነው ይለናልና፥ ሌላ አላውቅም» አላቸው።

«በወንጌል አላፍርምና፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፥ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና» (ሮሜ 1፡16)።

አዎ ወገኖቼ ሆይ፥ በዚህ ምድር ላይ ያሉ የጦር መሳሪያዎች ሁሉ የሚያጠፉ ናቸው፤ የእግዚአብሔር መሣሪያ ግን የሚያድን ነውና እንድንታመንበትና እንድንኖርበት ጌታ ይርዳን። አሜን!

# ክርሞ ጥጃ

ሰባኪው በታላቅ ኮንፈረንስ ላይ ለሕዝብ ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል ብስለት ስለማደግ ሲናገሩ «የእግዚአብሔርን ቃል በግላችን፥ በኅብረትና በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሁሉ እግዚአብሔር በሰጠን ጊዜ በትጋት እያጠናን ከወተት ወደ አጥንት መቆርጠም ማደግ አለብን እንጂ ሁልጊዜ ክርሞ ጥጃ መሆን የለብንም» ለሚለው ትምህርታቸው ይህን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንድ ወጣት በቤተሰብ ውስጥ ጥፋት አጠፋና አባቱ ገረፉት፤ እርሳቸው እየገረፉት እያሉ እናቱ ይደርሳሉ፤ በዚህ ጊዜ እርሳቸውም ጥፋቱ ባይገባቸውም ባልና ሚስት አንድ ልብ መሆናቸውን በተግባር ለልጁ ለማሳየት አብረው በመተባበር ገረፉት። ግርፋቱ ካበቃ በኋላ ለምን እንደተቀጣ ከአስረዱትና ወደፊት በዚህ ጥፋት ፈንታ ሌላ በጎ ነገር እንደሚያደርግ አምኖ ከተቀበለ በኋላ ምሳ ሰዓት ነውና ምሳ ተሰጠው። ለምሳውም በጌታ ፊት ሲጸልይ እንዲህ አለ «ጌታ ሆይ፥ በጠላቶቼ ፊት ገበታን ስላዘጋጀህልኝ አመሰግንሃለሁ።» አለ፤ እንደ ጠላት የሚላቸው ወላጆቹን ነበር። በእግዚአብሔር ቃል ብስለት ስላላደገ አልገባውምና።

አዎ በእግዚአብሔር ፊት ሲታይ የአብዛኛዎቻችን መንፈሳዊ እድገት ከላይ እንደተጠቀሰው ወጣት ታሪክ ይሆን ይሆናል። ብዙ ዘመን በጌታ ቤት አለን፤ ጌታን ግን ደስ የሚያሰኘው ብዙ ዘመን በቤቱ መቆጠራችን ብቻ ሳይሆን እንደ ፈቃዱ በቃሉም ማደጋችንና መብሰላችን ነውና የእግዚአብሔር ቃል በሙላት እንዲኖርብን ጌታ ይርዳን። አሜን!

«ከጊዜው የተነሣ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደገና ያስፈልጋችኋልና፤ የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም» (ዕብ. 5፡2) ።

# ማን ሊበላው ነው!

ሰባኪው «እኛ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ያለብን የእግዚአብሔር ልጆች ነን እንጂ የቁጣ ልጆች አይደለንምና በትንሽ በትልቁ እየተቆጣን ጌታን ማሳዘን የለብንም፤ ይልቁንም በምስጋና በመሞላት በሆነልንና በሆነብን ነገር ፈጣሪን ልናመሰግነውና ልናከብረው ይገባል።» ለሚለው ትምህርታቸው ይህን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንድ በዕድሜአቸው የገፉ አባት ሁልጊዜ በትንሽ በትልቁ ውኃ ቀጠነ ብለው ይቆጡ ነበር። ምንም የማያስቆጣው ቀላልና ትንሽ ነገር ለእርሳቸው ከባድ ነበር። አንድ ቀን ምሳ ሊበሉ እጃቸውን ከታጠቡ በኋላ የቀረበላቸውን ምሳ ሲመለከቱት ሊጨርሱት አይችሉም ነበርና ሙከ ብለው ያቀረበችላቸውን ልጅ «ይህን ሁሉ ማን አባሽ ሊበላው ነው!።» ብለው ተናደዱ።

«በሁሉ አመስግኑ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና።» (1ኛ ተሰ. 5፥18)

ወገኖቼ፥ እንድናመሰግን ተጠርተናል እንጂ መራራ እንድንሆን አልተጠራንም። ውኃ ጥሩ ነው ግን አንድ በርሜል በአንድ ጊዜ መጠጣት ስላልቻልን ማማረር (መቆጣት) የለብንም። ከአሥር ቂጣ ዘጠኙን በልታ አንድ ሲቀራት ማመስገን ሲገባት «ምን ነው ጌታዬ የምግብ ፍላጎቴን ዘጋኸው?» ብላ እንዳማረረችው ሴት መሆን የለብንም። በእውነት ልባችንና አንደበታችን በምስጋና የተሞላ እንዲሆን ጌታ ይርዳን። አሜን!

# ሰገባውና ማህደሩ

ሰባኪው «ጠላት ዲያቢሎስ ተንኮለኛ ነው፤ አዳምና ሔዋንን በተንኮሉ አጥምዶ ከእግዚአብሔር እንደለያቸው ሁሉ፥ እኛንም በረቀቀና ጥበብ በተሞላበት ዘዴው እንዳይጎዳን ሁልጊዜ ነቅተን በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈሱ ልንቃወመው ያስፈልጋል።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለማስጨበጥ የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንድ ሰው በአገሩ ላይ የመጣውን ጠላት ለመከላከል ከአገሩ ወታደሮች ጋር ተቀላቅሎ ወደ ጦር ግንባር ዘመተ። ነገር ግን ጠላት በአቋራጭ መንገድ ላይ አገኘውና ማረከው፤ የታጠቀውንም ሰይፍ ከሰገባው፥ ሽጉጡንም ከማህደሩ ወሰዱና እርሱን እስር ቤት ከተቱት። መሽትሸት ሲልለት ከዚያ እስር ቤት በጨለማ አመለጠና ከሙሉ ትጥቅ ጋር በፈረስ የሄደው ሰውዬ ሁሉንም አስወስዶ ሰገባውንና ማህደሩን ብቻ ታጥቆ ባዶውን ተመለሰ። ባለቤቱም ደህና በመመለሱ እየተደሰተች እንዲህ ብላ ጠየቀችው «እንዴት ሰይፉንና ሽጉጡን ወስደው ሰገባውንና ማህደሩን አልወሰዱትም?» ብትለው፥ «ይኸን እስኪወስዱት ድረስ እኔ ወንዱ ሞቻለሁ እንዴ?» ብሎ መለሰላት።

«በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና።» (1ኛ ጴጥ. 5፡8)።

አዎ፥ ዛሬም ጠላት ዋና ዋና መዋጊያችንን በተንኮሉ ወስዶ ጠላትን ሊጎዳ የማይችል የሥጋ መጫሪያ ይዘን በከንቱ እንዳንፎክር ጌታ በቃሉና በመንፈሱ ጸጋውን በእጥፍ ያብዛልን። አሜን!

# ጅኒ ለማንጫጫት

ሰባኪው «እኛን ክርስቲያኖችን እግዚአብሔር ወደ ራሱ የጠራን በዓላማ ነው። ይኸውም በዚህ በጠማማና በአመንዝራ ትውልድ እርሱን እየፈራንና እያከበርን በጽድቅ ከእርሱ ጋር እንድንኖር፥ ሰዎችን ሁሉ የሚያድነው ወንጌል እንዲሰበክና በሰይጣን ክፉ ሥራና በደዌ ሁሉ ላይ እንድንሠለጥን ነውና፤ ይህንን ዓላማችንን መሳት የለብንም።» ለሚለው ስብከታቸው ይህን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንድ መጋቢ እንዲህ ሲል ስለ ምእመናኑ አሰበ፥ «ለመሆኑ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን እግዚአብሔር በመጀመሪያ ለምን ዓላማ እንደጠራቸው በደንብ ገብቷቸዋል ወይ? ይህን ማወቅ አለብኝ» ብሎ ሦስት ሰዎችን ጠየቀ። «እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ራሱ የጠራህ የመጀመሪያው ዓላማ ምን እንድታደርግ ነው?» የመጀመሪያው ሰው እንዲህ ብሎ መለሰ፥ «በሰዎች ሁሉ ላይ እጆቼን ጭኜ በመጸለይ መንፈስ ቅዱስን እንዲሞሉ ለማድረግ።» ሁለተኛውም እንዲህ አለ፥ «በሥልጣን ቃል እየጸለይኩ በሽተኞችን ለመፈወስ።» የመጨረሻው ሰው በኩራት ደረቱን ነፋ አድርጎ የመለሰው መልስ መጋቢውን እጅግ አስገረመው፥ «እኔ ወደ እግዚአብሔር የመጣሁበት ዋናና የመጀመሪያው ዓላማ ጅኒዎችን ለማንጫጫት ነው።» አለው።

ወገኖቼ፥ እነዚህ ሁሉ መልካም ናቸው፥ ግን ሁለተኛና ሦስተኛ እንጂ የመጀመሪያ ዓላማ ሊሆኑ አይችሉም። የመጀመሪያው ዓላማ በቅድስናና በንጽሕና እርሱን ደስ በሚያሰኝ ሕይወት ከአምላካችን ጋር መኖር ነው። ከዚያ በኋላ የምንመኘው ምኞት ሁሉ ይሳካል። ጌታ ይርዳን። አሜን!

«ወደ ተራራም ወጣ፥ ራሱም የወደዳቸውን ወደ እርሱ ጠራ፥ ወደ እርሱም ሄዱ። ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው፥ ድውዮችንም ሊፈውሱ አጋንንትንም ሊያወጡ ሥልጣን ይሆንላቸው ዘንድ አሥራ ሁለት አደረገ።» (ማር. 3፥13–15)።

# እኔ መንፈስ ነኝ

ሰባኪው «እኛ የሰው ልጆች በዚህ ምድር ስንኖር ንስሐ በመግባትና በጌታ በመታመን የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆንን መንፈሳዊያን ነን እንጂ፥ ቃሉን በመቃረን አንዳንዶች እንደሚሉት እኛ ራሳችን መንፈስ አይደለንም።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለማስረዳት የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

መላው ቤተሰባቸው በክርስቶስ አዳኝነት አምኖ ጥሩ የክርስቲያን ባሕሪ እየተከተለ የሚኖር አንድ ቤተሰብ ያላቸው ሰው ነበሩ። ድንገት ከመሀከላቸው አንደኛው ልጅ ከቀድሞ የክርስቲያን ባሕሪው የተለየ ነገር እያሳየ መጣ። እንደ መንፈሳዊ ሰው ሳይሆን እንደ መንፈስ ያደርገው ጀመረ። ጭራሽ ከነአካቴው በአፉ ለቤተሰቡ «እኔ ሰው ሳልሆን፥ መንፈስ ነኝ» ማለት ጀመረ። ለካስ በጊዜው በተነሣው የሐሰት ትምህርት ተወስዶ ነበር። በዚህ ጊዜ አባቱ ብልህ ነበሩና ለእናቱ ይህንን ትእዛዝ አስተላለፉ። «ልጃችን ከዛሬ ጀምሮ መንፈስ ሆኖአልና መንፈስ ደግሞ ምግብ አይበላምና፥ እኛ ቤት ምግብ እንዳይሰጠው» ብለው አዘዙ። ልጁም ለሦስት ቀን ያህል ያለምግብ ከቀጠለ በኋላ እየደከመ በመሄዱ ማታ በተሰበሰቡበት እንዲህ ሲል ንስሐ ገባ፤ «አባዬ፥ እኔ ሥጋ ነኝ እንጂ መንፈስ አይደለሁምና ምግብ እንዲሰጠኝ ይፈቀድልኝ» አለ።

«ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።» (1ኛ ቆሮ. 6፡20)።

አዎ ወገኖቼ ሆይ፥ እኛ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚኖርብን መንፈሳዊያን ነን እንጂ መንፈስ አይደለንምና እንጠንቀቅ። በሚነፍሰውም የሐሰት ትምህርት ነፋስ ከቃሉ ውጭ ወጥተን ተፍገምግመን እንዳንወድቅ ጌታ ያግዘን። አሜን!

## እናቴንስ አላገባም!

ሰባኪው «እግዚአብሔር ፈቃዱን ለሚፈልጉት ልጆች ሁሉ ይገልጻል ፈቃዱን የሚገልጽበት መንገድም አንዱና ዋናው በቃሉ በኩል ነውና ከዚህ ውጪ ለሥራም ሆነ ለትዳር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ሌላ መንገድ አትጠቀሙ። ምናልባት በሕልምም ሆነ በሌላ መንገድ ለመጠቀም ብትሞክሩ እንኳ መጀመሪያ በቃሉ መዝኑት» የሚለውን ትምህርታቸውን ለማስገንዘብ ቀጣዩን ተናገሩ።

አንድ ወንድም ትዳር ለመመሥረት ፈለገና የትኛዋ ሴት የአሁኑ እጮኛው የወደፊት ደግሞ ሚስቱ እንደምትሆን ለማወቅ እንደሚከተለው ተጠቀመ። እንዲህ ሲል፥ «አሁን ሚስት ታስፈልገኛለች፤ ይህም የመጨረሻ የእግዚአብሔር ፈቃድ የማወቂያ መንገዴ ነው። ዛሬ ጠዋት ቤተ ክርስቲያን ሄጄ ባለው የጸሎት ፕሮግራም ላይ ተንበርክኬ እጸልያለሁ፤ ከእኔም ጎን መጥታ ተንበርክካ የምትጸልየው ሴት ከሆነች የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ማለት ነው፤ እርሷን ሳላቅማማ አገባለሁ» ብሎ እንዳሰበው እሑድ ጠዋት ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ተንበርክኮ ሲጸልይ ከጎኑ አንዲት ሴት መጥታ ተንበረከከች። ቀስ ብሎ ሲያይ ነጠላዋን ይመለከታል፤ ሴት በመሆኗ በጣም ደስ አለው። ጌታም ሚስት በመስጠት ፈቃዱን በዚህ መንገድ ስለ ገለጠለት አመስግኖ ጸሎቱም አልቆ ብድግ ብሎ ሲመለከታት የወለዱት እናቱ ሆነው ተገኙ። ተበሳጨና «እናቴንስ አላገባም» ብሎ ጥሎ ሄደ።

«ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ።» (ኤፌ. 5፥17)።

ቅዱሳን፥ እግዚአብሔር ለእኛ ፈቃዱን ሁሉ በቃሉ ገልጾልናል። ከቃሉ ውጪ ወጥተን በራሳችን ስንሄድ ወድቀን እንዳንገኝ ጌታ ወደ ቃሉ ይመልሰን። አሜን!

## ይነሣሉና እንዳይቀበሩ!

ሰባኪው «የክርስትና መሠረቱና ዋልታው የክርስቶስ ትንሣኤ ነው። ትንሣኤ ባይኖር ኖሮ ክርስትናን ከሌሎች ሃይማኖቶች የሚለየው ነገር ባልኖረ ነበር። ታዲያ ይህንን ያልተረዱ አንዳንድ ሰዎች ወገኖቻቸው በሞት ሲለዩ በጣም ከሚገባው በላይ ያዝናሉ፤ አንዳንድ ጊዜ መቀበር የለበትም ብለው ያውካሉ። ይህንንም የሚደግፉ አጉል መንፈሳዊነት ተጠናውቷቸው የምድሩን እንጂ የሰማዩን የማያስቡ አንዳንድ አገልጋይ ነን ባዮችም አይጠፉም፤ የሞተው ይነሣል በማለት ቀባሪውን ገትረው የሚያውሉ፤ ይህ ግን ትክክልና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። በሕይወታችን የከበረ ጌታ በሞታችንም ቢሆን ሊከበር ይገባዋልና» ሲሉ ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንድ ጊዜ አንድ አማኝ ሞተው አንድ ወጣት ልጅ «ይነሣሉና እንዳይቀበሩ» ብሎ አዘዘና ሁለት ሰዎችን ጸሎት እንዲያደርጉ አዘዘ። እነዚያም ሰዎች ባንጸልይ ምክንያቱ በእኛ ይሆናል ብለው በጸሎቱ ሳያምኑበት ጸለዩ። ሟቹ አልተነሡም ጉባኤውም ግራ ገባው። ከቤት ወጥተው የሚሄዱበት የቀብር ሰዓት ደረሰ። መጨረሻ ላይ ራሱም ጸለየ፤ አሁንም አልተነሡም። በመጨረሻ ማጠፊያው ቢያጥረው ያለመነሣታቸውን ምክንያት እንዲህ ሲል ገለጸ «ተዉት ተዉት አብርሃም በእቅፌ ነውና አታስቸግሩት ብሏል» ብሎ አረፈ። በዚህ ጊዜ ሰዎቹ «አሁን የምንቀብረው ይህን ብቻ ሳይሆን፥ አንተንም ጭምር ነው፥ ብለው ሲነሡበት በጓሮ በር አምልጦ ተሰወረ።

«ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፥ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና።» (1ኛ ተሰ. 4፡14)

አዎ ወገኖቼ ሆይ፥ ሞትም ቢሆን እኮ ጥቅማችን ነውና ለኀዘናችን ልክ ልንሰጠው ልክ፥ ለመንፈሳዊነታችንም እንደ ቃሉ ልናደርገው ይገባል። ለዚህም ጌታ ይርዳን። አሜን!

# የዱላ ቅብብሎሽ

ሰባኪው ለቤተ ክርስቲያን ወጣቶች ወንጌል ሲያስተምሩ « ወጣቶች ጌታ ወንጌልን በ12 ደቀ መዛሙርት ጀምሮ፥ በእምነት አባቶቻችን አድርሶ፥ ዛሬ እኛ ዘንድ ደርሶአልና እኛም በአንድነት፥ በትጋትና በታላቅ ተጋድሎ ይዘነው ወደፊት ልንሮጥ ይገባናል እንጂ በራሳችንና በጊዜው የሥጋ ጉዳይ ተይዘን ወደ ኋላ ልናስቀረው መሞከር የለብንም» ሲሉ ይህን ምሳሌ ተጠቀሙ።

በአንዲት ከተማ የዱላ ቅብብሎሽ ውድድር ሲካሄድ አንድ አስደናቂና ታይቶ የማይታወቅ፥ ድል የሚያጎናጽፍ ሳይሆን ከጨዋታ ውጭ የሚያደርግና የሚያሳፍር ሥራ ተፈጸመ። ታሪኩ እንዲህ ነው፤ ዱላ እየተቀባበሉ በስታዲየሙ ዙሪያ እየሮጡ እያለ የአንደኛው ጓደኛ ዱላውን ይዞ ዘገየበት፥ ተቀባዩ ይጮኻል፥ ኧረ እባክህ፥ ቶሎ በል፥ ዱላውን አምጣልኝ፥ ፍጠን፥ ፍጠን» ቢልም ጓደኛው ስለደከመ ወደ ኋላ ቀረ፤ ከአንድ ጊዜ በላይ ደረቡ፥ ሌሎቹ ሯጮች ሩጫቸውን ጨረሱ። መጨረሻ ላይ እንደምንም ብሎ በብዙ ድካም ዱላውን አምጥቶ ለቀጣዩ ሯጭ ለጓደኛው ሲሰጠው ይኸኛው ከብስጭቱና ከመናደዱ የተነሣ ዱላውን ይዞ ወደፊት መሮጥ ሲገባው ባልንጀራውን ለመጣታት ወደ ኋላ እያሳደደው መሮጥ ጀመረ። «ኧረ እባክህ ሕጉ ወደፊት ነው» ቢለው «ዛሬ እኔ በፈቃዴ ለውጩዋለሁ» እያለ ማሯሯጡን ቀጠለ።

«ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ።» (2ኛ ጢሞ. 2፡2)።

የእግዚአብሔር ሰዎች ሆይ፥ የወንጌል ሕግ ወደፊት እንጂ ወደኋላ አይደለም። አባቶች ደምን አፍስሰው እኛጋ አድርሰዋል። እኛም እርስ በርስ መሳደዱን ትተን የእውነትንና የሕይወትን ወንጌል ወደፊት ይዘን እንድንሮጥና እንድናሸንፍ ጌታ ይርዳን። አሜን!

## ግራ የተጋባው ሰባኪ

ሰባኪው «በዚህ ምድር ላይ ስንኖር አንድ ቀንም ቢሆን የማናንኳኳድለውና ለመኖራችንም ዋስትና የሆነን ነገር ቢኖር ምግብ መመገባችን ነው። ልክ እንደዚሁ ለመንፈሳዊ ሕይወታችንም ሳናንኳኳድል በየቀኑ መመገብ ያለብን ነገር ቢኖር የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ዛሬ ግን ብዙዎቻችን በብዙ ነገር ተይዘን አንዳንዶቻችን በሳምንት አንዴ፥ አንዳንዶቻችን በወር አንዴ፥ አንዳንዶቻችን ደግሞ በዓመት አንዴ የእግዚአብሔርን ቃል እናነብ ይሆናል ምናልባት ጭራሹኑ አናነብም ይሆናል። ስለዚህ የብዙዎቻችን መጽሐፍ ቅዱስ አዲስ ነው፥ በሳምንት አንዴ ከተቀለፈበት ሳጥን ነውና የሚወጣው። የሌሎቻችን ደግሞ በሸልፍ ላይ አቧራ ጠግቧል፥ በየቀኑ የሚያነበው የለምና። በመሠረቱ ከምንም ነገር በፊት ቅድሚያ ሰጥተን ማንበብና ነፍሳችንን መመገብ ያለብን የእግዚአብሔርን ቃል ነው እንጂ ሌላ ነገር አይደለም። ዛሬ ግን እኛ ሌሎችን ነገሮች አስቀድመን የእግዚአብሔር ቃል ወደ ጎን አድርገናል። ይህንን አመለካከታችንን ልንለውጥ ይገባል።» ለሚለው ትምህርታቸው እንዲረዳ የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«ጥሩ መንፈሳዊ ሕይወት የነበረውና በቤተ ክርስቲያን ጥሩ የሚያገለግል ዕለት ዕለት በቃሉ ሕይወቱን ያሳድግ የነበረ ልጅ ዩኒቨርስቲ ገባና ለትምህርቱ ብቻ ትኩረት በመስጠት ጨርሶ እስኪመጣ ድረስ የእግዚአብሔርን ቃል ሳያነብ ቀረ። በመጨረሻም ተመርቆ ሲጨርስ ቤተሰቦቹ ቤት የምስጋና ፕሮግራም አዘጋጁና እርሱ ሰባኪ እንደሚሆን ሲነግሩት አሁን ወደ ረሳው መጽሐፍ ቅዱስ ተመልሶ ሊናገርበት የፈለገውን ጥቅስ ሁሉ በመምረጥ የሰበዝ ምልክት በእያንዳንዱ ላይ በማድረግ መጽሐፍ ቅዱሱን ሰበዝ ብቻ አደረገው። ጊዜው ደርሶ ሊሰብክ መጽሐፉ ቅዱስን ይዞ ወጣና እጆቹን ከመጽሐፍ ጋር ወደ ላይ አንሥቶ ለተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ ሰላምታ ሲሰጥ ምልክት ያደረጋቸው ሰበዞች ሁሉ ከእጁ ላይ ካለው መጽሐፍ ሾልከው በመውደቅ የደስታውን ጊዜ ወደ ኀዘን ለወጡበት። ከዚያም በኋላ የሚያነበው ስለሌለው የተማረው እንዳልተማረ ሆኖ ግራ ገብቶትና አጋብቶ ምንም ሳያነብ አጭር ጸሎት ብቻ አድርጎ ከመድረኩ ወረደ።

ወገኖቼ ሆይ፥ የስኬቶቻችን ምንጭ እኮ እግዚአብሔር ነው። ይህንንም ጌታ የምናውቀው በቃሉ ነውና በቀረልን ዘመን ለቃሉ ቅድሚያ ሰጥተን ነፍሳችንን በመመገብና በማሳደግ እንድንኖር ጌታ ይርዳን። አሜን!

# ክፍል ሦስት

## ስለ ጸሎት

### ለእናቴም ደህና አማች ስጣት

ሰባኪው በአንድ ትልቅ አዳራሽ ውስጥ ለተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ መልእክት ሲያቀርቡ፥ «እኛን የሰው ልጆች ሁሉ እግዚአብሔር በምድር ላይ ያስቀመጠን እንደ ቃሉ ሁልጊዜ እርሱን እንድናመሰግን እንጂ ስለ ራሳችን እንድንለምን ብቻ አይደለም» በማለት የሚከተለውን ምሳሌ በመጠቀም፥ ሁል ጊዜ አመስጋኞች እንጂ መጸለይ ከጀመርንበት ጊዜ አንሥቶ እስከ መጨረሻ ያለው ጊዜ ሁሉ በልመና ብቻ የተሞላ መሆን የለበትም ሲሉ አስረግጠው ተናገሩ።

አንዲት ወጣት ልጃገረድ በጌታ ፊት ሆና የጸሎት ፕሮግራሟን ስትመረምረው ከምስጋና ይልቅ ስለ ራሷ በልመና ብቻ የተሞላ እንደሆን ተረዳችና ለራሷ እንዲህ ስትል ወሰነች። «ከዚህ በኋላ የጸሎት ጊዜዬን ምስጋና ብቻ ነው የማደርገው እንጂ ስለ ራሴ አንድም አልለምንም» በማለት ጸሎቷን ጀመረች፤ እንዲህ እያለች፥ «ጌታ ሆይ፥ ስለ ቤተሰቦቼ አመሰግንሃለሁ፥ ስለ ቤተ ክርስቲያኔ አመሰግንሃለሁ፥ ስለ አገሬና መሪዎቹ አመሰግንሃለሁ።» እንዲህ እንዲህ እያለች ቀጠለችና ድንገት ሳታስበው «በል እንግዲህ ጌታ ሆይ፥ ለእናቴም ጥሩ አማች ስጣት» ብላ ስለ ራሷ ለመነች።

ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ። (ገላ. 6፡2)።

አዎ ምንም ስለ ራሳችን መጸለይ (መለመን) መልካም ቢሆንም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ስለ ራሳችን በልመና ብቻ ተሞልተን ስለ ሌሎች መጸለይንና ማመስገንን እንዳንረሳ። ድል የሚገኘው በልመና ሳይሆን በምስጋና ነውና ይህን እንድናደርግ እግዚአብሔር በጸጋው ይደግፈን። አሜን!

# የድሀው ሰው ጸሎት

ሰባኪው «እግዚአብሔር የሰጠንን ንብረት እግዚአብሔር ራሱ በቃ ብሎ እስከሚቀይረው ወይም እስከሚያሳድግልን ድረስ ያለማንጎራጎር ደስ በመሰኘትና ኑሮዬ ይበቃኛል በማለት መኖር አለብን እንጂ ወደፊት ማጉረምረም የለብንም። የሚያስፈልገንን እግዚአብሔር ሰጥቶናል፥ ይሰጠናልም።» የሚለውን ትምህርታቸውን በምሳሌ አስረግጠው እንደሚከተለው አስተማሩ።

አንድ ሀብታምና አንድ ድሀ እንዲህ ብለው ጸሎት አደረጉ። ሀብታሙ «ጌታ ሆይ፥ ይህቺ ቮልስዋገን መኪና በጣም ከማርጀቷ የተነሣ ሰዎች ለሠርግና ለተለያዩ ፕሮግራሞች አብሬአቸው እንድሆን አይጋብዙኝምና እባክህን አዲስ ማርቼዲስ መኪና እንድትለውጥልኝ እለምንሃለሁ» አሉ። ድሀው ደግሞ «ጌታ ሆይ፥ ዛሬ እራቴን የምበላው ዳቦ የለኝምና እንድትሰጠኝ እለምንሃለሁ።» አሉ። በዚህ ጊዜ የድሀውን ሰው ጸሎት ሀብታሙ ሰሙና «አንተ አሁን ከእኔ ጋር እኩል ቆመህ የዳቦ ጸሎት ታደርጋለህ፥ ይህንን ትንሽ ጸሎትስ እኔ እመልሰዋለሁ።» አሉና ሁለት ብር አውጥተው ሰጡት። ድሀውም «ጌታዬ፥ ከእርስዎ ጸሎት ይልቅ የእኔ ቀድሞ ተሰምቷልና አመሰግናለሁ» ብሎ ሄደ።

«አምላኬም እንደ ባለ ጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል።» (ፊልጵ. 4፥19)።

አዎ ወገኖቼ ሆይ፥ እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ሰጥቶናል፥ ከዚህ በበለጠ ደግሞ እባርክሃለሁ ብሎ ራሱ እስከሚነሣ ድረስ እርሱ በሰጠን ነገር ላይ ረክተንና ተደስተን ያለማንጎራጎር እንድንኖር እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን!

# ወይ ውረድ፥ ወይ ፍረድ

ሰባኪው «በራሳችን ለራሳችን ምንም ማድረግ ስለማንችል መጨነቅ የለብንም። ነገሮች ሁሉ ከአቅማችን በላይ የሆኑት ለእኛ ለሰው ልጆች እንጂ ለእግዚአብሔር አምላክ አይደለምና ጭንቀታችንን ወደ እርሱ እንደ ቃሉ እናምጣ፥ ለጌታ የሚሳነው ነገር የለምና።» የሚለውን ስብከታቸውን ለማስጨበጥ የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«አንድ በጣም የሚያስጨንቁና የሚያስቸግሩ ባላባት ነበሩ። በትንሽ በትልቁ ከሥራቸው ያሉትን ጭፍሮች ያርበደብዱ ነበር። አንድ ቀንም እንደ ልማዳቸው በሰው ዘንድ ማድረግ የማይቻል ትእዛዝ እንዲህ ሲሉ ለጭሰኛው ሰጡ፥ «በሦስት ቀን ውስጥ ከፊትና ከኋላ ራስ ያለው በቅሎ አፈልጋለሁና እንድታመጣልኝ!» ጭሰኛውም እሺ ብሎ ከየት እንደሚያገኝ ግራ ገብቶት ወደ ቤቱ ሄደና ጭንቀቱን ለባለቤቱ ነገራት። እርሷ እንዲህ ብላ አጽናናችው «አይዞህ፥ ለዚህ ጥያቄ ወይ ባዝራችን ትወልዳለች፥ ወይ እግዚአብሔር ይፈርዳል።» አለችውና አብረው በዚህ ጉዳይ ላይ ወደ ፈጣሪ «ወይ ውረድ፥ ወይ ፍረድ» የሚለውን ጸሎታቸውን ቀጠሉ። በሁለተኛው ቀን ባላባቱ ከፈረስ ወድቆ እንደ ሞተ ሲሰሙ፥ «ባላባቱ ሞተ አትበሉን እግዚአብሔር ፈረደ በሉን እንጂ» ብለው ተናገሩ።

«እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት።» (1ኛ ጴጥ. 5:7)።

ቅዱሳን፥ ምን ይሆን ከአቅማችን በላይ ሆኖ ያስጨነቀን ነገርና አልገፋ ያለን ተራራ፤ እግዚአብሔር አምላካችን እውነተኛ ፈራጅ ነውና ወደ እርሱ በእምነት እናቅርበው። እርሱ በቅን ይፈርድልናል። ይህንንም ሁልጊዜ ማድረግ እንድንችል ጌታ በጸጋው ይደግፈን። አሜን!

# የትንሹ ልጅ ጸሎት

ሰባኪው «የእግዚአብሔርን ቃል የበለጠ በማጥናትና በማወቅ እንዲሁም በመኖር ከወተት ወደ አጥንት እየበሰልንና እያደግን ልንመላለስ፥ ጌታንም ደስ እያሰኘን ልናድግና የበለጠ ለማወቅ እንጓጓ እንጂ በትንሹ በቃሉ እውቀት ብቻ ካቆምን ምናልባት ልንስት እንችላለን።» የሚለውን ጤናማና አስፈላጊ ትምህርት ለማስረዳት ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«አንድ ትንሽ ልጅ ሁልጊዜ በቤቱ ሲኖር የሚጸልየው ለምግብ ብቻ ነው፥ ማለትም ምግብ ሲቀርብ፥ ሁልጊዜ እንዲጸልይ የሚጋበዘውም እርሱ ነው። እርሱም በትንሽ አንደበቱ «ጌታ ሆይ፥ ይህንን ምግብ ስለ ሰጠኸን እናመሰግንሃለን። ላጡትና ለተቸገሩትም የሚበሉትን ምግብ እንድትሰጣቸው እንለምንሃለን።» ብሎ ይጸልያል። ታዲያ አንድ ቀን እናቱ በጠና ታመሙና እርሱም እንዲጸልይ አባቱ ጋበዙት። እርሱም በኮልታፋ አንደበቱ የተለማመደውን ከዚህም የተለየ ሌላ ጸሎት የሌለ የመሰለውን ጸሎት እንዲህ ሲል ጸለየ! «ጌታ ሆይ፥ ይህንን በሽታ ስለ ሰጠኸን እናመሰግንሃለን፥ ላጡትና ለተቸገሩትም እንደ ቸርነትህ እንድትሰጣቸው እንለምንሃለን።» ብሎ አረፈው።

አዎ ወገኖቼ ሆይ፥ ዛሬም እኛ በቃሉ ላይ ካለን እውቀት በተጨማሪ የበለጠ ለማወቅ ባለመጣራችን የዱሮዋን ብቻ ይዘን አዲስ ነገር በሕይወታችን ሲመጣ ለመቀበል ፈቃደኞች እንሆንም! ከዚህ የተነሣ ከእግዚአብሔርም ከሰውም ጋር ስንጣላ እንገኛለን። ከእንደዚህ ዓይነት ሕይወት ጌታ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በጸጋው ይጠብቅ። አሜን!

## የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዋሳ ይሁን!

ሰባኪው «እኛ ሰዎች በዚህ ምድር ስንኖር እኔነት ሊያጠቃን አይገባም። «ከእኔ ይልቅ ለባልንጀራዬ» የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳብ ሊኖረን ይገባል እንጂ ሁልጊዜ ነፍስ እንዳላወቀ ሕፃን ልጅ ሁሉንም ነገር ለእኔ ለእኔ እያልን የራሳችንን ጥቅም ብቻ ማሳደድ የለብንም። ይህ እግዚአብሔርን ያሳዝነዋልና» ለሚለው ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ ተናገሩ።

«ታሪኩ የተፈጸመው አዋሳ ነው። እናትና ልጅ አብረው ተንበርክከው ቤታቸው እየጸለዩ ሳለ ልጁ የሚጸልየው ጸሎት እናቲቱን አስገረማቸውና የራሳቸውን ጸሎት መጸለይ አቁመው እንደተንበረከኩ የልጃቸውን መስማት ጀመሩ። እየደጋገመ በተመስጦ ሆኖ ልጃቸው እንዲህ እያለ ይጸልያል። «ጌታ ሆይ፥ እለምንሃለሁ፤ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዋሳ ይሁን!» መጨረሻ ላይ ጸሎታቸውን ሲጨርሱ እናት ስለ ገረማቸው ጠየቁት። «የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዋሳ ይሁን እያልክ የጸለይከው ለምንድን ነው? አዲስ አበባ እንደሆነ አላወቅክም ወይ?» ቢሉት፥ «ትናንትና የ ስድስተኛ ክፍል ሚኒስትሪ ፈተና ላይ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ማን ነው ተብዬ ተጠይቄ አዋሳ ነው ብዬ ስለመለስኩ ራይት እንዳገኝ ነው» አላቸው።

«እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥» (ፊልጵ. 2፡4)።

ወገኖቼ፥ ሁልጊዜ የራሳችንን ብቻ አንመልከት። የራሳችንን ጥቅም ብቻ ከፈለግን በእውነት ላይ እንስታለን። በቀሪው ዘመናችን ከእኛ ይልቅ የሌሎችን ጥቅም እንድናስቀድም አምላክ ይርዳን። አሜን!

# የራብ አድማ

ሰባኪው በቤተ ክርስቲያን ለተሰበሰቡ ሰዎች ሁሉ ስለ ጾም ጸሎት ሲያስተምሩ «በእግዚአብሔር ፊት መጾምና መጸለይ የተገባ ነው። ይህ የሚሰማልን ግን ከቂምና ከቁርሾ ርቀን በልብ ንጽሕናና በቅንነት ሲሆን ነው። በተቃራኒው ግን ወደ ጌታ ብንቀርብ ጾም ሳይሆን የራብ አድማ ነው።» ለሚለው ትምህርታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ የጸሎት አገልጋዮች እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያናችንን እንዲያሳድግ፣ አገራችንን እንዲባርክ፣ በሽታን ከምድራችን ላይ እንዲያጠፋልን፣ ለአንድ ሳምንት የጾም ጸሎት ቀን ይኑረን ብለው ጾም ጸሎት አደረጉ። በሳምንቱ መጨረሻ ላይ በኅብረት በፕሮግራማችን ፍጻሜ ላይ ማዕድ አብረን እንቁረስ በማለት ሁሉም በአንድ ላይ ምግብ ለመብላት ተሰበሰቡ። በዚህ ጊዜ ሁሉም ሁለት ሁለት ሆነው እየበሉ ሳለ ሁለት ወንድሞች ብቻ ከመካከላቸው አይበሉም። አስተናጋጃቸውም «ምን ነው ተጸልዮአል እኮ ለምን አትበሉም?» ቢላቸው እንዲህ አሉት። እኛ እኮ አብረን አንበላም፣ ምክንያቱም ከተኮራረፍንና ከተጣላን ሁለት ወር አልፎናል።» ብለው መለሱለት።

«እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ ነውን. . .?» (ኢሳ. 58፥5)።

ቅዱሳን፣ እርስ በርሳችን ይቅር ሳንባባል በጥልና በኩርፊያ ወደ ጻድቁ አምላክ ፊት በጾም በጸሎት መቅረብ የባሰ ፍርድ ያመጣልና እርስ በርሳችን ይቅር ተባብለንና ተቀባብለን ከእግዚአብሔር ጋር እንድንኖር ፈጣሪ ይርዳን። አሜን!

# ጌታ ሆይ፥ ቤታችን እንዳይጠፋህ!

ሰባኪው «እግዚአብሔር በስሙ ታምነው የሚለምኑትን ሰዎች ጸሎት ይሰማል እንጂ በቤቱ ውስጥ ብዙ ዘመን ማስቆጠራቸውን፥ ብዙ ጊዜ ጾም ጸሎት መያዛቸውን፥ አስራትና መባ መክፈላቸውንና መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብተው ተምረው መመረቃቸውን እንደ ዋና ነገር አድርጎ አይመለከትም። እርሱ ጸሎትን ለመመለስ የሚመለከተው ዋና ነገር እምነትን ነው። ከልባቸው በእርሱ ላይ ታምነው የሚጸልዩትን ሰዎች ጸሎት በእውነት ይሰማል» ለሚለው ስብከታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንድ አገር ውስጥ ያሉ ሚስዮናውያን ባልና ሚስት አንዲት ምስኪን ሴት ያገኙና «ክርስቶስ ከዘላለም ሞት ያድናል።» ብለው ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ይመሰክሩላታል። እርሷም ይህንን አምና በእውነት ሕይወቷን ለጌታ ትሰጣለች። ይህ በእንዲህ እንዳለ ከሳምንት በኋላ የምትወደው አንድ ልጁ በጠና ይታመማል። ወደ ሚሲዮናውያኖቹ ትሄድና ባለፈው ስትነግሩኝ ኢየሱስ ያድናል ብላችሁኝ ነበር፥ እኔም አምኜአለሁ፥ ያድናልና ልጄን ሳይሞት ጌታ እንዲያድነው ጸልዩልኝ» ትላለች። እነርሱም «ጌታ የሚያየው እምነትሽን እንጂ አዲስነትሽን አይደለምና አንቺው ጸልዪ ይሰማሻል» ይሏታል። እርሷም «እኔ አዲስ አማኝ ነኝ ጸሎት አልችልም» ትላለች። እነርሱም «አንቺ ጸልዪ ይሰማሻል» ይሏታል። እርሷም «አዲስ አማኝ ስለሆንኩ ጸሎት አልችልም» ትላለች። እነርሱም «ጌታ የሚያየው እምነትሽን እንጂ አዲስነትሽን አይደለምና ጸልዪ» ይሏታል። በዚህ ጊዜ እጇን አንሥታ ዓይኗን ጨፍና ከእነርሱ ጋር እንዲህ በማለት አብራ ጸለየች፥ «ጌታ ሆይ፥ አንተ አዳኝ እንደሆንክ አምናለሁና ልጄን ፈውስልኝ! ቤታችንም እንዳይጠፋህ ልንገርህ ከዚህ ካለንበት በስተቀኝ በኩል ባለው መንገድ ቀጥታ ትሄድና ወደ ግራ ትታጠፋለህ፥ ታጥፈህም የምታገኘውን የእንጨት በር አልፈህ ገርበብ ያለውን የቤታችንን በር ቀስ ብለህ ልጄን ሳታስደነግጥ ገብተህ ፈውስልኝ፥ አሜን።» ብላ ጨርሳ ወደ ቤቷ ስትሄድ ልጁ ሮጦ እማዬ ብሎ ተቀበላት።

«ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን፦ አንተ ልጅ፥ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ አለው።» (ማር. 2፡5)

አዎን ጌታ እምነትን ያያል። ወገኖቼ ሆይ፥ ጌታ ሲያየው የሚያስደስተውን እምነት አምላክ ይስጠን። አሜን!

# ክፍል አራት

## እግዚአብሔርን ስለማስቀደም

### የተዘቀዘቀው ስፒል

ሰባኪው «በሕይወታችን በዚህ ምድር ላይ በምንኖርበት ጊዜ ከማንም በላይ ሆኖ የሚያጽናናን አምላካችን እግዚአብሔር ብቻ ነውና በእርሱና በእኛ መካከል ሌላ ነገር ሊገባ አያስፈልገውም። የመጀመሪያውን ቦታ ጌታ ብቻ ሊወስድ ይገባል።» በማለት ይህን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አዲስ የተጋቡ ባልና ሚስት አንድ ቀን እርስ በርሳቸው እንዲህ ተባባሉ። ሚስት «አሁን አንተ ተከፍተህ ከውጭ ብትመጣ ወይም እኔ ተከፍቼ ከውጭ ብመጣ እርስ በርሳችን መጽናናት አለብን። ግን በምን እናውቃለን? ስለዚህ አንድ ምልክት እናድርግ» አለችው። ባልም «ጥሩ አሳብ ነው። እኔም የአንቺን ደስታ እንጂ ከፋ አልወድምና ላጽናናሽ እፈልጋለሁ። ለዚህም የሚሆን ምልክት አለኝ ይኸውም የተከፋ ሰው ስፒል በኮቱ ኮሌታ ላይ ዘቅዝቆ በመሰካት ምልክት ይሰጣል፥ እኛም በዚህ እናውቃለን» አላትና ተስማሙ። በቀጣዩ ቀን እርሷ ከአለቃዋ ጋር ተጋጨችና አዝና ስፒል ዘቅዝቃ መጣች። ባልም መከፋቷን አውቆ በእግዚአብሔር ቃል አበረታታት፥ አጽናናት። በቀጣዩ ሳምንት እርሱ እንደዚሁ ስፒል ዘቅዝቆ መጣ፥ እርሷ ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል አጽናናችውና ጸለየችለት። እንዲህ እንዲያ እያሉ ሲቀጥሉ አንድ ቀን ግን አንድ አዲስ ነገር ተፈጠረ። በአንድ ቀን ሁለቱም ተከፉና ሁለቱም እኩል ስፒል ዘቅዝቀው መጡ። በዚህ ጊዜ ማን ያጽናና? በዚህ ጊዜ የሚያጽናናው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

«. . . እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም» (ዘዳግም 33፥26)።

አዎ እውነት ነው እንደ ጥላ የመዘዋወር ባሕሪ የሌለው፥ የማይለወጥና የማይከዳ፥ ከሁሉ በላይ የሆነ እውነተኛ ወዳጅና አምላክ እግዚአብሔር ነው። በቀሪው ዘመናችን ሁሉ ከማንም በላይ በሆነው አባታዊ መጽናናቱና ምክሩ ውስጥ እንድንኖር የእስራኤል ፈጣሪ ቅዱስ እግዚአብሔር ያግዘን። አሜን!

# ማዳበሪያውና ጨዉ

ሰባኪው «በዚህ ምድር ላይ ትልቅ ሀብት ሊኖረን ይችል ይሆናል፤ ዝናችንም በዓለም የታወቀ ይሆናል። በዚህ ሁሉ ግን ክርስቶስ ከሌለን ከንቱዎች ነን፤ ምክንያቱም ሀብትም፥ ዝናም ክብርም፥ በዚህ ይቀራሉ። ክርስቶስ ግን የዘላለም ነው። ዛሬ የምንመካበት ትልቁ ሀብታችን ብርና ወርቅ ሳይሆን ጌታ ኢየሱስ ብቻ መሆን አለበት።» የሚለውን ትምህርቱን ለአድማጮቹ ለማስገንዘብ ይህንን ምሳሌ ተጠቀመ።

«አንድ ማዳበሪያ በመነገድ የታወቀ ሀብታም ሰው ነበር። አንድ ወቅት ላይ ግን ድርጅቱ በእሳት ወደመ። ሰውዬም ከዚህ የተነሣ አበደና በከተማ መዞር ጀመረ እና አንድ ወንጌላዊ አገኘውና ጸለየለት። ስለ ጌታም መሰከረለትና አእምሮውም ልቡም ተፈወሰ፥ ልብስ ለብሶ ጌታን በደህና መከተል ጀመረ። እንደገና ከጥቂት ዓመታት በኋላ የሚከታተለውን ወንጌላዊ ጨው መነገድ እንዳለበት አማከረውና ከአንዳንድ ወገኖቹ ተበድሮ የጨው ንግድ ጀመረ፥ ተሳካለትም። ዕዳውንም ከፍሎ ከጨረሰ በኋላ እንደገና አንድ ቀን የውኃ ሙላት መጣና የጨዉን መጋዘን ባዶ አስቀረው። በዚህ ጊዜ ይህንን አደጋ ወንጌላዊው ሰማ፥ እንዲህም አለ «ባቃ ባለፈው ማዳበሪያው በእሳት ሲበላ አብዶ ነበር፥ አሁን ራሱን ይሰቅላል፤ ለማንኛውም ቶሎ ልሂድና ልየው!» ብሎ ሲሄድ፥ ሳያብድና ራሱን ሳይገድል፥ ነገር ግን ልብሱን እንደለበሰ የመጋዘኑ ትንሽ የውስጥ ቢሮ ውስጥ ቁጭ ብሎ መጽሐፍ ቅዱሱን ያነባል። ወንጌላዊው አንኳኩቶ ከገባ በኋላ «ደህና ነህ ወይ?» እያለ ወተወተው። እርሱም «አዎን ደህና ነኝ፥ ማዳበሪያውን እሳት በላው፥ ጨዉንም ውኃ ወሰደው፤ ኢየሱስ ግን ከእኔ ጋር አለ።» አለው።

«በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም።» (ቆላ. 3፡2)።

አዎ፥ ትልቁ የሰው ልጅ ሀብት ብልና ዝገት የማይበላው፥ የማይከዳና የማይጠፋ ክርስቶስ ብቻ ነውና ቀሪውን ሕይወታችንን ከእርሱ ጋር በእርሱ ጉያ ሆነን እንድናሳልፍ መድኃኒዓለም ይርዳን። አሜን!

# ጭስ ማውጫ

ሰባኪው በቤተ ክርስቲያን ለተሰበሰቡ ምእመናን ሁሉ «በሙሉ ልባችን ለእግዚአብሔር የተሰጠ ኑሮ መኖር አለብን። ክርስትና የምር ነው፤ የልብም ነው እንጂ የአፍ ብቻ አይደለም። ከአፋችን ይልቅ ሕይወታችን የእግዚአብሔርን ማንነት መመስከር አለበት። ይህ እንዲሆን ሰዎችን ፈርተን ሳይሆን እግዚአብሔርን ፈርተንና አክብረን መመላለስ አለብን።» የሚለውን ስብከታቸውን ለአዳማጮቻቸው ለማስገንዘብ የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ!

አንድ በቤተ ክርስቲያን ሌላ፥ በውጭ ደግሞ ሌላ ሕይወት ያለው ሰው ነበረ። አንድ ቀን ማንም አያየኝም ብሎ በገመተው መንገድ ላይ ሲጋራ እያጨሰ ሲሄድ ድንገት የቤተ ክርስቲያኑን መጋቢ ከፊቱ ሲመጣ ያየዋል። አሁን ሲጋራውንም ለማጥፋት ጊዜ አላገኘምና ከድንጋጤው የተነሣ እንዳለ ኪሱ ውስጥ ከተተውና መጋቢውን ተገናኘ፥ ጨበጠው፥ ሰላምታውንም አቅኃደኃደ። «እንደምን አሉ? እኔ ደህና ነኝ። ጌታ ይባረክ። ኢየሱስ ጌታ ነው። ሃሌ ሉያ አሜን. . .» እያለ። በዚህ ጊዜ ሲጋራው ኪሱ ውስጥ ሥራውን ቀጠለና ኮቱ መጨስ ጀመረ። መጋቢውም «አንተ ደህና ነኝ፥ ጌታ ይባረክ፥ ሃሌሉያ እያልክ በአፍህ ደኅንነትህን ታውጃለህ፥ ነገር ግን ይህ ከኃንህ የሚወጣው ጭስ ምንድን ነው? እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ሲጋራ ማጨስ የሚያስፈልገው ቢሆን ኖሮ ገና ከመጀመሪያው አዳምን ሲፈጥር ጭስ ማውጫም ጨምሮ ይሠራለት ነበር። ልክ አይደለህም።» ብሎ ገሠጸው።

«እግዚአብሔር ሳያልን አለው የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርጌአለሁ ትላለህ ነገር ግን ይህ ከበስተጀርባ የምሰማው ግሳት ምንድን ነው?»

አዎ ወገኖቼ፥ ሕይወታችን የቃል ብቻ ሳይሆን የተግባርም ይሁን። ምስክርነታችንን የሚያጠፋው የአፋችን ቃል በተግባር ስለማይታይ ነውና እንጠንቀቅ። ጌታን ደስ የሚያሰኝ በሰውም በእግዚአብሔርም ዘንድ አንድ ዓይነት የሆነ ሕይወት ይዘን እንድንመላለስ እግዚአብሔር አምላክ ራሱ ይርዳን። አሜን!

## *በአፍንጫዬ ይውጣ!*

ሰባኪው «ዓይናችንን ሁል ጊዜ በጌታ ላይ ብቻ ማድረግ አለብን እንጂ በሰዎች ላይ ብቻ ካደረግን ልንሰናከል እንችላለን፥ ሰዎች እንከን አይታጣባቸውምና። ሰዎችንም አይተን ክርስትና እንደዚህ ከሆነ በአፍንጫዬ ይውጣ ማለት የለብንም። ይልቁንም የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ የሆነውን ክርስቶስን ተመልክተን ከፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት ልንሮጥ ያስፈልጋል።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለማስጨበጥ የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንድ ሰው ጌታን ካመነ በኋላ ከዘፍጥረት ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነብ ወንጌላዊው ከተከታተለው በኋላ ይነግረዋል። ሰውዬውም ከዓመት በኋላ ዕብራውያን ምዕራፍ 13፡7 ላይ ይደርስና «መጽሐፍ ቅዱስን ሁለተኛ አላነብም ብሎ ለወንጌላዊው ይነግረዋል።» «ለምን» ሲለው «ከዘፍጥረት–ዕብራውያን 13፡6 ጥሩ ነበር 7 ላይ ግን «ሰዎችን ምሰሉአቸው» ብሎ ያስተምረናልና ሰዎችን መምሰል ስለማልፈልግ አላነብም አለው።» ወንጌላዊውም «ዕብ. 13፡7 ደርሰህ ከሆነ ያቆምከው እባክህ ዕብ. 13፡8ን አንብብና አቁም» አለው። እርሱም እሺ ብሎ ሲያነብ «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።» ይላል። በዚህ ጊዜ ሰውዬው እኔ ጥፋተኛ ነኝ የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን ሁሉ መታዘዝ ሲገባኝ በተዛባና የሥጋ አስተሳሰብ ውስጥ ወድቄአለሁ ብሎ ንስሐ በመግባት ንባቡን ቀጥሎ ደስ እያለው ዮሐንስ ራእይ ድረስ አንብቦ ጨረሰ።

አዎን፥ የጌታን ቃል በችኮላ ሳናስተውል እያነበብን ከመሰናከል ይልቅ በጥንቃቄ ተረድተን ለተግባር መሰናዳት ይበጃል። ለዚህም ጌታ ይርዳን። አሜን!

# እሰይ ፈጀኝ

ሰባኪው የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ሁሉ ሰብስበው የአንድ ቀን ትምህርት ሲሰጡ «የምናመልከውና የምናገለግለው አምላክ እውነተኛ አምላክ ነው። እኛም በእውነትና በጽድቅ ልናገለግለው ይገባል። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኃጢአት በእጅና በእግሩ እየገባ ዝም ብለን ማለባበስ የለብንም። እውነትን እንናገር እንጂ ገና ለገና ቀለባችን ይቀራል ወይም ከሰው ጋር እንቀያየማለን ብለን ከእውነት መሸሽ አያስፈልግም።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለተማሪዎቻቸው በሚከተለው ምሳሌ አስረግጠው ተናገሩ።

«አንድ ሰው በጠና ታመመና ይፈውሳል የተባለለትን ጠበል ለመጠመቅ ሩቅ አገር ሄደ። እዚያም እንደደረሰ ሰዎች እንዲህ አሉት፥ ይህ ጠበል ይፈውሳል፥ ይፋጃልም፥ የሚፈውስህ በምትጠመቅበት ጊዜ እሰይ የምትል ከሆነ ነው እንጂ ፈጀኝ ፈጀኝ የምትል ከሆነ አይፈውስህም አሉት። በዚህ ጊዜ ሰውዬው ጠበሉ ውስጥ ገባና ሲያየው በጣም ተቸገረ እንዳሉት እሰይ እሰይ እንዳይል ፈጅቶታል (አቃጥሎታል)፥ ፈጀኝ ፈጀኝ እንዳይል አይፈውስህም ብለውታል፤ ስለዚህ ሁሉም እንዳይቀር፥ «እሰይ ፈጀኝ፥ እሰይ ፈጀኝ» አለ።

አዎን ወገኖቼ፥ እኛ የእግዚአብሔር ባሪያዎች እውነቱን እውነት፥ ውሸቱን ውሸት ካላልንና የተሰማን ሌላ ሆኖ ሳለ የምናሰማው ግን ሌላ ከሆነ እግዚአብሔር አይከብርም። ቤተ ክርስቲያንም አትጸዳም። በቀሪው የአገልግሎት ዘመናችን ለእውነት ቆመን ለእውነት እንድንወድቅ ጌታ ይርዳን። አሜን!

«ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፤ እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ።»

ኤፌሶን 4፥25

# የምተኛው የት ነው?

ሰባኪው «የእግዚአብሔር ሰዎች በየትኛውም ዓለም እንኑር በግልጽነትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆነ ፍርሃት ነፃ ወጥተን ልንኖርና ልናገለግል ይገባናል፤ እንጂ በይሉኝታ ተይዘን መጎዳትና ሰዎችንም መጉዳት የለብንም።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለአድማጮቻቸው ለማስገንዘብ ይህንን ምሳሌ ተናገሩ።

«አንድ የእግዚአብሔር ሰው ጌታውን ለማገልገል ጌታ በከፈተለት በር ተጠቅሞ ወደ ውጭ አገር ሄደ። አንድ ቀን ሲያገለግል ውሎ ማታ ወደሚያርፍበት ሆቴል መጣ። አስተናጋጆቹም የሚያርፍበትን ክፍል አሳዩትና ቁልፉን ሰጡት። እርሱም ክፍሉን ከፍቶ ሲገባ ምንም ዕቃ የሌለበት ባዶ ክፍል ሆኖ አገኘው። በዚህ ጊዜ ሰውየው ራሱን ጠየቀ፥ የት ነው የምተኛው? አልጋ የለም፤ የማርፍበት ወንበር የለም፤ ይህን በመሰለ የሠለጠነ ሀገር ውስጥ እንዴት መሬት እተኛለሁ? መጠየቅ አለብኝ ብሎ መጥሪያ አድርጎ አስተናጋጁን ጠራና «የእኔ ወንድም፥ አልጋ የለ፥ ወንበር የለ የማርፈውና የምተኛው የት ነው?» ቢለው አስተናጋጁ ከየግድግዳው ውስጥ ገብተው የተሰወሩትን ዕቃዎች ሁሉ ጫፍ ጫፋቸውን እያያዘ ሁሉንም ከያሉበት መዞ አወጣቸው። መጨረሻም ላይ፥ «ጌታዬ፥ እርስዎ ብልህና አዋቂ ሰው ነዎት፤ ብዙ ሰዎች መናገር አስፈርቶአቸውና ይሉኝታ ይዟቸው ወለሉ ላይ ተኝተው አድረው ሄደዋል» አላቸውና በሩ ዘግቶላቸው ሄደ።»

«ነገር ግን ኬፋ ወደ አንጾኪያ በመጣ ጊዜ ፊት ለፊት ተቃወምሁት ይፈረድበት ዘንድ ይገባ ነበርና።» (ገላ. 2፡11)

አዎ፥ ያለ ፍርሃትና ይሉኝታ ጌታን አገልግለን ቤተ ክርስቲያንና ራሳችንንም ጠቅመን ቀሪውን ዘመናችንን እንድን ጨርስ ጌታ ይርዳን። አሜን!

# አለች አትበላት

ሰባኪው «በሰማይም ሆነ በምድር የሰውን ልጆች የሚያድን ጌታ ብቻ ነው፤ ያለ እርሱ መዳን የለም፤ ከኩነኔ በታች ነን። ልንበላ፥ ልንጠጣ፥ ልንለብስና ልንደሰት እንችላለን፥ ነገር ግን የሞትን ነን ወይም እያለን የሌለን ነን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ጎድሎናልና።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለማስጨበጥ ይህን ምሳሌ ተናገሩ።

«አንድ ሰው ባልንጀራውን ሲመክረው «ለምን አታገባም?» ሲለው፥ «አለች የምላት ጥሩ ልጅ አጥቼ ነው።» ይለዋል። በዚህ ጊዜ መካሪው፥ «እጅግ በጣም ጥሩ ልጅ እኛ ሰፈር አለች እርሷን አግባ። ትንሽ ብቻ እግሯ ሽፋፋ ነው፥ አንድ ዓይኗ ጠፍቷል፥ አንድ እጅም የላትም፥ ፀጉሯንም ላሽ በልቶታል፥ አፍንጫም የላት እንጂ ጥሩ ልጅ አለች» ሲለው፥ ድንገት አቋረጠውና «ተወው ተወው፥ ይህችንማ ምን አለች ትላታለህ፥ አለች አትበላት የለችም እንጂ» አለው።

«ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም።» (1ኛ ዮሐ. 5፥12)።

አዎ ቅዱሳን፥ አንዳንድ ጊዜ የሕይወት ውበት ከእኛ ተወስዶብን እኛ አለን እያልን እናወራለን ወይም እናስወራለን እንጂ የለንም። ያለ ክርስቶስ የሞትን ነንና ነፍሳችን ከመለየቷ በፊት የዘላለሙን ዋስትናችንን ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛችን አድርገን እንድንቀበል ጌታ ይርዳን አሜን።

# የቀለበት መንገድ

ሰባኪው «ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው። አካሉ ደግሞ እኛ የእርሱ መንፈስ ቅዱስ ያለብን ሰዎች ነን። የሰውነት ክፍል ሁሉ በራስ እንደሚመራ ሁሉ እኛም በክርስቶስ ልንመራ ይገባል። ዛሬ ብዙ ሰዎች ሕይወታቸውን ሊያድን ለሚችለው ለክርስቶስ መስጠት ሲገባቸው በተቃራኒው ለሌሎች ነገሮች ሰጥተው ይሆናል። ይህ ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለአድማጮቻቸው ለማስጨበጥ የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንድ ወንጌላዊ ሰዎች ሕይወታቸውን ለጌታ እንዲሰጡ ወንጌልን በየመንገዱ እየሰበከ በሚዞርበት ጊዜ አንድ የጸጉሩ አቆራረጥ የሚያስገርም ወጣት ልጅ ያገኛል። የጸጉሩን ዙሪያ ክብ አድርጎ ተቆርጧል! የመካከሉ ደግሞ እንደ መስኖ በይ ዓይነት በቀጭኑ ተላጭቶ ለትልቁ መንገድ የሚገቡሩ ዓይነት ሆነው ተሠርተዋል። በዚህ ጊዜ ወንጌላዊው ገረመውና «ጸጉርህን እንደዚህ የተሠራኸው ለምንድን ነው? እስቲ ንገረኝ» ሲለው፥ ወጣቱ እንዲህ አለ፥ «ይኸ የምታየው ክቡ የቀለበት መንገድን ይወክላል፥ እነዚህ ቀጫጭኖቹ ደግሞ ለእርሱ የሚገቡሩ መንገዶች ናቸው። በሁሉም ሙሶ፥ ቲኮና መርቸዲስ የሚባሉ መኪናዎች ይሄዱበታል» ሲለው፥ ወንጌላዊ ተገረመና ረጋ ባለ ሁኔታ፥ «የእኔ ወንድም ራስህን ለቀለበት መንገድ ለሙሶና ለቲኮ ከምትሰጥ ለክርስቶስ ብትሰጥ ይሻልሃል።» ብሎት ስለ እውነተኛውም ወንጌል ነግሮት ተለያዩ።

«. . . እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ።» (ኤፌ. 4:15)።

አዎ ወገኖቼ፥ የዚህ ዓለም መልክና ውበት ሁሉ ጠፊና አላፊ ነውና የሕይወት ሁሉ ራስና መሪ ለሆነው ለዘላለሙ ጌታ ለአምላካችን ነፍሳችንን በእጁ እንድንሰጥ ጌታ በጸጋው ያግዘን። አሜን!

# እርሳቸውን ትመስላለች

ሰባኪው «ከማጉረምረም ይልቅ እግዚአብሔርን ልናመሰግነው ይገባናል። ምክንያቱም ያለነው በእርሱ ቸርነት ነውና። ጠበቃችንና አማላጃችን የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ ቀኝ ሆኖ ሁልጊዜ ባይማልድልንና በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ባይገባ ኖሮ፥ እንደኛ በደልና ክፉ ሥራማ ቢሆን ኖሮ እስከ ዛሬ በጠፋን ነበር።» ለሚለው ስብከታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንድ ቄስ በፊታቸው ላለው የሰንበት መልእክት ስብከት ለሕዝባቸው ለማቅረብ በቤታቸው ሆነው ዝግጅት እያደረጉ ሳለ ትንሿ ልጃቸው ትረብሻቸው ጀመር። ጀርባቸው ላይ እየወጣች የጻፉበትን ማስታወሻ እየቀደደችና እየጣለች ተይ ተይ በማለት ብዙ ታገሷት። መጨረሻ ላይ ግን በሚያነቡት መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የብርጭቆውን ውኃ ብድግ አደረገችና ከለሰችበት። በዚህ ጊዜ በጣም ተበሳጩና ብድግ አድርገው ወደ ሰማይ አንሥተው መሬት ሊያፈርጧት ሲሉ፥ ቀና ብለው መልኳን ሲያዩአት ቁርጥ እርሳቸውን ትመስላለች። በዚህ ጊዜ ልባቸው ራራና ሶፋ ላይ ቀስ ብለው አስቀመጧት።»

«የሞተው፥ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።» (ሮሜ 8፡34)።

አዎ፥ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ሊያጠፋን ያስብና ዘወር ብሎ በተቀመጥንበት በቀኙ ሲያይ ኢየሱስን ያየዋል። እኛም ልጁን ስለምንመስል ምሕረትን ያደርግልናል። ይህ ግን የበለጠ እንድንፈራውና እንደ አባትነቱ እንድናከብረው የሚረዳን እንጂ በበደል እንድንቀጥል የሚያደፋፍረን አይደለምና ነቅተን በምስጋና ሕይወት እንድንከተለው ጌታ ይርዳን። አሜን!

# ስልሳ ሚሊዮን

ሰባኪው «እግዚአብሔር ባስቀመጠን በዚህ ምድር ላይ ለእውነት በእውነት ሠርተን፥ እግዚአብሔርን ደስ አሰኝተን፥ ሰዎችንም ጠቅመን ማለፍ አለብን እንጂ ለወንድሜ ይጠቅማል በሚል በከንቱና ረብ በማይሰጥ ነገር ውስጥ መዘፈቅ የለብንም።» ለሚለው ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ እንደሚከተለው ተጠቀሙ።

«አንድ መሥሪያ ቤት ውስጥ በወጣው ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ዘመዱን ለማስገባት የፈለገው ባለሥልጣን ለዘመዱ እንደሚያመች አድርጎ ጥያቄዎችን አዘጋጀና መጀመሪያ ዘመዱን፥ ቀጥሎ ሌላውን ሰው አስገባና ጥያቄዎቹን ጠየቀ። ለዘመዱ «የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ስንት ነው?» የሚለውን ጠየቀ! ዘመዱም በጥሩ ሁኔታ መለሰለት፥ አመሰገነውና ሸኘው። እንዲወድቅ የሚፈልገውን ሁለተኛውን ሰው ደግሞ አስገባና፥ «ከአንተ በፊት የተወዳደረውን ሰው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ስንት ነው ብዬ ጠይቄው 60 ሚሊዮን ብሎ መልሶልኛል! አንተ ደግሞ የእያንዳንዳቸውን ስም ጥራ!» አለውና አሳረፈው።

«ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቁጠር! እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ።» (ፊልጵ. 2፡3-4)።

አዎን፥ ወገኖቼ፥ ሰው ባያየን እግዚአብሔር ያየናልና የተቀመጥንበትም ወንበር አንድ ቀን ይከዳናልና ግፍ አንሥራበት። እኛ ኢትዮጵያውያን በቀረው ዘመናችን አንተ ትብስ፥ አንቺ ትብሽ ተባብለንና ተሳስበን ሕይወታችንን እንድንፈጽም እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን!

# ዓለምን አልከድም!

ሰባኪው «እግዚአብሔር እኛን የሰው ልጆችን በዚህ ዓለም ላይ ፈጥሮ ሲያኖር በክፋው ዓለም ደጉን እግዚአብሔርን እያሳየን እንድንኖር እንጂ የጽድቅን ኑሮ ትተን ዓለምንም ወድደን በዓለማዊነት እንድንኖር አይደለምና፤ ዛሬ ዓለምን ከነክፋ ሥራዋ ክደን ወደ እግዚአብሔር ፊታችንን ልንመልስ ይገባል» ለሚለው ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ አቀረቡ።

በአንድ ትልቅ የወንጌል ስብከት በሚካሄድበት ቦታ ብዙ ሰዎች የወንጌሉን የማዳን ጥሪ ሰምተው ንስሐ ለመግባት በሰባኪው አማካይነት ወደ መድረኩ ወደፊት መጡ። ሰባኪውም «እኔ የምለውን ከእኔ ቀጥላችሁ በሉ ብሏቸው ቀጠሉ።» «ሰይጣንን ክጃለሁ፥ ሥራውን ክጃለሁ፥ ሥጋዊነትን ክጃለሁ፥ ዓለምን ክጃለሁ. . .» ድንገት አንዱ ሰው ከመካከላቸው ደህና ሲሉ ቆይተው ዓለምን ክጃለሁ የሚለው ጋ ሲደርሱ «አልክድም» አሉ። «ምን ነው?» ተብለው ሲጠየቁ «ዓለምን፥ ዓለም ክፉ ቀን ያወጣችኝ የክፉ ቀን ወዳጄ ናትና አልክድም» አሉ። ለካ ሲጠና ሰውየው «ዓለም» የምትባል የብዙ ዓመት ውሽማ አለቻቸው።

«ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል።»

ሰዎች፥ እንታለል በዚህ ዓለም ያለው ሁሉ የሥጋ ምኞት፥ የዓይን አምሮት ነውና እንመለስ። የነፍሳችን አዳኝ የሆነውን ጌታ እንመን፥ ከእርሱም ጋር ተጣብቀንና ተስማምተን ዓለምንና ዓለማዊነትን ክደን በጽድቅ እንድንኖር እግዚአብሔር አምላክ ይርዳን። አሜን!

## የፋሲካው በሬ

ሰባኪው «በዚህ ምድር ላይ ስንኖር ውለን መግባታችን፥ አድረን ማንጋታችን ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና ምንም ነገር በሕይወታችን ላይ ከማድረጋችን በፊት በእኛ ላይ መልካም ዓላማ ያለውን ጌታችንን ፈቃዱን መጠየቅ አለብን።» ለሚለው ስብከታቸው ይረዳቸው ዘንድ ይህንን ምሳሌ እንደሚከተለው ተጠቀሙ።

«ሁለት ሰዎች የፋሲካ ሰሞን በሬ በግ ሊገዙ ወደ ገበያ ሲሄዱ አንድ አማኝ መንገድ ላይ ያገኛቸውና ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ወዴት እንደሚሄዱ ይጠይቃቸዋል። አንደኛው ቀደም ብሎ እግዚአብሔር ቢፈቅድ በግ ልገዛ ነው የምሄደው ሁለተኛውም ሰውዬ በመቀጠል እኔም «በሬ ልገዛ እየሄድኩ ነው» ይለዋል። በዚህ ጊዜ መንገድ ላይ ያገኛቸው አማኝ «በሬ ልገዛ ነው ብቻ ለምን ትላለህ? እግዚአብሔር ቢፈቅድ፥ በሬ ልገዛ ነው ለምን አትልም? ያለ እርሱ ፈቃድ ምንም ማድረግ አንችልም» ባለው ጊዜ በስጩት አለና፥ «እናንተ ደግሞ ታበዙታላችሁ። ምንድን ነው ይኸ ሁሉ ጭንቀት? 500 ብር በኪሴ ይዣለሁ፥ በሬ ገበያ ይጠብቀኛል፥ ሄጄ ብቻ መግዛት ነው» ብሎት ጥሎት ይሄዳል። ነገር ግን እንዳሰበው ሳይሆን መንገዱ ላይ ወንበዴዎች ጠብቀው ዘርፈውና እንከት አድርገው ደብድበው ይለቁታል። በሬውንም ሳይገዛ እያነከሰ ሲመለስ ያው አማኝ ሰውዬ ያገኘውና «ምን ሆንክ? ወዴት እየሄድክ ነው?» ቢለው፥ «እግዚአብሔር ቢፈቅድ ወደ ቤቴ እየሄድኩ ነው» አለው ይባላል።

«ያለ እርሱ ፈቃድ የበላ ደስ ብሎትም ተድላን የቀመሰ ማን ነው? (መክ. 2፡25)

አዎ ወገኖቼ ሆይ፥ ሁሉ ነገር ቢኖረንም ያለ ጌታ ፈቃድ ምንም የማድረግ አቅም የለንምና በሕይወታችን የእርሱን ፈቃድ እንድናስቀድም አምላክ ይርዳን። አሜን!

# ወ/ሪት ብርጭቆ

ሰባኪው «ባሕሪው ሁልጊዜ የማይለዋወጠውን አምላክ እግዚአብሔርን እያየን በዚህ ምድር ላይ ካልኖርን፥ ልባችንንና ዓይናችንን በሰው ላይ ካደረግን እንጎዳለን፥ እንሰበራለን፤ ሰው በባሕሪው ተለዋዋጭ ነው። ነገር ግን የተቀጠቀጠ ሸንበቆን የማይሰብረውን፥ የሚጤስን ጧፍ የማያጠፋውን የደካሞችን ወዳጅ እግዚአብሔር እንመልከት።» የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከታቸውን ለአድማጮቻቸው በሚገባ ለማስጨበጥ ሲሉ የሚከተለውን ምሳሌ ተናገሩ።

«በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምትገኝ አንዲት ወጣት ነበረች። ታዲያ ሁልጊዜ ዓይኖቿ ከጌታ ይልቅ ወደ ሰዎች ይመለከታሉ ወይም ሰውን ታስቀድማለች። ከዚህም የተነሣ ኀዘንም ደስታም ይደርስባት ነበር። ቶሎ ሮጣ ወደ ሰው ነው የምትሄደው። «ከዚህም የተነሣ ሰውን እንዳሰበችው ሆኖ ስለማታገኘው ትጎዳለች። እና ሁልጊዜ ቋንቋዋ፥ «እከሌ እንደዚህ ብላ በመናገር ሰበረችኝ፤ እከሌ ሰበረኝ። እነእከሌም በኅብረት ሆነው ሰበሩኝ።» በዚያ ቤተ ክርስቲያን «መሰበር» በሚል ጉዳይ ነው የምትታወቀው። ታዲያ ይኸ «ሰበረኝ» «ሰበረችኝ» ያሰለቻቸው ሰዎች «ወ/ሪት ብርጭቆ» ብለው ስም አወጡላት።

አዎ ቅዱሳን፥ የተሰበረውን የሚጠግነውንና የወደቀውን የሚያነሣውን ጌታን እንመልከትና በእርሱ እንታመን እንጂ፥ ዓይኖቻችን በሰዎች ላይ ካደረግን እንጎዳለንና እንጠንቀቅ። ከዚህ ዓይነትም አካሄድ እግዚአብሔር ያድነን። አሜን!

**«ትመልስልኛለህና በመከራዬ ቀን ወደ አንተ እጠራለሁ።» [መዝ. (86)፥7]።**

## አባዬ በላኸው!

ሰባኪው «ሰዎች በአብዛኛው ከአባታችን ከእግዚአብሔር ጋር የምንጣላው በሆድ ነውና እንዴት እንደምንበላና እንዴት እንደምንጠጣ እንጠንቀቅ። ጌታ በፈቃዱ የወሰነልን ይበቃናልና የማይገባንን በልተን ስንጣላ እንዳንገኝ። አዳምና ሔዋን፥ ያዕቆብና ኤሳው፥ እስራኤልና እግዚአብሔር፥ ደቀ መዛሙርትና ጌታ ኢየሱስ፥ በአብዛኛው ሁልጊዜ የሚጣሉበት ዋናው ምክንያት ሆድ ነበረ። ዛሬም እኛ ልናስብ ይገባል።» ለሚለው ትምህርታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

በአንድ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ቁርባን ሥርዓት እየተካሄደ ነው። ሕዝቡ በአንድ እጁ የጌታን ሥጋ የሚወክለውን ኅብስቱን ይዟል፥ በሌላ እጁ ደግሞ የጌታን ደም የሚወክለውን ወይኑን ይዟል፤ ሰባኪውም «የጌታን ሥቃይ፥ ሞትና ትንሣኤ የሚያሳስበንን ይህንን ቅዱስ ሥርዓት ስንወስድ ሳይገባን እንዳይሆን ራሳችንን እንመርምር፥ የተጣላን ካለን ይቅር እንባባል» እያሉ ተናገሩ። በዚህ መሀል አንዲት ትንሽ ልጅ ከጉባኤው መሐል አባቷን ፈለገችና አገኘችው፤ ሄደችና ከእግሮቹ መሀል ገብታ ወደ ጆሮው ጠጋ ብላ፥ «አባዬ፥ እነዚህን በሁለቱም እጆችህ የያዝካቸውን የሚበሉ ነገሮች እፈልጋቸዋለሁና ሰው ዓይኑን ሳይገልጥ ስጠኝና ልብላቸው!» አለችው። አባትም «ይህ ለአንቺ አይገባም፥ ከቤታችን ሌላ ነገር እሰጥሻለሁ» ቢላትም ጥያቄዋን ቀጠለች። ፕሮግራሙን የሚመሩትም ቄስ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው «አሁን ሁላችንም በአንድነት ሁለቱንም እንወስዳለን!» ሲሉ ዓይኗ እያየ አባቷ ሳይሰጣት ሁለቱንም በአንድነት በላቸው። በዚህ ጊዜ በጣም ተበሳጭታ ወደ አባቷ ጆሮ ጠጋ አለችና «አባዬ በላኸው!» ብላ ጮኸችበት። ከቤተ ክርስቲያን ጀምሮ እስከ ቤት ድረስ አኮረፈች። አባትና ልጅ በሆድ ተጣሉ።

«. . . ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍም በልተሃልና ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን!» (ዘፍ. 3፥17)።

አዎ፥ የማይገባንን በልተን ዛሬም እርግማን በራሳችን ላይ እንዳናመጣ ጌታ ይርዳን። አሜን!

# ዓለም ሁሉ ገምቷል ለካ!

ሰባኪው ዛሬ ሰዎች «የዚህ ሁሉ በደል ምክንያት እኔ ነኝና እኔን ይቅር በሉኝ፥ እኔን ማሩኝ!» ብለው ከመቅረብ ይልቅ ወደ ሌላው ማሳበብን ይመርጣሉ። የቤተሰባችን በረከት መጥፋት ምክንያት እከሌ ነው። የቤተ ክርስቲያናችን ፈውስ መጥፋት ምክንያቶቹ እነእከሌ ናቸው። የአገራችንም በዚህ ሁሉ ችግር ማለፍ ምክንያቶቹ አሁንም እነእከሌ ናቸው እንጂ ለዚህ ሁሉ ምክንያት እኔ ነኝ ብሎ የሚቀርብ ሰው የለም። ይህ ደግሞ ከአባታችን ከአዳም የወረስነው ነው። «አትብላ ካልኩህ በላህ ወይ?» ብሎ እግዚአብሔር ሲጠይቀው «አዎን» በልቻለሁና ይቅር በለኝ!» ማለት ሲገባው፥ «ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርሷ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ» ብሎ ጥፋቱን ሔዋንን ሰጪ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔርም ወደ ሔዋንም አዞረ። ከዚህም የተነሣ ምድር ተረገመች። እኛና ምድራችን፥ እንድንባረክና እንድናድግ፥ ራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት ገልጠን እናቅርብ።» ለሚለው ትምህርታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተናገሩ።

«አንድ ረጅም ጺም ያለው ሰው ነበር። ታዲያ ሁልጊዜ ጺሙን አጥቦ ስለማያጸዳው የሚበላውና የሚጠጣው የምግብ ፍርፋሪ ሁሉ ጺሙ ውስጥ እየገባ ከመቆየቱ የተነሣ ጺሙ እየከረፋ መጣ። ይህንን ግን ራሱም አላወቀውምና፤ አንድ ቀን ቤት ሲገባ ሸተተው፥ ወደ መኝታ ቤቱም ሲገባ ያ ሽታ ሸተተው። ወደ ውጭም ቢወጣ ያው ዓይነት ሽታ ሸተተው፥ በዚህ ጊዜ እንዲህ አለ «ዓለሙ ሁሉ ገምቷል ለካ!»

አዎን፥ ምናልባት ለዓለም ሁሉ ኃጢአት መዘፈቅ ምክንያት ራሳችን ልንሆን እንችላለንና፥ «ለዚህ ሁሉ መመሰቃቀል እኔ ነኝና ምክንያቱ ይቅር በለኝ!» ብንል ጌታ ይምረናል። እኛንና አገራችንንም ይፈውሳል። ይህንን እንድናደርግ አምላክ ይርዳን። አሜን!

«እርሱም፡- ይህ ታላቅ ማዕበል በእኔ ምክንያት እንዳገኛችሁ አውቃለሁና አንሥታችሁ ወደ ባሕር ጣሉኝ፥ ባሕሩም ጸጥ ይልላችኋል አላቸው።» (ዮናስ 1፡12)

# የአይጥ መርዝ

ሰባኪው «እዚህ ከተሰበሰብነው ውስጥ አንድም ሰው በዚህ ምድር ሲኖር ሀብታም እንጂ ድሀ እንዲሆን አይፈልግም። ከዚህ የተነሣ ሁሉ ሰው ሀብታም ለመሆን ይጥራል። አንዳንዱ ተግቶ ስለማይሠራና ስለማይባረክ ድህነቱን ይዞ ይቀጥላል። አንዳንዱ ደግሞ በተቃራኒው ለሥራ በመትጋትና በንጽሕና ሲመላለስ ያለው እየተባረከ፥ ካለው ላይ እየጨመረ እግዚአብሔር ሀብታም ያደርገዋል። አንዳንዱ ደግሞ ሀብታም ለመሆን ከመጓጓቱ የተነሣ በቀናው መንገድ ሀብታም ለመሆን ባይመቸው በጠማማው መንገድ ሀብታም ለመሆን ይሞክራል። ይህም በጉቦ፥ ፍርድን በማጣመም፥ ነጋዴ ከሆነ በበርበሬ ላይ የሸክላ አፈርን፥ በቅቤ ላይ ሙዝን በመጨመር፥ እነዚህን በመሳሰሉት የሐሰት መንገዶች ነው፤ ይህ ግን ተገቢ አይደለም። እንዲህ በማድረግ የሚመጣ ብልጽግና በአፍንጫችን ይውጣ!» ለሚለው ትምህርት ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንድ ገበሬ ከመድኃኒት ቤት ለራሱ የሚሆን መድኃኒት እና የአይጥ መርዝ ሲገዛ የጤና ባለሙያው እንዳይቀላቀልበት በመፍራት በቀኝ እጁ የራሱን መድኃኒት፥ በግራ እጁ የአይጡን መርዝ አስያዘውና «የእኔ አይጥ፥ እያልክ ወደ ቤትህ ሂድ!» ይለዋል። እርሱም እባክህን ይህስ አይጠፋኝም ብሎ የዶክተሩን ትእዛዝ በትክክል ሳያጤን መንገዱን ሁሉ «የእኔ አይጥ፥ የእኔ አይጥ» እያለ እጁን እያነሣ የንግግር ፍጥነቱን በመጨመር ዶክተሩ እንዳዘዘው ሳይሆን እጁን አዟዟረው፤ በመጨረሻም ቤቱ ሲደርስ ተደበላለቀበትና የአይጡን ለራሱ፥ የራሱን ለአይጥ አድርጎት አረፈው።

ወገኖቼ፥ በሕይወት ጉዞ ላይ የእኛን ሀብትና የከፋውን ድርሻ ካለወቅን ውጤቱ የከፋ ነውና ከቃሉ መመሪያ መውጣት የለብንም። ሀብታምም ድሀም የሚያደርገው እግዚአብሔር ነውና ለመበልጸግ የምናደርገውን የከፋ ፍጥነት የተሞላበት እርምጃ እንድናስወግድ ጌታ ይርዳን። አሜን!

«እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋር ያለ ጥቂት ነገር ሁከት ካለበት ከብዙ መዝገብ ይሻላል።» (ምሳሌ 15፥16)።

# እግዚአብሔር የቱን ያክላል?

ሰባኪው «እግዚአብሔር የተለያዩ የጸጋ ስጦታዎችን ወይም ችሎታዎችን የሰጠን ክብሩን ለእርሱ እንድንሰጥ እንጂ ለእኛ እንድንወስድ አይደለም። እንዲያውም እግዚአብሔር በአገልግሎታችንና በሕይወታችን ሁሉ መሳካትን ሰጥቶ ሲባርከን ወይም ሲያሳድገን እኛነታችንን ደብቀን እርሱን ማሳየት አለብን። ዛሬ ዛሬ ግን በተቃራኒው አንዳንድ አገልጋዮች ከእግዚአብሔር ይልቅ ራሳቸውን ማሳየት ጀምረዋል። ሕዝቡም «እንዴት ዓይነት ሰባኪ ነው ቃሉን ይገልጠዋል፥ እንዴት ዓይነት ዘማሪ ነው ያንቆረቁረዋል።» ብለው እንዲያሞጋግሷቸው በሩን ከፍተዋል። ይህ ግን ለጥፋት እንጂ ለልማት አይደለምና ከእንግዲህ እኛን ሳይሆን በእኛ የሠራውንና የሚሠራውን የጸጋውን ባለቤት እግዚአብሔርን እናሳይ፤ ራሳችንን ግን እንሰውር።» ለሚለው ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ።

ቄሱ «እግዚአብሔር ትልቅ ነው። ከአእምሮአችንም በላይ ነው። እኛም የሰው ልጆች በዚህ በትልቁ ጌታ ታምነንና ተደግፈን ብንኖር የሚያስደንግጠን።» የለም እያሉ ካስተማሩ በኋላ ጉባኤው አልቆ ሲበተን ከጉባኤው መሀል ከእናቱ ጋር ቁጭ ብሎ ሲሰማቸው የነበረው ትንሽ ልጃቸው እንዲህ ሲል ይጠይቃቸዋል፥ «አባባ ቅድም እግዚአብሔር ትልቅ ነው፥ እያልክ ስታስተምር ሰምቻለሁ፥ እስቲ አሳየኝ እግዚአብሔር የቱን ያክላል?» ቄሱም የሚያስረዱበት ቢያጡ ፊት ለፊታቸው ያለውን ረጅምና ትልቅ ሕንፃ እያመለከቱ «እግዚአብሔር ይህን ትልቅ ሕንፃ ያክላል።» ቢሉት ልጁም መለሰና «ይህንን ትልቅ ሕንፃ የሚያክለው እግዚአብሔር በሰው ውስጥ ካደረማ፥ ሰው አይታይም ማለት ነዋ!» ብሎ ደመደመ።

አዎ፥ ትልቁ እግዚአብሔር ብቻ በእኛ ሕይወት ከፍ ብሎ ይታይ፥ እኛ ግን እንሰወር ፤ ይህ እግዚአብሔርን ያስደስተዋልና። ለዚህም ጌታ ይርዳን። አሜን!

«. . . የማንጠቅም ባሪያዎች ነን፥ ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል በሉ።» (ሉቃ. 17፡10)።

# ክፍል አምስት

## እግዚአብሔርን ስለሚያስከብር ሥራ ምን አለበት ባትጮኹብኝ?

ሰባኪው «ሴቶች በቤትም ሆነ በውጭ በትጋትና በታማኝነት እግዚአብሔርንም በመፍራት እንደ እግዚአብሔር ቃል መሥራትና ማገልገል አለባቸው እንጂ ሰነፍ መሆን የለባቸውም።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለአድማጮቻቸው ለማስጨበጥ ፈልገው የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

ከተጋቡ ስድስት ወር አለፉቸው፤ ስድስት ወር ሙሉ ተከታትሏታል። ሁልጊዜ የምትነሣው ሰው ሁሉ ወደ ተግባሩ ከተሰማራ በኋላ አርፍዳ ነው። ጠዋት ጠዋት ቁርስ የምትሠራው እርሷ ሳትሆን እናቱ ናቸው። ይህ ነገር ባልየውን ከበደውና ከእናቱ ጋር ተማከረ። «እማዬ፥ እስቲ ነገ ጠዋት አንቺ ቤቱን ልትጠርጊ ስትነሺ እኔ እጠርጋለሁ ልበልና ሁካታ እንፍጠር፤ ምናልባት በዚህ ጊዜ ሰምታና አፍራ ተነሥታ ሁለታችሁም ተዉት እኔ እጠርጋለሁ ትል ይሆናል» ተባባሉ። ሲነጋም እንደተማከሩት «ልጥረግ፥ አትጠርግም» በማለት ሁካታ ሲፈጥሩ ነቃችና ከራሷ ቀና ብላ አልጋዋ ላይ እንዳለች፥ «ምንአለበት ባትጮኹብኝ? ለምን በተራ በተራ አትሠሩም?» ብላ አምቧረቀችባቸው። የገመቱት ቀርቶ ያልገመቱት ሆነባቸው ይባላል።

«ልባም ሴትን ማን ሊያገኛት ይችላል? ዋጋዋ ከቀይ ዕንቁ እጅግ ይበልጣል።» (ምሳ. 31፡10)።

ወገኖቼ፥ በተሰማራንበት ቦታና ኃላፊነት ሁሉ በትጋት እንድንሠራ ጌታ ይወዳልና ስንፍናንና እንቅልፍን አስወግደን ለቤታችንና ለአገራችን እንድንሮጥ እግዚአብሔር ራሱ በጸጋው ይደግፈን። አሜን!

# የዕለት ጉርሷን አጣች

ሰባኪው «እኛ የዛሬ ነን፥ ለነገ መጨነቅ የለብንም፥ ነገ ለራሱ ይጨነቃልና። ዛሬ ግን ለእኛ ተሰጥቷልና ተግተን መሥራትና ባለን ረክተን መኖር አለብን።» የሚለውን አስፈላጊ ትምህርት ለማስተማር ይህንን ምሳሌ እንደ መግቢያ አድርገው ተናገሩ።

«አንዲት ወጣት፥ በራሷ ላይ በትንሽ ገንቦ ወተት እየተሸከመች ከገጠር ወደ ከተማ በማመላለስ ትሸጥና ራሷንና ቤተሰቧን ታስተዳድር ነበር። አንድ ቀን እንደተለመደው ወደ ከተማ ለመሸጥ በራሷ ተሸክማ ስትሄድ በመንገድ ላይ እንዲህ እያለች ስለ ነገው ማሰብ ጀመረች። ይህንን ወተት እያመላለስኩ እሸጥና ብዙ ገንዘብ አጠራቅሜ ወደ ከተማ እገባለሁ፥ ቤት እሠራለሁ፥ መኪና እገዛለሁ፥ የአንድ ትልቅ ድርጅት ኃላፊም እሆናለሁ። ይታየኛል ጠዋት ወደ ሥራ ስገባ የማስተዳድራቸው ሠራተኞች ሁሉ ዝቅ ብለው ሲሰግዱልኝ ብላ ጎንበስ ስትል የያዘችው ገንቦ ከራስዋ ላይ ወድቆ ተከሰከሰ። በዚያም ቀን ገዝታ የምትመገበውን የዕለት ጉርሷን አጣች።

አዎን፥ ከልክ ባለፈ የነገ እንዲህ እሆናለሁ ምኞትና ከንቱ መጎምጀት ውስጥ ገብተን የዛሬን ኑሮአችንን እንዳናበላሸው ዛሬን በደስታና በእርካታ እንኑረው። አምላክ በጸጋው ይደግፈን። አሜን!

# አጥር ገፊው

ሰባኪው «ማንም ክፉ ቢያደርግባችሁ መልሳችሁ ክፉ አታድርጉ። ይልቁንም በጎ በማድረግ ለእግዚአብሔር አሳልፋችሁ እየሰጣችሁ በቀና መንፈስ ብትመላለሱ እግዚአብሔር በጠላታችሁ ላይ ድል እንድትቀዳጁ በማድረግ ታሪካችሁን ይለውጣል።» የሚለውን ወርቃማና የተባረከ ትምህርት ለማስረዳት የሚከተለውን ምሳሌ ተናገረ።

አንድ አጥር የሚገፋ ጎረቤት ያላቸው አማኝ ሰው ነበሩ። ሰውየው ሥራው የክፍለ አገር ሾፌር ነውና ሁልጊዜ ከስድስት ወራት በኋላ ሲመጣ አጥሩን ይገፋል። አማኙም ይህን ሲያዩ እንዲህ እያሉ ይጸልያሉ፣ «አባክህ ለዚህ ሰውዬ አእምሮ ስጠው! ከዚህ ክፉ ሥራው መልሰው! ከሁሉም በላይ አንተን እንዲያውቅህ እርዳው ይላሉ።» እርሱም ከክፍለ አገር ሲመጣ ሌላ አዲስ አጥር ያጥራል። እንዲህ እያደረገ ወደ አማኙ ቤት ለመግባት የሚቻለው በጎን ሆኖ በጭንቀት በመሄድ ብቻ ሆነ። እርሳቸውም ጸሎታቸውን ቀጠሉ። እግዚአብሔርም አንድ ቀን በዚያ ክፍለ አገር ተገናኘውና ጌታን አወቀው፣ ከክፉ ሥራውም ንስሐ ገባ፣ ወደ አእምሮውም ተመለሰና እንዲህ አለ፣ «ጎረቤቴን በድያለሁ። አሁን ስመለስ አጥሩን ወደ በታው እመልሳለሁ፣ ጎረቤቴንም ይቅርታ እጠይቃለሁ። በመካከልም በር አወጣና ቡና እንጠጣለን።» አለ አደረገውም። ከዚያ ከ5 እና ከ6 ወር በኋላ ክፍለ አገር ሲመጣ ለጎረቤቱ መቶ ኪሎ ጤፍና አንድ ጆንያ ከሰል አምጥቶ በረንዳ ላይ ቁጭ አደረገ። አማኙ ከሥራ ሲመጡ ይህን ባዩ ጊዜ «ጎረቤቴ መጥቷል፣ ይኸው ምልክቱ፣ ጥሩትና ጌታን እናመስግን» አሉ። ድሮ ጎረቤታቸው መምጣቱ የሚታወቀው አጥር በመግፋቱ ነበር! አሁን ግን በተቃራኒው። አዎ፣ እግዚአብሔር ታሪክ ይለውጣል።

«ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ! በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ። (ሮሜ 12፥17)።

አዎ፣ በቀል የእኔ ነው እኔ ብድራትን እመልሳለሁ ብሏልና ጌታ! በሚያልፈውና በሚጠፋው ዓለም ሳንወሰድ ክፉውን በመልካም እያሸነፍን ለጌታ ክብር እንድናልፍ እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን!

## ዶክተሩ በተወለዱ በአራት ዓመታቸው ሞቱ

ሰባኪው «እግዚአብሔር በዚህ ተዳደር፥ ይህን እስከ ዕድሜህ መጨረሻ ድረስ ሥራው ብሎ በሰጠን በማንኛውም የሥራ መስክ ከልባችን ተግተንና የምንችለውን ሁሉ አድርገን አንድ ቁም ነገር ሠርተን ማለፍ አለብን።» ለሚለው ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ እንደሚከተለው ተጠቀሙ።

«አንድ ሰው ውጭ አገር ሄዶ ከተማውን እየተዘዋወረ ሲጎበኝ ድንገት በተለያዩ የእምነ በረዶች ሐውልት የታነጹ የመቃብር ስፍራዎችን ይመለከታል። ወደ ግቢ ውስጥም ገብቶ ጉብኝት ሲያደርግ በየሐውልቱ ላይ ባለው የሟች ፎቶግራፍ ግርጌ የሚያነበው ነገር ገረመው። ዶክተሩ እከሌ በተወለዱ በአራት ዓመታቸው ሞቱ። ኢንጂነር እከሌ በተወለዱ በ አምስት ዓመታቸው ሞቱ።» በዚህ ጊዜ እዚያው አካባቢው ያለውን የአገሩን ተወላጅ ይጠይቃል። «እንዴት ነው ይህ ነገር የዚህ አገር ሰው ሳይወለድ በፊት ነው እንዴ የሚማረው?» ብሎ በጠየቀ ጊዜ፥ «አይደለም እዚህ አገር ሰው ሲሞት መቃብሩ ላይ የሚጻፍለት በምድር ላይ የኖረበት ዘመኑ ሁሉ ሳይሆን፥ በሙያው ለአገሪቱ ቁም ነገር የሠራበት ብቻ ነው። ለምሳሌ፥ እኚህ ፕሮፌሰር ሰባት ዓመት፥ ዶክተሩና ኢንጂነሩ ደግሞ አራትና አምስት ዓመት ነው ያገለገሉት።» ቢለው። አሰብ አደረገና «ታዲያ አሁን እኔ ብሞት ምን ተብሎ ነው የሚጻፍልኝ?» አለ። «ለአገርዎት ምንም ቁም ነገር አልሠሩም ወይ?» አለው። «ምንም አልሠራሁም» አለው። «የእርስዎ ቀላል ነው፥ አቶ እከሌ ወዲያው እንደተወለዱ ወዲያው ሞቱ ይባልልዎታል» አለው።

«. . . መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ» (2ኛ ተሰ. 3፥13)።

ወገኖቼ፥ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና አገራችንን የሚጠቅም አንድ ቁም ነገር በተሰማራንበት ሥራ ሁሉ ያለ ስንፍና በትጋት ሠርተን አበርክተን እንድናልፍ ጌታ ይርዳን። አሜን!

# ይፍቱ ሥራ

ሰባኪው «እግዚአብሔር የሰጠንን ጊዜ እርሱን ደስ በሚያሰኝና አገርን በሚያለማ ሥራ ላይ እናውለው እንጂ በየመሥሪያ ቤቱና በየመንደሩ እየዞርን አሉባልታ ወሬ ማውራት የለብንም፤ አልተፈቀደልንምና።» ለሚለው ዋና ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ በመጠቀም አድማጮቻቸውን አስገነዘቡ።

«በስድስት ወርና በሰባት ወር አንድ ጊዜ ወደ ቤቱ የሚመጣ የከፍለ አገር ሾፌርነት ሥራ ያለው አማኝ ሰው ነበር፤ በሚመጣበትም ጊዜ ብዙ ቀን ቤት ስለማይታይ አንድና ሁለት ቀን አድሮ ስለሚሄድ፥ አንዳንዴም ከዓመት በላይ ይጠፋ ነበር። በዚህ መካከል ታዲያ ሚስቱ አርግዛ ጎረቤቶች ተመለከቱና ከባሏ ውጭ ነው ያረገዘችው እያሉ የቡና መጠጫ አደረጓት። እርሷ ግን ያረገዘችው ከትክክለኛ ባለቤቷ ነበር። ይህንን ወሬ በሰማች ጊዜ አዘነች፤ ባለቤቷም ሲመጣ አጫወተችው፤ እርሱም ሚስቱን «እኔና አንቺ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ነውና የተሳሰርነው አይዞሽ አትጨነቂ! ግን ለእነዚህ ለወረኞቹ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የምንወልደው ልጅ ወንድም ሆነ ሴት ስሙን «ይፍቱ ሥራ» ብዬ ዋለሁ። የማይሆን ወሬ እያወሩ ሥራ ከሚፈቱ ሥራቸውን ብቻ ሠርተው ቤተሰቦቻቸውን በደህና ቢመሩ ይሻላቸው ነበር በማለት።»

«ሥራ ከቶ ሳይሠሩ፥ በሰው ነገር እየገቡ፥ ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናል።» (2ኛ ተሰ. 3፡11)።

አዎ፥ ወሬ፥ ሐሜትና አሉባልታ እነዚህ ሁሉ አያሳድጉም። የሚያኮራና የሚያሳድግ ክቡር የሆነው ነገር ሥራ ነውና ጊዜአችንን ለቁም ነገር እንድናውለው ጌታ ኢየሱስ በጸጋው ይደግፈን። አሜን!

# ዝጊው ስልሽ፥ ዝጋው ስልህ!

ሰባኪው «እርስ በርሳችን በመተባበር፥ በመከባበርና በመተሳሰብ እንድንኖር እንጂ እንድንፎካከርና ሥራን እንድንበድል አልተጠራንም። ስለዚህ በቀረልን ዘመን እግዚአብሔር በሰጠን አቅም ያለ ፉክክርና ስንፍና ተግባራችንን ልንወጣ ይገባል። የሚለውን ጤናማ ትምህርታቸውን ለማስገንዘብ ይህንን ቀጣይ ምሳሌ አቀረቡ።

«አንድም ቀን አንዳቸው ለአንዳቸው ሳይታዘዙ በፉክክርና በንትርክ የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ። እና አንድ ቀንም እንደተለመደው ባል ከሥራ ማታ ሲመጣ በሩን ሳይዘጋው ገባ። ሚስትም፥ በሩን ዘግተህ ግባ እንጂ ብትለው አንቺ ተነሥተሽ ዝጊው፥ እኔ ደክሞኛልና እንደገና አልመለሰም» አለ። እርሷም፥ «በኋላ የመጣኸው አንተ ዝጋ እንጂ እኔስ አልዘጋም!» በማለት ከሁለቱ ፉክክር የተነሣ በሩ ሳይዘጋ ቀረና ሌሊት ቆንጨራ የታጠቁ ወንበዴዎች ዘው ብለው ገብተው የተኙትን ባልና ሚስት ቀስቅሰው በጣም ስለ ራባቸውና የተልባ ወጥም ስላማራቸው ተልባ አዘጋጅተው እንዲሰጧቸው ጠየቁ። ባልና ሚስትም ተልባ ቆልተው ሲወቅጡ ዘነዘናውን በየተራ እያነሡ ሲጥሉ እንዲህ ይሉ ነበር፥ «ዝጊው ስልሽ፥ ዝጋው ስልህ፤ ዝጊው ስልሽ፥ ዝጋው ስልህ!»

ቅዱሳን፥ በራሳችን ድካምና ስንፍና ስንት ችግር ደረሰብን? በመፎካከራችንና በመናናቃችን በእኛና በአገራችን ላይ ስንት አላስፈላጊ ሽክምና ድካም አተረፍን? በቀረልን ዘመን ያለ ፉክክርና ስንፍና ሥራችንን በትጋት ሠርተን እኛንና አገራችንን እንድንጠቅም እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን!

«ለሰው የከበረ ሀብት ትጋቱ ነው» (ምሳ. 14፡27)

# የእኛ ኑሮ ተሳትፎ ነው!

ሰባኪው «እግዚአብሔር ኢትዮጵያዊ ሆነን ተወልደን በኢትዮጵያ እንድንኖር ፈቅዷል። ይህ ከሆነ ዘንድ ሁላችንም በውስጧ ሆነን በተማርነው ትምህርትና በችሎታችን እንደ አቅማችን ሁሉ ልናለማት በደስታና በርካታ ልንኖርባት እንጂ የውጭውን ዓለም ብቻ እያደነቅን፥ «ላም አለኝ በሰማይ . . .» በሚል ከንቱ ምኞት ሥራን ሳንሠራ በማጉረምረም ልንኖርባት አይገባም። ደግሞም ዛሬ የሆንነውን የሆንነው በእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና «ኑሮዬ ይበቃኛል» እያልን፥ እግዚአብሔርንም በዚህ እያመሰገንን ብንኖር ራስ እንጂ ጅራት አያደርገንም።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለማስገንዘብ የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«አንድ ሰው ለብዙ ዘመን የተለየው ጓደኛው ከውጭ አገር እንደመጣ ሰማና ቤቱ ጋበዘው። ስለ ውጭው ሀገር ኑሮ ሁኔታ ይጠያይቀው ጀመር። «ውጭ አገር እንዴት ነው?» ከውጭ የመጣውም ሰው የውጭውን ኑሮ እያደነቀ ይነግረዋል። «እባክህ ተወኝ፥ ኑሮ ውጭ አገር ነው። ያሰብከውንና ያለምከውን የምታገኝበት፥ በቀን አምስት ጊዜ የምትበላበት፥ ጥሩ ውኃ የምትጠጣበት፥ ባጠቃላይ ኑሮ አልጋ በአልጋ የሆነበት አገር ውጭ ነው።» ይለዋል። ቀጠለና የአገር ቤቱ ሰው፥ «ከኢትዮጵያ ኑሮ ጋር እንዴት ታስተያየዋለህ?» ይለዋል። በዚህ ጊዜ ራሱን እየነቀነቀ «ፐ ፐ ፐ ፐ ፐ ከኢትዮጵያ ጋር ምንም አይወዳደርም። ቃላትም የለኝ። የእኛ ኑሮ፥ ኑሮ አይደለም፥ ተሳትፎ ነው። ኑሮውን እነርሱ ይኖራሉ፥ እኛ ግን እነርሱን እንተባበራለን።» ብሎት አረፈ።

«ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው።» (1ኛ ጢሞ. 6፡6)።

ወገኖቼ ሆይ፥ የሩቅ ሣር ለምለም መስሎ ይታያልና ያስጎመጃል፤ ከሠራንባትና ካለማናት ኢትዮጵያ መልካም ናት። ወርቁና ብሩ ላይ ቁጭ ብለን እግዚአብሔርን እንዳናማርር ጌታ ይርዳን። አሜን!

## አቶ ቃለ ሕይወት ጥሩ ሰው ነው!

ሰባኪው «እኛ የሰው ልጆች የተፈጠርነው መልካምን ሥራ ለማድረግና በመልካም ምስክርነት እግዚአብሔርን እያከበርንና እያስከበርን በወንጌል እንድንኖር ነው።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለማስጨበጥ ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«በአንድ አካባቢ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የውኃ ፕሮጀክት ከመሬት ውስጥ ጉድጓድ እየቆፈረ ውኃ በማውጣት ኅብረተሰቡን ያገለግል ነበር። ታዲያ አንድ ቀን የዚሁ ፕሮጀክት ንብረት የሆነች መኪና ከገጠር ወደ ከተማው ስትመጣ መንገድ ላይ በረሃ ልትወልድ የደረሰች ሴት ገበሬዎች በቃሬዛ ተሸክመዋት ሾፌሩ ያይና የሚሄድበት መንገድ አንድ ዓይነት ስለሆነ በመኪናዋ በመውሰድ ይረዳቸዋል። ሴትየዋም በሰላም ከተማ መጥታ ከተገላገለች በኋላ እንዲህ ብላ ጠየቀች– «በረሃ ላይ ሳልበላሽ ደርሶ የእኔንም የልጄንም ሕይወት ያተረፈ ያ ሰው ስሙ ማን ነው?» ብላ ስትጠይቅ፥ ገበሬዎቹ መኪናውን እንጂ ሾፌሩን አያውቁትምና «ስሙ ቃለ ሕይወት ነው» ይሏታል። በዚህ ጊዜ «የልጄን ስም ቃለ ሕይወት ብዬ ሰይሜአለሁ» ትላለች። ይህ ዝና በአገሩ ሁሉ ላይ ይወጣል። በሌላ ጊዜ የቃለ ሕይወት የውኃ ፕሮጀክት ሥራውን ወደ ሌላ ወረዳ ማስፋፋት ፈለገና መስተዳደሩን ፈቃድ ሲጠይቅ ሕዝቡንም እንሰብስብና የሕዝቡን ፈቃደኝነት አይተን እንፈቅድላችኋለን አሏቸው። ሕዝቡን ሰብስበው፥ «በዚህ ወረዳ ቃለ ሕይወት የውኃ ጉድጓድ ሊቆፍርላችሁ ይፈልጋልና ፈቃደኛ ናችሁ ወይ?» ብለው ሲጠይቁ ሾፌሩ ያደረገው መልካም ሥራ ወሬው ተዛምቶ ነበርና ሁሉም በአንድነት፥ «ፈቃደኛ ነን» አሉ። በዚህ ጊዜ የመስተዳድሩ ኃላፊዎች «ልብ በሉ፥ ፈቃደኛ ነን ስትሉ በደንብ አስቡበት! ቃለ ሕይወት ውኃ ብቻ ሳይሆን ሃይማኖትንም ጨምሮ ነው የሚያስፋፋው» ሲሉ! አንድ ሽማግሌ ተነሡና «እንኳን ውኃና ሃይማኖቱን የፈለገውን ያድርግ አቶ ቃለ ሕይወት ጥሩ ሰው ነው።» ብለው ተናገሩ።

መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።» (ማቴ. 5፡16)።

አዎ፥ ዛሬ ከቃላችን ይልቅ ተግባራችን ሊጮኽ ይገባል። በመልካም ምስክርነት እየተመላለስን ሰዎችን ሁሉ ወደ መልካሙና አዳኙ ጌታ እንድንማርክ ራሱ ጌታ ይርዳን። አሜን!

## ክፉ ለራሱ፥ ደግ ለራሱ

ሰባኪው «ሰው የሚያጭደው የዘራውን ዘር ነው። ደግ ነገር አድርገን ቢሆን፥ ደግ ነገር ይሆንልናል፤ ክፉ ነገር አድርገን ቢሆን፥ ክፉ ነገር ይሆንብናል። ደግሞ እኮ እግዚአብሔር እኛን የፈጠረን ክፉ ሥራን ትተን መልካሙን ሥራ እንድናደርግ ነው፤ በዚህ ምድር ላይ በምንኖርበት ዘመን ሁሉ ደግ ሥራን ለማድረግ አንታክት። ሰዎች ወድቀው የሚሞቱበትን ጠላት የቆፈረውን ጉድጓድ እንድፈን እንጂ፤ ጠላትን በመተባበር ለክፉት ጉድጓድ ብንቆፍር የሚገባበት አይታወቅምና እንጠንቀቅ፤ ተመልሶም ክፉ ሥራችን እኛን ሊጎዳን ይችላል።» ለሚለው ትምህርታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተናገሩ።

«በድሮ ጊዜ አንድ ለማኝ ነበር፤ በየመንደሩ ለምኖ ቁራሽ ሲሰጠው «እግዚአብሔር ይስጥልኝ» በሚለው ምርቃት ፈንታ «ክፉ ለራሱ፥ ደግ ለራሱ ብሎ ነበር የሚሄደው። በየሰፈሩ የሚታወቀውም በዚህ አባባሉ ነበር። ልጆችም መንገድ ላይ ሲያገኙት፥ «አባባ ክፉ ለራሱ፥ ደግ ለራሱ!» ብለው ነበር የሚጠሩት። እና አንድ ቀን አንድ ሀብታም ሴት «ይኸ ለማኝ ክፉ ለራሱ፥ ደግ ለራሱ» የሚለው እኔን በአሽሙር ክፉ ነሽ ማለቱ አይደለም፥ ቆይ እስከ ወዲያኛው እሠራለታለሁ» አለች። አንድ ቀን ቤቷ በር ላይ ቆሞ ሲለምን በቁራሹ እንጀራ ላይ ወጥ በመርዝ አድርጋ ሰጠችው። እርሱም፥ «የሀብታም እንጀራ ስለሆነ ለብቻ ይሁን» ብሎ ከሌላው እንጀራ ጋር ሳይቀላቅል ለብቻ ለይቶ አስቀመጠና፥ «ደግ ለራሱ፥ ክፉ ለራሱ» ብሏት ሄደ። እርሷም፥ በልቧ «ይህ የመጨረሻ ቃልህ ይሆናል፥ ሠርቼልሃለሁ።» ብላ ወደ ቤቷ ገባች። በመንገድ ላይ የእርሷው ልጆች ከትምህርት ቤት ሲመጡ ለማኙን ያገኙትና «አበባ ክፉ ለራሱ፥ ደግ ለራሱ፥ ርቦናል እስቲ የምንበላው ስጡን» ይሏቸዋል። በዚህ ጊዜ «ራባችሁ? ኑ እሺ እንደውም የራሳችሁ እናት የሰጠችኝን ምግብ ይኸው ለብቻ አስቀምጬዋለሁ፥ እንኩ ብሉ» ይልና ይሰጣቸዋል። ሁሉም መርዛሙን ምግብ ከበሉ በኋላ ያልቃሉ። ለማኙም ተይዘው ነገሩ ሲጣራ፥ እናትየዋ የጉዳዩ ባለቤት ሆና ትገኛለች። በተሰበሰበውም ሕዝብ ሁሉ ፊት «ልጆቼን በመርዝ በመግደል ራሴን በራሴ የበላሁት እኔ ነኝ፤ እርሳቸውን ተዉአቸው፤ ሁልጊዜ ክፉ ለራሱ፥ ደግ ለራሱ እንደሚሉት እርሳቸው ደግ፥ እኔ ክፉ ነኝ።» ብላ ተናገረች።

አዎ የእግዚአብሔር ልጆች፥ ምንጊዜም ቢሆን ክፉ ሥራ ክፉ ነው፥ ደግም ሥራ ደግ ነው። «ሰው የዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳል ባንዝል በጊዜው እናጭዳለንና። ስለዚህ በዚች በቀረችልን ትንሿ ዘመናችን ደግ ሥራን ብቻ አድርገን እንድናልፍ ጌታ ይርዳን። አሜን!

«. . . መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት።» (ገላ. 6፡8–9)

## የታረደው በግ

ሰባኪው ፈሪሀ እግዚአብሔር አለን፥ ወይም በእውነት ክርስቲያኖች ነን ለሚሉት ሰዎች ሁሉ «ሁላችንም በክርስቶስ አንድ አካል ነን፥ በመካከላችን ልዩነት የለም» የሚለውን ትምህርት በምሳሌ ለማስጨበጥ ሲሉ ይህንን ምሳሌ ተናገሩ።

«አንድ ሽማግሌ ነበሩ፤ እና ጌታን የሚያመልኩት በየአብያተ ክርስቲያናቱ እየዞሩ ነበር። በተከታታይ አባል በሆኑበት ቤተ ክርስቲያን አለመምጣታቸው ትክክል እንዳልሆነ ያሳሰበው አገልጋይ እንዲህ ሲል አናገራቸው። «እርስዎ አርፈው አንድ ቤተ ክርስቲያን የማያመልኩት ለምንድን ነው? አንዱ ቃለ ሕይወት፥ አንዱ ገነት፥ አንዱ ሙሉ ወንጌል፥ አንዱ አዲስ ኪዳን፥ አንዱ ሌላ ቤተ ክርስቲያን የሚዞሩት ለምንድን ነው?» ቢላቸው፥ ሽማግሌው እንዲህ ሲሉ መለሱ፥ «አይ ልጄ፥ ሉካንዳ ቤቶች በዙ እንጂ የታረደው በግ አንድ ነው።» እንዳልከው ግን በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ሆኖ መመገብ ለእኔም ለጤናዬ ጥሩ ነውና ግሣጼህን ተቀብዬዋለሁ አሉት።

«እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፥ እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን።» (ሮሜ 12:5)

አዎ፥ ስለ በደላችንና ኃጢአታችን በቀራንዮ መስቀል ላይ ሞቶ ከሞትም ተነሥቶ፥ ከሞት ያዳነን ጌታ ክርስቶስ አንድ ነውና እኛም በአንድነትና በኅብረት ልዩነት ሳናደርግ ወንጌሉን እንድንናገር እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን።

# ክፍል ስድስት

## ስለ እግዚአብሔር ተስፋ

## አቤት! የገና አባት ጺም

ሰባኪው «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል ስናከብር ትኩረታችንንና አሳባችን በሚበላውና በሚጠጣው፥ በሚለበሰውና በሚብለጨለጨው ላይ ሳይሆን፥ የሰው ልጅን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ ከሰማይ ሰማያት ወርዶ፥ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፥ ለዓለም መድኃኒት ወደ ሆነው ወደ መድኃኒዓለም ይሁን። ሌሎች ነገሮች ሁሉ የሚያልፉና የሚያለፉ ናቸው» የሚለውን ጤናማ ትምህርታቸውን በአድማጮቻቸው ልብ ለማስረጽ እንዲረዳቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«በገና በዓል ሁለት ወንደላጤ ወጣቶች ጓደኛቸውን ለመጠየቅ ወደ ቤቱ ሄዱ። በቤቱ ውስጥ ተቀምጠው ሳሉ የክርስቶስን የልደት በዓል ምክንያት በማድረግ ጓደኛቸው በቤቱ ውስጥ ያደረገው ዝግጅት ቀልባቸውን ወሰደውና ዙሪያ ገባውን ሲያማትሩ ብልጭ ድርግም በማለት የተለያዩ ቀለሞችን የሚያበራውን መብራት የተሸከመ ትልቅ የገና ዛፍ ይመለከታሉ። በላዩ ላይም የተለያዩ ትንንሽ ፖስት ካርዶችና ትልልቅ ሥዕሎችም አሉበት። በቀኝ በኩል አንድ ረጅም ነጭ ጺም ያንዠረገገ ትልቅ ሰው (የገና አባት) በካርቶን ላይ ዓይን በሚስብ ሁኔታ ተቀምጧል፥ በግራ በኩል ደግሞ ማርያምና ዮሴፍ ሕፃኑ ኢየሱስ ደግሞ በግርግም ተኝቶ የሚያሳይ ከፍ ያለ ሥዕልም ይታያል። በዚህ ጊዜ አንደኛው ጓደኛውን በክርኑ ነካ አደረገና፥ «አየኸው የዮሴፍ ልብስ ጥራቱ፥ የማርያም ዓይን ውበቱ፥ አቤት የገና አባት ጺም!» እያለ ሲቀጥል፥ አቋረጠውና በስጨት ባለ ሁኔታ የእኔ ወንድም፥ አትሞኝ ዓይንህን ከእነዚህ ሁሉ ላይ አንሣና ኢየሱስን ተመልከት፤ እርሱንም አድንቅ። እንደ ሰው ራሱን ዝቅ አድርጎ፥ የሰውን ሥጋ ለብሶ፥ በከብቶች በረት ተወልዶ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ያስታረቀ እውነተኛ የገና አባት (የዘላለም አባት) እርሱ ነው።» አለው።

«ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።» (ኢሳ. 9፡6)።

አዎ የተለመደውን የገናን በዓል ስናከብር ለእኛ ለኢትዮጵያውያኖች ትኩረታችን የጊዜውን ደስታ በሚሰጡ ነገሮች ላይ ሳይሆን የሕይወታችን ጌታ በሆነው ክርስቶስ ላይ እንዲሆን እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን!

# ካሮቱና አህያው

ሰባኪው ምንም እንኳን የጊዜው ሁኔታ ከብዶ ቢያጎብጠንም አንወድቅምና ተስፋ አንቁረጥ። እግዚአብሔር አምላካችን በሕይወታችን ላይ የተናገረውን ተስፋ በጊዜውና በሰዓቱ ይፈጽማል እንጂ የሚረሳ ወይም እንደ ሰይጣን የሚያታልል አምላክ አይደለም። ኢያሪኮን ላይጥል ሕዝቡን አያስጮህም፥ ዳዊትን ላይሾመው በበረሃ አያንከራትተውምና» የሚለውን ትምህርቱን በአድማጩ ጆሮና ልብ ለማስረጽ የሚከተለውን ምሳሌ ተናገረ።

«አንድ ብልህ ገበሬ ነበሩ። ብዙ ገበሬዎች ከሚያደርጉት ነገር ሁሉ የተለየ ፈጠራና ችሎታም ነበራቸው። ለምሳሌ ብዙ ገበሬዎች፥ በአህዮቻቸው ከአውድማ እህል ጭነው ወደ ቤት ሲወስዱ አህዮቹ ከብዷቸው ከነጭነቱ መሬት ሲተኙ በዱላ ይደበድቧቸዋል፤ እኚህ ገበሬ ግን አይደበድቡም፤ ገና ማለዳ ከቤታቸው ሲወጡ ለአህያው ማባቢያ የሚሆን ካሮት በኪሳቸው ይዘው ይሄዳሉ። የጫኑት አህያ መሬት ሲተኛ ረጅም እንጨት ከጋማው ጋር ያስሩና ከእንጨቱ ጫፍ ካሮቷን ጨምረው ያስራሉ፤ በዚህ ጊዜ አህያው ካሮቷን ሲያይ ለመብላት ይነሣል፤ ወደ ካሮቷም ይገሰግሳል፥ ካሮቷም ትሄዳለች፥ እርሱም ይሄዳል። በዚህ ሁኔታ በቀላሉ ቤት ይደርሳል። አሁንም ገበሬው ካሮቷን አንሥተው በኪሳቸው ያደርጋሉ፤ አይሰጡትም። ለምን? ሌላ ጊዜ ያታልሉበታልና።» ሰይጣንም እንዲሁ ነው። እሰጥሃለሁ ይላል ግን አያደርገውም።

እኔና እናንተ የምናመልከው አምላክ ግን እንደዚህ ገበሬ አይደለም፤ እሰጣለሁ ወይም አደርጋለሁ ብሎ የተናገረውን ቃል የሚፈጽም አምላክ ነው፤ በእርሱ ዘንድ ውሸት የለም።

«እግዚአብሔር ለሰጠው የተስፋ ቃል ሁሉ አዎን ማለት በእርሱ ነውና፥ (2ኛ ቆሮ. 1፥20)።

አዎ ወገኖቼ፥ ቃሉን ሳይለውጥ የሰጠውን ተስፋ በጊዜው ይፈጽማልና በቀረልን ዘመን ተስፋ ሳንቆርጥ ተስፋችንን በተስፋ እያደስን እንድንኖር ጌታ ይርዳን። አሜን!

# እግዚአብሔር ሆይ፥ ታዘብኩህ

ሰባኪው «ለእኛ የሚያስፈልገንን የሚያውቅ እግዚአብሔር በጊዜውና በሰዓቱ ሊያደርግልን ይችላል። ነገሮች ሁሉ በእኛ ጊዜና ሰዓት ሳይሆኑ ሲቀሩ ተስፋ መቁረጣችንንና በእግዚአብሔር ላይ በማጉረምረም መነሣታችንን ትተን የእግዚአብሔርን ጊዜ በተስፋ ልንጠብቅ ይገባል።» የሚለውን ትምህርታቸውን እንዲጨብጡላቸው ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«ልጅቷ 12ኛ ክፍልን ካጠናቀቀች በኋላ ከ8 ዓመት በላይ ያለ ሥራ ተቀመጠች። ከእርሷ ጋር የጨረሱት ሁሉ ሥራ በመያዛቸው በእግዚአብሔር ላይ «እኔን ለምን ተውከኝ?» በማለት ማጉረምረም ጀመረች። አንድ ጊዜ የ600 ብር ደመወዝ ሥራ መጣና ተወዳደረች፥ ከእርሷ ጋር ግን እንደማይሄድ ስለ ቆረጠች ብዙም ጸሎት አላደረገችም። ሌላ ጊዜ ደግሞ የ300 ብር ሥራ ማስታወቂያ ወጣና ተወዳደረች፤ ወደ ውድድር ቦታው ከመሄዱ በፊት መኝታ ቤቷን ዘጋችና እንዲህ ስትል ጸለየች፥ «ጌታ ሆይ፥ ይህ ሥራ ከእኔ ትምህርት ጋር ይሄዳልና ስጠኝ፥ ካልሰጠኸኝ ግን እታዘብሃለሁ» አለች። ከሳምንት በኋላ ለዚህ ሥራ አለማለፋዋን የሚገልጥ ደብዳቤ በፖስታ ደረሳት። መኝታ ቤቷ ገብታ፥ «እግዚአብሔር ሆይ ታዘብኩህ!» ብላ ጸለየች። እንደገና አሁንም በሌላ ቀን የመጀመሪያው ለ600 ብር የተወዳደረችበት ሥራ ምላሽ በፖስታ ታሽጎ ደረሳት። ደብዳቤው እንዲህ ይላል፥ «ለዚህ ሥራ ብቁ ሆነው ስለተገኙ በዚህ ቀን መጥተው ሥራውን እንዲጀምሩ። በዚህ ጊዜ ወደ መኝታ ቤቷ በሩጫና በደስታ ሄደችና፥ «እግዚአብሔር ሆይ፥ ታዘብከኝ!» ብላ ጸለየች።

አዎ ወገኖቼ፥ እግዚአብሔር የእኛን ነገር በጊዜውና በሰዓቱ ያደርገዋል። በእኛ ጊዜ ግን ሳይሆን ሲቀር ተስፋ ቆርጠን እንዳንወድቅ ጌታ በኃይሉና በችሎታው ይርዳን። አሜን!

«ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም።» (ኤር. 29፥11)።

# መነጽር የተሸከመው ጉንዳን

ሰባኪው «ዛሬ እየሆነብን ያለው ነገር፥ ባይገባንም ጌታ ሳያውቀው በእኛ ላይ የሚሆን ነገር የለምና ከማጉረምረም ይልቅ ለበጎ ነው ብለን ብንቀበል እግዚአብሔር የጸሎታችንን መልስ በአስደናቂ ሁኔታ በጊዜው ይመልስልናል።» የሚለውን ስብከታቸውን ለማስረዳት ይህን ምሳሌ እንደሚከተለው ተናገሩ።

«አምስት ተራራ ከሚወጡት ሰዎች መሀል አንዷ ወጣት ሴት የምትወጣበት ገመድ ዓይኗን ይመታትና ለማየት የሚረዳት ዓይኗ ውስጥ የምታደርገው መነጽር (ኮንታክት ሌንስ) ይወጣና በሮ ሣር ውስጥ ገብቶ ይጠፋል። ለረጅም ጊዜ ብትፈልገውም ስላጣችው ተራራው ጫፍ ላይ ከወጣች በኋላ ከጓደኞቿ ጋር ስለዚህ ጉዳይ ትጸልያለች። ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ሌላው ሁለተኛ ቡድን ተራራውን ሲወጣ አንዱ ወጣት ይደከመውና ተራራው መሀል ላይ ትንሽ ቁጭ ብሎ ወደ መሬት እያየ እረፍት ሲወስድ ድንገት በሣሩ ውስጥ አንድ ጉንዳን የልጅቱን የዓይን ማያ ትንሽ መነጽር (ኮንታክት ሌንስ) ተሸክሞ ሲሄድ ያየዋል። በዚህ ጊዜ በእጁ ያነሣና ከጉንዳኑ አላቆ ተራራው ጫፍ ላይ የጠፋውን ሰው ጠይቆ ለጠፋት ልጅ ይሰጣል። እርሷም «ጌታ ጸሎቴን መለሰ።» ብላ ተደስታ ማታ ለአባቷ ትነግራቸዋለች። አባትዋም ሰዓሊ (አርቲስት) ስለነበሩ የነገረቻቸውን በሥዕል እንዲህ አድርገው አስቀመጡት። አንድ ጉንዳን መነጽር (ኮንታክት ሌንስ) ተሸክሞ ሲሄድ በትልቁ ሳሉና ከሥሩ እንዲህ ብለው ጻፉበት፥ «ለምን እንደተሸከምኩኝ ባላውቅም እሸከመዋለሁ!»

አዎ ወገኖቼ ሆይ፥ ለምን ይህን ቀንበር እንዳሸከመን እኛም ባይገባንም እግዚአብሔር አምላክ ግን ዓላማ አለው፥ ለበጎ ነውና ሳንሰለች እስከሚያሳርፈን ድረስ እንድንሸከም ጌታ ይርዳን። አሜን!

«እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።» (ሮሜ 8፡28)።

# ክፍል ሰባት

## በእግዚአብሔር ስለመታመን

## ቋጥኙን ልቀቅ!

ሰባኪው «ለሰው ልጆች ሁሉ አምነን እንድንድንበት የተሰጠን የእግዚአብሔር ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነውና በእርሱ ብቻ እንመን፤ ሌላ መመኪያና የሕይወት መደገፊያ አይኑረን፤ ለዘላለም አይሆንምና።» የሚለውን ትምህርቱን ለማስጨበጥ የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀመ።

አንድ ሰው በሕልሙ ትልቅና ረጅም ገደል ውስጥ ገብቶ አየ። የገደሉ መሐል ላይ ሆኖ አንድ ቋጥኝ ይዟል። ሰውነቱ ሁሉ ውን ውን እያለ ከላይ ረጅሙን ገደል ወርዷል፤ ከበታች ሌላ ረጅም ገደል ይቀረዋል። መሀል ላይ ሆኖ «ጌታ ሆይ፥ አድነኝ፥ ጠፋሁ፥ እርዳኝ!» እያለ ሲጮህ እግዚአብሔር በገደሉ ጫፍ ላይ ብቅ ብሎ ይመስለዋል፥ «እንዳድንህ ትፈልጋለህ?» ይለዋል። «አዎን እፈልጋለሁ» ይላል። «እንግዲያውስ ቋጥኙን ልቀቅ» ሲለው ደነገጠና «እምቢ አለ»። እንዲያውም እንዲህ ብሎ ጮኸ፥ «ከዚህ የተሻለ አሳብ ያለው ሌላ እግዚአብሔር አለ ወይ?» በኋላ ብንን ሲል በሕልሙ ነው። ወደ ጸሎት ክፍሉ ሄደና ሲጸልይ ከጌታ ጋር የሚያወዳድረው ሌላ የሚመካበት ነገር እንዳለው ገለጠለት። አጎቱ የታወቁ ሀብታም ናቸው፤ የነዳጅ ማደያ ዴፖ አላቸውና ወደ ጌታ ሲጸልይ «ጌታ ሆይ፥ ይህን ይህን ስጠኝ እምቢ ካልከኝ ግን ወደ አጎቴ እሄዳለሁ።» ይል ነበር። ዛሬ ግን ጌታ ከተናገረው በኋላ ግን ሲጸልይ «ጌታ ሆይ፥ ይህን አድርግልኝ፥ እምቢ ካልከኝ ግን ወደ ማን እሄዳለሁ?» ይል ጀመር።

«ወደ ማን እንሄዳለን አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ» (ዮሐ. 6፥68)

አዎ ወገኖቼ፥ ከዘላለም ሞት ወደ ዘላለም ሕይወት የሚያሻግር ጌታ ብቻ ነውና ወደ እርሱ እንምጣ። ለእኛ የሚያስብልን ከእርሱም የተሻለ ሌላ አሳብ ያለው እግዚአብሔር የለምና ከእርሱ ውጭ የምንታመንበትን ሁሉ ትተን ጌታን ብቻ እንድንይዝ እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን!

## *ነፍሴን ለባለቤቱ ላስረክብ!*

ሰባኪው «ሕዝቡን የሚጠብቅ እግዚአብሔር ለሕዝቡ በነፍስም በሥጋም ዋስትና አለው። በዚህ ምድር ስንኖር በእርሱ ታምነን ልንወጣና ልንገባ ይገባል። እንዲህ ከሆነ እግዚአብሔር ከጠላታችን እጅ ይታደገናል፥ ከሞትም አፋፍ ቢሆን እንደ ፈቃዱ ያድነናል።» የሚለውን ትምህርት ለማስረዳት የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀመ።

አንድ ቀን ወንበዴዎች «ይህ በሰፈራችን ያለው አማኝ ሰውዬ ሁልጊዜ ደልቶትና ደስ ብሎት ጥሩ ለብሶ፥ ጥሩ በልቶ የሚኖረው ብዙ ሀብት ቢኖረው ነውና እንዝረፈው» ተባባሉ አንድ ቀንም አማኙ አምሽቶ ሲመጣ አሳቻ ቦታ አስቆሙትና «ያለህን አውጣ» ብለው ገንዘቡንና የለበሰውን ልብስ ሁሉ አስወለቁት፤ መጨረሻ ላይ ሊገድሉት ሲነሡ፥ «ከመግደላችሁ በፊት ነፍሴን ለባለቤቱ ላስረክብ፤ የጸሎት ጊዜ ስጡኝ!» ብሎ ተንበረከከና እጁን ወደ ላይ አድርጎ ሲጸልይ አዩትና ሰዎቹ «ይኽ ሰውዬ በእውነትም ባለቤት ሳይኖረው አይቀርም» አሉና ፈርተው በሩጫ ከአካባቢው ሮጠው ተሰወሩ። እርሱም በጨለማ ራቁቱን ወደ ቤቱ ሄደ። እግዚአብሔርም ከሞት አፋፍ አዳነው።

«እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ ከሚያስደነግጥም ነገር ያድንሃልና።» [መዝ. (91)፡3]።

አዎ፥ በታላቁ እግዚአብሔር ከታመንንና በእርሱ ከተደገፍን እርሱ የነፍሳችንም የሥጋችንም ባለቤት ነው። ከሞትም የሚያድን ጌታ እርሱ ብቻ ነውና ሕይወታችንን ለእርሱ ሰጥተንና በእርሱም ታምነን እንድኖልፍ እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን!

# የሰይጣን ቀንበር

ሰባኪው «ዛሬም እግዚአብሔር «ወደ እኔ ኑ» የሚለው ቃሉ አልታጠፈም። ለደካሞችና ሸክም ለበዛባቸው ሸክማቸውን ሊጋራ የፍቅር ጥሪውን አብዝቷል። በእርሱ አምነን ወደ መንግሥቱ ብንመጣ ሸክማችን ይወገዳል፤ ይህንን ጥሪ ባንቀበል ግን በሸክማችን ላይ ሌላ የማንችለው ሸክም ይጨመርብናል።» ለሚለው ስብከታቸው በዚህ ምሳሌ አድማጮቻቸውን አስገነዘቡ።

«አንድ ተንኮለኛ አህያ ነበረች። ሁልጊዜ ባለቤቷ ጨው ጭኖት ስትሄድ ወንዝ አካባቢ ስትደርስ ትተኛና ትንፈራገጣለች። በዚህ ጊዜ ውኃ ጭነቱ ውስጥ ይገባና ጨው ሟሙቶ ትንሽ ሸክም ይቀልላታል። ሁልጊዜ በተደጋጋሚ ይህንን በምታደርግበት ጊዜ ባለቤቷ ነቃባትና፤ ጨው የሚጭንባት የነበረችውን ይህችን ተንኮለኛ አህያ አሸዋ ጭኖ ያመላልስባት ጀመር። እርስዋም እንደለመደችው ጭነት ይቀልልኛል ብላ ወንዝ ዳር ሄዳ ውኃው ላይ ስትንፈራገጥ ውኃው ወደ አሸዋው ይገባና ከመቅለል ይልቅ በጣም ከብዶ ለመነሣት ያቅታትና በዚያው ትቀራለች።»

አዎ፥ ቀላሉንና የሚጠቅመውን የእግዚአብሔርን ቀንበር አልሸከምም ካልን ሰይጣን የራሱን ቀንበር ያሸክመናልና እንመለስ፤ ለዚህም ደግሞ በምሕረቱ ባለጠጋ የሆነው አምላክ በጸጋው ያግዘን። አሜን!

«እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና።» (ማቴ. 11፥28–29)

# በኢየሱስ ስም አቃጥለኝ

ሰባኪው «እግዚአብሔር የልባችን እንጂ የአፋችን ብቻ አምላክ አይደለም። እርሱ የመነሻ አሳባችንን ያውቃል። በቋንቋችን የገለጽነውን ብቻ ሳይሆን፤ በልባችን ያሰብነውን ያውቃልና የምናደርገው ነገር ከልባችን በእውነትና በእምነት ሊሆን ይገባዋል።» ለሚለው ትምህርታቸው ይህንን ምሳሌ እንደሚከተለው ተናገሩ።

«አንድ አማርኛ አጣርተው መናገር የማይችሉ ግን የስሙትን በማመንና በመተግበር የሚታወቁ የእምነት አባት የሆኑ የኦሮሞ ተወላጅ ነበሩ። እግዚአብሔር በሕይወታቸው ድንቅ ተአምርን ያደርጋል። ዕውሮች ያያሉ፥ በሽተኞች ይፈወሳሉ፤ ግን የአማርኛ ንግግር ችሎታ የላቸውም። ሰይጣንን እንኳ ሲያስወጡ «በኢየሱስ ስም አቃጥለኝ» ብለው ነው የሚገሥጹት። አንዳንድ የአማርኛን ቋንቋ የሚያቀላጥፉ ሰዎች ሲያርሟቸው፥ «አቃጥለኝ ማለት እኮ እኔን ግደለኝ ማለት ነውና ተቃጠል ነው የሚባለው» ሲሏቸው፥ እንዲህ ብለው ይመልሱ ነበር፥ «እባካችሁ ተዉኝ፥ አምላኬ ይገባዋል፤ የልቤን እንጂ የአፌን አያይምና፤ ደግሞ ሰይጣንም ቢሆን ይገባዋል» ይሉ ነበር።

«ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም።» (ዕብ. 11፥6)

ወገኖቼ፥ ዛሬ በብዙ ጥበብ፥ በረቀቀና በተደባለቀ ቋንቋ የሚቀርብ ብዙ ጸሎት አለ። ግን በውስጡ እምነት ስለሌለበት ውጤት የለውም፤ መፈታቱ ቀርቶ መታሠሩ ይበረታል። የእግዚአብሔር ሰዎች ሆይ፥ እግዚአብሔር አምላካችን በውጭ ከምናደርገው ይልቅ በውስጥ የምናምነውን እምነት ያያልና በእምነት እንድንበረታ ጌታ ይርዳን። አሜን!

# ጥቁሯ ዶሮ

ሰባኪው «እኛ የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ውጭ የምንታመንበትን እርግፍ አድርገን ትተን የሰማይና የምድር ጌታ ወደ ሆነው ወደ መድኃኒዓለም ብንመጣና በእርሱ አዳኝነትና ጠባቂነት ብቻ ብንታመን በእኛ ላይ የሰይጣን ኃይልና አሠራር ሁሉ ፈጽሞ ዋጋና ቦታ አይኖረውም፤ ሊሠለጥንብንም አይችልም።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለማስጨበጥ ይህንን ምሳሌ ተናገሩ።

ከእግዚአብሔር ሌላ አዳኝ እንደሌለ በማወቅና በእርሱም በመታመን የሚኖር አንድ ቤተሰብ ነበረ። ሁሉም ደግሞ የተሳካላቸውና የተከናወነላቸው ነበሩ። ይህ ያስቀናቸው ጎረቤቶች እያስጠነቀሉ ሥራ ሥርና የተለያዩ የጥንቆላ ነገሮችን ወደ እነዚህ ሰዎች ግቢ ይወረውራሉ። በተለይ በየዓመት በዓሉ በጥቁር ዶሮ ያስደግሙና በዓሉ አንድ ቀን ሲቀረው ከንሕይወቷ ወደ እዚሁ ቤተሰብ ግቢ ይወረውሯታል። በጌታ ብቻ የሚታመኑት ቤተሰብ አባወራም «ይህችን ዶሮ ያዙልኝ» ይሉና በጌታ ስም ጸለየው ይባርኩና ከንቤተሰባቸው በልተው በዓሉን ያሳልፋሉ። ሁልጊዜ በየዓመት በዓሉ ዶሮ አይገዙም «ዶሮ ከመግዛት ወጪ ያሳረፍከን ጌታ እናመሰግንሃለን» እያሉ ለእግዚአብሔር ምሥጋናቸውን ያቀርቡ ነበር። በቤተሰባቸውም ላይ የሚመጣ ምንም ችግር አልነበረም፤ በአምላካቸው ታምነው ነበርና።»

«በያዕቆብ ላይ አስማት የለም፥ በእስራኤልም ላይ ምዋርት የለም!» (ዘኁ. 23፥23)።

ቅዱሳን፥ በእስራኤል ላይ እኮ ጥንቆላ (ምዋርት) አይሠራም። በእስራኤል አምላክ ታመኑ፥ እርሱ የጠላትን አሳብ እያፈረሰ በትርፍ እንጂ በኪሳራ አያኖረንም። በቀረው ዘመናችን በባለሥልጣኑ ጌታ ላይ ብቻ እንድንታመን አምላክ ይርዳን። አሜን!

## ከመቶ በላይ ቁጥር አለ ወይ?

ሰባኪው «እግዚአብሔር አምላክ የሰውን ልጆች ከዘላለም ሞት አድኖ ወደ ዘላለም ሕይወት ለማስገባት የከፈለው ዋጋ ቀላል አይደለም፤ ይኸውም አንድያና የመጨረሻ የሆነውን የሚወደውን ልጁን በእኛ ፈንታ እንዲሞት አሳልፎ በመስጠት ነው። በዚህ በልጁ (በክርስቶስ) ያመነ የዘላለም ሕይወትም አለው፤ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግሯል፤ በዚህ በልጁ ያላመነ ግን የዘላለም ሕይወት የለውም፤ እሳቱ ወደማይጠፋ ለዘላለም ወደ ሚሠቃይበት ወደ ሲዖል ይገባል። ይህ ከመሆኑ በፊት ዛሬውኑ ንስሐ ገብተን እግዚአብሔር ለእኛ ሲል የከፈለልንን ዋጋ አውቀንና ተገንዝበን ወደ ጌታ ልንመለስ ይገባናል።» የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርታቸውን ለማስጨበጥ ይህንን ምሳሌ እንደሚከተለው ተጠቀሙ።

«አንድ አባት በብዙ ሺህ ብር የገዙአቸውንና የሚመኩባቸውን ከወርቅ የተሠሩ የጥንት የወርቅ ጎራዴዎችና የወርቅ ዋንጫዎች ሲሞቱ ለልጃቸው ያወርሱታል። ልጁም አባቱ ለእነዚህ ዕቃዎች የከፈሉት ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ ስለማያውቅ በራሱ ዋጋ ውድ ነው ብሎ በሚያስበው ዋጋ ማለት መቶ መቶ ብር ሁሉንም ሸጣቸው። በምን ያህል እንደሸጠ አንድ ቀን ለአጎቱ ሲነግረው፥ አጎቱ በጣም ያዝንና ልክ አይደለህም፤ እንዴት መቶ መቶ ብር ትሸጣቸዋለህን ለምን ከመቶ በላይ አልሸጥካቸውም?» ቢለው። ልጁም በየዋህነት እንዲህ ሲል ጠየቀ «አጎቴ ለመሆኑ ከመቶ በላይ ቁጥር አለ ወይ?» ብሎ አረፈ።

አዎ ወገኖቼ ሆይ፥ ጌታ ለእኛ ሲል ተሠቃይቶ ራሱንም ዝቅ አድርጎ እንደ ባሪያ ሆኖ በእርግማናችን ገብቶ ከእርግማን አድኖናል፤ የተከፈለልንን የሕይወት ዋጋ አውቀንና ተገንዝበን ወደ ጌታ እንድንመለስ እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን!

«በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን» (ገላ. 3፡13)።

## *ለሕይወትህ ዋጋ ስጥ!*

ሰባኪው «የሰው ልጅ ከዘላለም እሳት የሚድነው እግዚአብሔር የሚለውን በመስማት፥ በማመንና በመተግበር ነው። የእግዚአብሔር ቃል በዮሐንስ ወንጌል 14፡6 ላይ እንዲህ ይላል። «ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።» አዎ ይህን ቃል አምነን በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ካልተመለስን ምንም እናድርግ፥ ማንም እንሁን ከገሃነመ እሳት አናመልጥም። አንዳንድ ሰዎች «እኔ ሰውን ቀና ብዬ ስለማላይ፥ የሰው ገንዘብ ስለማልፈልግ፥ ቀኜን ሲመቱኝ ግራዬን ስለምሰጥ፥ ስእለቴን በጊዜው ስለምፈጽም፥ መልካምን ሥራ ሁሉ ስለምሠራ መንግሥተ ሰማይ እንጂ ገሃነም አልገባም» ብለው ያምናሉ። ይህ ግን ከቃሉ የራቀ ነው። እኛ ከገሃነመ እሳት የምንድነው ከላይ በዘረዘርናቸው በእኛ ሥራዎች ሳይሆን በክርስቶስ የመስቀል ሥራ ብቻ ነው።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለአድማጮቻቸው ለማስገንዘብ ቀጣዩን ምሳሌ አቀረቡ።

«አንድ አማኝ ሰው ስለ ክርስቶስ አዳኝነት ለአንድ ወጣት ልጅ ሊነግረው ይፈልግና «ሕይወት እንዴት ነው?» ብሎ ይጠይቀዋል። እርሱም «ቆንጆ ነው፥ ሬድዮና ቴሌቪዥን በሚለን መሠረት ሕይወቴን እየመራሁ እገኛለሁ» ይለዋል። አማኙ «ምንድን ነው የሚለው?» ይለዋል። «ለሕይወትህ ዋጋ ስጥ፥ አንድ ለአንድ ተወሰኑ፥ ማምለጥ ነው የሚያወጣው።» አማኙም «ጥሩ ነው በዚህ ምድር ላይ ስንኖር እነዚህን ሁሉ ማድረግ አለብን። ግን በክርስቶስ አዳኝነት በግልህ አምነህ ቃሉን ካልተቀበልክ እነዚህ የምትላቸው ሁሉ መንግሥተ ሰማያት ሊያስገቡህ አይችሉም። ለሥጋህ ያሰብከውን ያህል ለነፍስህ ደግሞ በበለጠ ማሰብ አለብህ። ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚያደርስ ብቸኛው መንገድ ክርስቶስ ብቻ ነው።» ይለዋል። በዚህ ጊዜ ይህ ወጣት ኃጢአቱ ይጸጸተውና ለቃሉ ልቦናውን ከፍቶ ንስሐ በመግባት የጌታን አዳኝነት ተቀብሎ አመነ።»

አዎ ወገኖቼ ሆይ፥ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ በዚህ ክፉና አስጨናቂ ዘመን ሞት ሳይቀድመን ቀድመነው ወደ ጌታ በመምጣትና በእርሱ በመታመን ለሕይወታችን ዋጋ መስጠት እንድንችል ጌታ ይርዳን። አሜን!

# ክፍል ስምንት

## ለእግዚአብሔር ስለ መስጠት

## የእግዚአብሔር ጥጃ ሞተችበት

ሰባኪው «ያለን ሁሉ የእግዚአብሔር ነው። ከእኛ የሆነ ምንም የለም። ስለዚህ በደስታና በውዴታ እርሱ የሰጠንን መልሰን ለእርሱ ልንሰጠው ይገባል። ለአምላክ ለመስጠት ፍጹም መሰሰት የለብንም።» የሚለውን ትምህርቱን በዚህ ምሳሌ ያስረዳ ጀመር።

አንድ ገበሬ «መቼ ነው ላሜ ወልዳ ወተት የምንጠጣው፥ ባለቤቴ ቅቤ ተቀብታ የምትወዛው፥ ልጆቼስ፥ እርጎ፥ አጓትና አሬራ ጠጥተው የሚረኩት» እያለ የላሟን መውለድ ሲጠባበቅ እንዳለውም ላሟ በጊዜው ነጭና ጥቁር መንታ ጥጆች ትወልዳለች። ይህን ደስታውን ሮጦ ለባለቤቱ ነገራት። እርሷም «እግዚአብሔር ይመስገን ብላ አንዷን ጥጃ ለጌታ እንስጥ» አለችው። እርሱም «ለምን ሌላ ጊዜ ሦስት ስትወልድ አንሰጥም?» አለ። ሚስት እንቢ በማለት አስገደደችውና እሺ አለ። «ለይተን እንስጥ ነጩአን ወይም ጥቁሯን የትኛዋን እንስጥ?» አለችው። እርሱም «ጌታ ደስ ያለውን ቀለም ይውሰድ እኛ ምን አገባን» አላት። እሺ ተባብለው ሦስት ወራት ካለፉ በኋላ ጥቁሯ ጥጃ ትሞታለች። ከሜዳ እየሮጠ መጥቶ ለባለቤቱ «የእግዚአብሔር ጥጃ ሞተችበት!» ብሎ ነገራት።

«እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ፥ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም» (2ኛ ቆሮ. 9፡7)።

አዎ፥ እኛ ወደዚህ ምድር ስንመጣ ያመጣነው ምንም ነገር የለም። ግን ሁሉን ከጌታ ተቀበልን። ሁሉ ከእርሱ ነው፥ ሁሉ በእርሱ ነው፥ ሁሉ ደግሞ ለእርሱ ክብር ይሁን። እግዚአብሔር የመነሻ አሳብን ይመዝናልና ሁሉንም ለጌታ በደስታ እንድንሰጠው ራሱ እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን!

# አባ ጎሴና አቡዬ

ሰባኪው «ሰው የሚባረከው ካለው ላይ ለእግዚአብሔር ሲሰጥ ነው። ደግሞ ቃሉም «ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ የተባረከ ነው» ይላል። እግዚአብሔር ከሰጠን ላይ መልሰን ለእርሱ ሥራ ማስፋፊያ ሳንሰስት በደስታ ልንሰጥ ይገባናል።» የሚለውን ስብከታቸውን ለአድማጮቻቸው ለማስያዝ ይህን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«ታሪኩ በደቡብ የተፈጸመ ነው። ጊዜው ለታላቁ የእግዚአብሔር ቤት ሥራ እንዲሆን በደስታ ስጦታ የሚደረግበት ታላቅ ኮንፈራንስ የተዘጋጀበት ቀን ነው። ሁሉም ሰው ለአምላኩ ቤት ሥራ በደስታ ለመስጠት እየተዘጋጀ ባለበት ወቅት ሁለት ሰዎች ግን በዚያ ቀን ምንም ለመስጠት አልፈለጉምና የማይሰጡበትን ዘዴ መፈለግ ጀመሩ። እና አንደኛው ሌላውን በመንገድ ላይ ሳሉ እንዲህ ሲል ጠየቀው «ዛሬ በስጦታው ፕሮግራም ላይ የሚሰብኩትና የሚዘምሩት እነማን ናቸው?» «አባ ጎሴና አቡዬ ናቸው።» ሲለው መልሶ እንዲህ አለ፥ «እንግዲያውስ አባጎሴ ከሰበከ አቡዬ ከዘመረ ግቻውን አጥብቀህ ያዝ!) እነዚህ ሁለት ሰዎች አንድ ላይ ተጣምረው ሲያገለግሉ ሰው ነፍስ አይቀርለትም፤ እግዚአብሔር በጣም የሚጠቀምባቸው ሰዎች ናቸው። ሕዝቡም የመጣበትን በቅሎ ሳይቀር ሰጥቶ ነው የሚመለሰውና ስለዚህ በመልእክቱ ተወስደህ ተሳስቶ እጅህ ወደ ኪስህ ሳታስበው እንዳይገባ ግቻውን (ሜዳ ላይ ችፍግ ብሎ የበቀለውን ሣር) ጥብቅ አድርገህ ያዝ!» ብሎ መከረው።

ወገኖቼ፥ ለእግዚአብሔር ሰጥቶ ያተረፈና ያደለበ እንጂ የከሰረ የለምና ዛሬም እኛን በዘመናችን እግዚአብሔር ግቻውን ያስለቅቀን። አሜን!

«ስጡ ይሰጣችሁማል. . . » (ሉቃስ 6፡38)

## የመባው ዕቃ

ሰባኪው «የእግዚአብሔር ቤት ሥራ የሚሠራው በእግዚአብሔር ሰዎች ገንዘብና ጉልበት ነው። እኛም ያለንን ሳንሰስትና ሳንቆጥብ በደስታ ለእርሱ ቤት ሥራ ብንሰጥ እናተርፋለን እንጂ አንከስርም፥ እንጠቀማለን እንጂ አንጎዳም። ደግሞስ የእግዚአብሔር ገንዘብ እኮ ሕዝቡ ነው፥ እኛ ካልሰጠን ለቤቱ ሥራ ለወንጌል ማስፋፊያ ማን ሊሰጥ ነው? ዛሬ ግን ለእግዚአብሔር መስጠት ምናልባትም እንደ ኪሳራ የተቆጠረበት ዘመን ይመስላል። በቤተ ክርስቲያን ብዙ ሕዝብ እሁድ እሁዱ ይሰበሰባል። የመባ ዕቃ ሲዞር የሚሰበሰበው ገንዘብ ከሰዉ ቁጥር ጋር ሲተያይ የሚያሳፍር ነው። ምክንያቱም እጁን ከሚዘረጋው ይልቅ እጁን አጣጥፎ የሚቀመጠው ብዙ ነውና፤ ይህ ግን የመባረካችን ሳይሆን የማጉደላችን ምልክት ነውና ከሕይወታችን ልናስወግደው ይገባል።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለማስጨበጥ ቀጣዩን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«በአንድ አካባቢ ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት ያሰቡ ሽማግሌዎች ሕዝቡን ሰበሰቡና ዓላማቸውን አስረዱ። ሕዝቡም ለዚህ ሥራ እንዲሰጥ የመባ ዕቃ እንዲዞር አደረጉ። የመባው ዕቃ ዞሮ ዞሮ የቤተ ክርስቲያኒቱ ቄስ ዘንድ ሲደርስ ባዶውን ነው። በጣም ያዘኑት ቄስ ብድግ አሉና ዕቃውን ዘቅዝቀው ለሕዝቡ እያሳዩ፥ «ከእንደዚህ ዓይነት ጉባኤ የመባው ዕቃ በሰላም ስለ ተመለሰ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባዋል።» ብለው ገሠጹ።

ወገኖቼ ሆይ፥ ለሰጠን ለእግዚአብሔር ቤት ሥራ እኛው ካልሰጠን ማን ሊሰጥ ነው? ሕይወቱን ለሰጠን እግዚአብሔር ሕይወታችንንና ያለንን ሁሉ በደስታ እንድንሰጠው ጌታ ይርዳን። አሜን!

## «ዘጠኝ ብር ከስረሃል!»

ሰባኪው ፈሪሃ እግዚአብሔር አለን ወይም በእውነት ክርስቲያኖች ነን ለሚሉት ሰዎች እንዲህ አሉ «ያለን ሁሉ የእግዚአብሔር ነውና ሁሉን ከእርሱ በነፃ ተቀብለናል መልሰን ታዲያ በደስታና በውዴታ ለእግዚአብሔር ከልባችን መስጠት አለብን።» በማለት ለመልእክታቸው የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«አንድ ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መባ ሲሰበሰብ አንድ ብር ለእግዚአብሔር ለመስጠት ፈለገና የአሥር ብር ዝርዝር ከኪሶቹ ፈላልጎ በማጣቱ ተቸገረ። እንዳይተወው ሰዎች አይተውታል፥ እንዳይሰጥ የአሥር ብር ዝርዝር አጥቷል። በዚህ ጊዜ መባ ሰብሳቢዎቹ ሲደርሱበት እንዳለ አሥር ብሩን ሰጠ። ወደ ቤቱ እያዘነ ሄደ። ቤቱም ሲደርስ ባለቤቱ ሁኔታውን አይታ እንዲህ እያለች ትጠይቀው ጀመር «ምን ነው ምን ሆንክ?» ከሰው ጋር ተጣላህ ወይስ ገንዘብ ጠፋብህ?» እርሱም «አይደለም ከሰው ጋር አልተጣላሁም፥ ገንዘብም አልጠፋብኝም፤ ግን በቤተ ክርስቲያን መባ ሲሰበሰብ የአሥር ብር ዝርዝር አጣሁና ሰዎች ይታዘቡኛል ብዬ አንድ ብር መስጠት ሲገባኝ እንዳለ አሥር ብሩን ሰጠሁ» አላት። እርሷም እንደ እግዚአብሔር ቃል መባውን እንዳልሰጠ ገባትና «አይ ባለቤቴ፥ ዝርዝር ብታገኝ ኖሮ አንድ ብር ሰጥተህ ዘጠኝ ብር ልትወስድ ፈልገህ ነበር፤ ነገር ግን ዝርዝር ስላላገኘህና የሰው ይሉኝታ ይዞህ እንዳለ አሥር ብሩን ሰጥተሃል። ነገር ግን ዘጠኝ ብር ከስረሃል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚቀበልህ ያችን በመጀመሪያ በልብህ ያሰብካትን አንድ ብር እንጂ ተቸግረህ የሰጠኸውን ዘጠኝ ብር አይደለም።» ብላው አረፈች።

«እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ፥ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም።» (2ኛ ቆሮ. 9፡7)

አዎ፥ ያለን ሁሉ የእግዚአብሔር ነው፥ ከዚህም በደስታና በውዴታ ለእርሱ ሥራ መስፋፋት እንድንሰጥ እግዚአብሔር ይርዳን አሜን!

# ክፍል ዘጠኝ

## እግዚአብሔርን ስለማገልገል

## ክራባት ታስራለህ

ሰባኪው «እግዚአብሔር በሰጠን የጸጋ ስጦታ በታማኝነት ጌታን እናገልግለው፤ የሌለንን ስጦታ በመፈለግ እንደነእከሌ መሆን እፈልጋለሁ በማለት ሳይሰጠን በእፈልጋለሁ ብቻ መነዳት የከፋ ችግር ውስጥ ስለሚከተን እርሱ በሰጠን ስጦታና ባስቀመጠን ቦታ በታማኝነት ልናገለግለው ይገባል።» በማለት ይህንን ምሳሌ እንደሚከተለው ተናገሩ።

«በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመስተንግዶ የሚያገለግል አንድ ሰው ነበር። ነገር ግን አንድ ቀን እንዲህ ብሎ አሰበ፤ ሰዎችን ጠጋ በል፥ ጠጋ በሉ፥ ቆም በሉ፥ ተነሡ ማለት ሰለቸኝ፤ አሁን እንደ መጋቢው መስበክ እፈልጋለሁ አለና በውሸት «እግዚአብሔር መልእክት ሰጥቶኛል፥ እንድሰብክ ፍቀዱልኝ!» ብሎ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ጠየቀ። እነርሱም ከጥቂት ማመንታት በኋላ ፈቀዱለት። የዛሬ ሦስት ሳምንት ትሰብካለህና ተዘጋጅ።» አሉት። እርሱም ከዚያን ቀን ጀምሮ መጨነቅ ጀመረ፤ ወደ ጓደኞቹም ሄዶ፥ «ስብከት ለመስበክ የሚያስፈልገው ምንድን ነው?» ብሎ ጠየቀ። እነርሱም፥ «ቀላል ነው፥ ሙሉ ልብስ ትለብሳለህ፤ ክራባት ታስራለህ፥ አንድ ጥቅስ ትመርጣለህ፤ ከዚያ በኋላ መድረኩ ላይ ወጥተህ ወደፊትና ወደኋላ እያልክ ያችኑ ጥቅስ ጮክ እያልክ መደጋገም ነው» አሉት። እርሱም ሁሉንም እንዳሉት አደረገ። በቀኑም ዮሐ. ራእይ 3፡11ን መረጠ «እነሆ ቶሎ ብዬ እመጣለሁ»። የሚለውን እንደተመከረው ወደ ኋላ ወደፊት እያለና እየጮኸ ደጋገመው። በመጨረሻም ከኋላ በጣም ስለተንደረደረ በፑልፒቱ አናት ላይ ዘሎ ከፊት ለፊት ከተቀመጡ አንዲት አሮጊት ላይ ተከመረባቸው። በዚህ ጊዜ ደነገጠና ሲትየዋን፥ «ይቅርታ እማማ ጎዳሁዎት» እያለ ሲማጠን፥ እርሳቸውም አቋረጡትና «አይ ልጄ ተወው፥ አንተ አላጠፋህም ያጠፋሁት እኔ ነኝ፤ አንተማ በቶሎ ብዬ እመጣለሁ ብለህ ሦስት ጊዜ አስጠንቅቀኸኝ ነበር፤ ያልተዘጋጀሁት እኔ ነኝ» ብለው መለሱለት።

«በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።» (ዘካ. 4፡6)

አዎ። ከጌታ ያልተሰጠ ስጦታ ለጌታ ክብር ማምጣቱ ቀርቶ ውርደትን ያመጣል። ይህ አስተናጋጅ እንኳን ሊሰብክ ሁለተኛ ማስተናገድም አልቻለም–የሠራው የኃይል ሥራ ያሳፍረዋልና። ወገኖቼ፥ እግዚአብሔር ባስቀመጠን ቦታና በሰጠን ጸጋ እርሱን በታማኝነት አገልግለን እንድናንቀላፋ ጌታ ይርዳን። አሜን!

# ምን ነው ምን ነካዎት?

ሰባኪው «እግዚአብሔር እንድናገለግለው መርጦናል፤ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የተለያዩ የጸጋ ስጦታዎችን ሰጥቶናል። በቤቱ እርሱና ሕዝቡን፥ በጽድቅና በእውነት እንድናገለግል እንጂ በዓመፅና በተንኮል፥ በውሸትና ግብዝነት በተሞላበት አገልግሎት ደስ አይለውም። እኛም የቤቱ አገልጋዮች ይህንን አውቀን ለጌታም ሆነ ለራሳችን የምናደርገውን ሁሉ በእውነትና ስለ እውነት ልናደርገው ያስፈልጋል።» የሚለውን ጠንካራ መልእክታቸውን ለመጠቀም ይህንን ምሳሌ ተናገሩ።

«በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች ፈተና በሚወስዱበት ጊዜ ከመካከላቸው አንድ በዕድሜያቸው ተለቅ ያሉ ተማሪ ፈተናው ከበዳቸውና መልሱን ለማግኘት የተማሩበትን ደብተር እያገላበጡ በማየት መልሱን መሥራት ጀመሩ። በዚህ ጊዜ ሁኔታው በጣም የገረመው አስተማሪ ወደ ተማሪው ጠጋ አለና «ምን ነው ምን ነካዎት? ይህ እኮ ፈተና ነው፤ ከደብተር እያዩ መሥራት አይችሉም!» ብሎ ቢጮኽባቸው፥ እርሳቸውም በተራቸው እንዲህ ብለው መለሱ «ለራሴ መሰለህ የምሠራው፤ ለጌታ ቤት እኮ ነው ብለው አረፉ።»

ክፉውን ነገር ተጠየፉት ከበጎ ነገር ጋር ተባበሩ። (ሮሜ 12፡9)

የእግዚአብሔር ልጆች፥ ለእግዚአብሔር ስንሠራ፥ እውነትን በሐሰት ላይ፥ ጽድቅን በዐመፅ ላይ ተጫምተን ይሁን እንጂ፤ ግብዝነት በሞላበት በከንቱ ውዳሴ እንዳይሆን ጌታ ይርዳን። አሜን!

# የመንደር መገለጥ

ሰባኪው «እኛ አገልጋዮች ለሚጠፋ መብል በግብዝነትና በከንቱ ውዳሴ መሥራት የለብንም። «ለሠራተኛ ደመወዙ ይበቃዋል» ያለው ጌታ ያኖረናል። ዛሬ በየመንደሩ መገለጥ አይላችኋለሁ ብለው ጥቂት ሞኝ ሴቶችን እንደሚያታልሉ እንደ አንዳንድ ውሸታሞች፥ ደመናና ነፋስ ሳይኖር ዝናብ ይዘንባል ብለው እንደሚቀላቅሉት አስመሳዮችም መሆን የለብንም።» የሚለውን ግሣጼ አዘል ትምህርታቸውን ለማስጨበጥ ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ።

አንድ በየመንደሩ እየዞረ በመገልጥ አገለግላለሁ የሚል ሰው አንድ ቀን አንድ ምእመን ቤት ይሄዳል። ጊዜው የምሳ ሰዓት እንኳ ባይሆንም ከምሳ ባልተናነሰ ሁኔታ ጥሩ በቆንጆ ቅቤ የተሠራ ክትፎ እስኪጠግብ ድረስ ያበሉታል፥ የሚጠጣውንም ለስላሳ መጠጥ እየደጋገመ ከጠጣና ከበላ በኋላ የግለሰቧ ውለታ በጣም ይከብደዋል። ከዚህም የተነሣ ምን እንደሚያደርግላቸው ሲያስብ በልጅነታቸው ከብት ሲጠብቁ ከእረኛ ጋር ተጣልተው አንድ ዓይናቸው ፈስሶ አሁን በሕክምና ሌላ የማያይ (አርቲፊሻል) ዓይን ተገጥሞላቸው ይመለከታል። በዚህ ጊዜ ወደ እርሳቸው ቀና ብሎ «ወይኔ! በቃ ለዚህ ዓይንሽ መድኃኒት ጠፋ ማለት ነው፤ እኔ እጸልይልሻለሁ» ብሎአቸው አረፈው።

«ለሚጠፋ መብል አትሥሩ» (ዮሐ. 6፡27)

አዎ ወገኖቼ ሆይ፥ ዛሬ ለጊዜው ለመኖር እንድንችል ብለን የማይሆን ተስፋ እንሰጣለን። የተደላደለ ኑሮ ለመኖር የባለጠጎችን ገንዘብ በመንፈሳዊነት አታልለን ለመውሰድ ያልታየንን ታየኝ፥ ያልተገለጠልንን ተገለጠልን ከማለት ጌታ ይጠብቀን። አሜን!

# የተዋሰኩት ነው!

ሰባኪው «የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሁሉ በእውነትና ስለ እውነት እግዚአብሔር አምላካችንን ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ማገልገል አለብን እንጂ በጊዜውና በሚያልፈው ዓለማዊ ጥቅማ ጥቅም ተይዘን በግብዝነት እግዚአብሔርን ማገልገል የለብንም። ዛሬ በየመንደሩም ሆነ በየቤተ ክርስቲያኑ የሚደረጉት ፕሮግራሞች ሁሉ ተገለጠልኝ (ታየኝ) በሚል ቃሉን ባልተከተለና መንፈሳዊ ሚዛናዊነት በጎደለው አካሄድ በመሄድ ላይ ይገኛሉ። ውሸትን ከእውነት፥ ኃጢአትን ከጽድቅ የሚለዩና የሚገልጡ፥ በእውነት እግዚአብሔር የሚጠቀምባቸው የእግዚአብሔር ሰዎች እንዳሉ ሁሉ፤ በአንጻሩ ደግሞ በዝናና በጥቅም ታውረው ሳይታያቸው ታየን፥ ሳይገለጥላቸው ተገለጠልን በሚል መንፈሳዊ የመሰለ ማጭበርበር ውስጥ የገቡ እንዳሉ ማወቅና መጠንቀቅ፤ ከዚህ ተግባራቸውም እንዲመለሱ መገሠጽና እውነትን ማስተማር አለብን።» የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ለማስገንዘብ ይህንን ምሳሌ እንደሚከተለው ተጠቀሙ።

«አንድ ፕሮግራም ላይ የተሰወረውን በመግለጥ አገለግላለሁ የሚል ስጦታው ሳይሰጠው የተሰጠው በማስመሰል የሚያጭበረብር ሰው ነበር። እና አንድ ቀን በጣም ቆንጆና አዲስ ጊታር ይዞ የመጣ ዘማሪ ተመለከተ፥ ጊታሯንም ወደዳት፥ የጊታር ችግር ነበረበትና በጸሎት ፕሮግራሙ መሀል ላይ እንዲህ ሲል ተናገረ፥ «በዚህ ጉባኤ መካከል በጣም ቆንጆ ጊታር የያዘ ሰው አለ። አንተ ሰው የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይህንን ጊታር ስጠው ይልሃል፤» ብሎ ሲናገር፤ ጉባኤውን በዝማሬ ለማገልገል ቆንጆ ጊታር ይዞ የመጣው ወንድም ውሸቱን ከሥጋው እንደተናገረ ገብቶታልና እንዲህ ሲል መለሰለት። «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የተዋሰኩት ነው ይልሃል።» ብሎ አሳረፈው።

«አንዱ ምንም ሳይሆን ምንም የሆነ ቢመስለው ራሱን ያታልላልና» (ገላ. 6፥3)።

አዎ፥ ጌታ ያልገለጠልንን ከመናገር የተገለጠውን ቃል ብቻ እንድንናገር ጌታ ይርዳን። አሜን!

# የጠፋው ፍየል

ሰባኪው የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ሁሉ ሰብስበው እንዲህ አሉ፥ «እኛ አገልጋዮች እግዚአብሔር መድረክ አዘጋጅቶልን (ሰጥቶን) ልናገለግል በምንወጣበት ጊዜ ትኩረታችን የምንሰብከው ጉባኤ አስደሳች ምላሽ (አስከፊ ምላሽ) ሳይሆን እውነተኛ የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል ማስተላለፋችን ላይ መሆን አለበት። የምንሰብከው ጉባኤ ሊስቅ ወይም ሊያለቅስ ይችላል። የጉባኤው ምላሽ እኛን ሊያስከፋን (ሊያስደስተን) ይችላል። የእኛ መሠረት ግን የማይለወጠውን ግን የሚለውጠውን እውነተኛውን ጌታ ሰብኬአለሁ ወይ? የሚለው ብቻ ሊሆን ይገባል።» በማለት ለአድማጮቻቸው ለማስገንዘብ ይህንን ምሳሌ እንደሚከተለው ተጠቀሙ።

«አንድ መጋቢ በስብከት ላይ እያለ ጉባኤውን ሲመለከት ከመሀከል አንዲት ሴት ወደ እርሱ አተኩረው እየተመለከቱ ያለቅሳሉ። እርሱም «እኚህ ሴት እንደዚህ የሚያለቅሱት በመልእክቱ ተነክተው መሆን አለበት። ቆይ ስብከቴን ስጨርስ ለምን እንደሚያለቅሱ እጠይቃቸዋለሁ።» ብሎ ሰብኮ እንደ ጨረሰ ጉባኤው ሲበተን ፈልጎ አገኛቸውና ጠየቃቸው። «እማማ፥ ቅድም እኔ ስሰብክ እንደዚያ ከሰው ሁሉ ተለይተው እኔን እየተመለከቱ ሲያለቅሱ የነበረው በመልእክቱ ተነክተው ነው አይደለም? እስቲ የትኛው ቃል እንደነካዎት ያጫውቱኝ» ቢላቸው እየተገረሙ «አይ ልጄ፥ አንተ እንዳሰብከው በመልእክቱ ተነክቼ ሳይሆን የሚያስለቅሰኝ ረጅሙ ጺምህ ነው። ይህን ጺምህን ሳይ ትላንትና የጠፋው ፍየሌ ትዝ እያለኝ ነው» ብለውት አረፉ።

አዎ ወገኖቼ ሆይ፥ የምናገለግለው ሕዝብ ምንም ይበል ምን፤ እኛ ግን ቃሉን ከመስበክ አንቆጠብ፥ ተስፋም አንቁረጥ ጌታን እያየን የወንጌል ሰባኪነት ሥራችንን እንድናደርግ ጌታ ይርዳን። አሜን!

«. . . የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፥ አገልግሎትህን ፈጽም።» (2ኛ ጢሞ. 4፡5)

# ዝሆን ትልቅ ነው

ሰባኪው «እግዚአብሔር እውነተኛ ነው፤ እኛ የእርሱ ልጆች ደግሞ የእውነት ልጆች ነን፤ ነገር ግን አንዳንድ ያልገባቸው ሰዎች ለእውነት ብቻ መቆም ሲኖርባቸው እነርሱ ግን እንደ ሁኔታው ሲለዋወጡ ይታያሉ። ሲያሻቸው ለእውነት ቆመናል ይላሉ፤ ሲያሻቸው ደግሞ እውነትን ከደው ለውሸት ይቆማሉ፤ ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። ለእውነት ቆሞ ለእውነት የሞተው ሐዋርያው ጳውሎስ በመልእክቱ ላይ ስለ ጴጥሮስ ሲናገር «ፊት ለፊት ገሠጽኩት» ይላል። ዛሬ ሰዎች ፊት ለፊት ከመገሠጽ ይልቅ በጓዳ ማማትን መርጠዋል። ፊት ለፊት ሲያገኙት ለባለጉዳዩ ጥፋቱን በፍቅር ከመንገር ይልቅ በውሸት ከበውት ከበውት ይመለሳሉ። ይህ ትክክል አይደለም።» የሚለውን ስብከታቸውን ለማስያዝ ይህን ምሳሌ ተናገሩ።

«በአንድ አካባቢ የአንድ ባላባት ዝሆኖች የገበሬዎችን ማሳ እየረጋገጡ ቢያስመርሯቸው ገበሬዎች ተሰባሰቡና እነዚህን ዝሆኖች እንዲያጠፉልን ሄደን ባላባቱን ፊት ለፊት እናነጋግር ተባባሉና ወደ ባላባቱ ቤት ሄዱ፤ በራቸውም ላይ ቆመው አስጠሯቸው። ባላባቱም ወፍራም ሰውነታቸውን እያገላበጡ በአሽከሮቻቸው ታጅበው ወጥተው ወደ እነርሱ ሲመጡ ባዩ ጊዜ ሁሉም ገበሬዎች ፈርተው ተርበተበቱ። ባላባቱም «ምን ፈለጋችሁ?» ሲሏቸው በጎርናና ድምፃቸው፤ ገበሬዎቹም የመጡበትን እውነት ትተው ሁሉም በአንድነት «ጌታችን ሆይ፥ እነዚህ ዝሆኖች በጣም ጠቅመውናል፥ ደግሞም ትልልቅ ናቸውና ይጨመሩልን። «ዝሆን ትልቅ ነው፥ ዝሆን ትልቅ ነው» እያሉ መፈክር አሰምተው ተመለሱ።

«የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ።» (2ኛ ጢሞ. 2፥15)

አዎ ወገኖቼ ሆይ፥ ፊት ለፊት እውነትን እውነት፥ ሐሰትንም ሐሰት በማለት የምንናገር የማናሳፍር ሠራተኞች እንድንሆን ጌታ ይርዳን። አሜን!

# ሰውም አይደለሁም

ሰባኪው «እኛ አገልጋዮች የአገልግሎት መድረክ የሰጠንን ጌታ ስናገለግል በብዙ ፍርሃትና በብዙ መንቀጥቀጥ እግዚአብሔርንና ሕዝቡን ፈርተንና አክብረን መሆን አለበት እንጂ፥ ዝም ብለን በልምድና በድፍረት ያለ ጸሎትና ዝግጅት መቆም የለብንም። እኛ እኮ በቅዱሱ በእግዚአብሔርና በቅዱሳን ሕዝቦች መካከል የምንቆም የዕለቱ የበረከት ማስተላለፊያ መሣሪያዎች (ቧንቧዎች) ነን። ስለዚህ ለአነጋገራችንም ሆነ ለአለባበሳችን ጥንቃቄ አድርገን፥ ተዘጋጅተንና ጸልየን መቆም አለብን እንጂ፥ የፈለግነውን ዓይነት የፋሽን ልብስ ለብሰን፥ የመጣልንን ሁሉ እየዘላበድን በመድረክ ላይ መቆም የለብንም። ይህንን መድረክ እኮ አባቶቻችን ብዙ ደም አፍስሰው ነው ለእኛ ያስረከቡን።» የሚለውን ጤናማ ትምህርታቸውን ለማስገንዘብ ይህንን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«አንድ ፕሮግራም መሪ ቆሞ «ዝንጀሮ አይደለሁም» የሚለውን በጊዜው ብዙዎቻችን የተጽናናንበትንና የተፈወስንበትን ዝማሬ ሲያዘምር እያለዋወጠ ማዘመር ፈለገና እንስሳትን ሁሉ መደርደር ጀመረ። ዝንጀሮ አይደለሁም፥ ጦጣ አይደለሁም፥ ሽኮኮ አይደለሁም፥ ከርከሮ አይደለሁም፥ እባብ አይደለሁም፥ ጉርጥ አይደለሁም፥ ነብር፥ አንበሳ፥ ተኩላ፥ ዝሆን፥ ትንኝ፥ ቅማል፥ ቁንጫ፥ ትኋን አይደለሁም እያለ ሲቀጥል ለጊዜው የእንስሳቱ ስም ሲያልቅበት ሳያስበው ሰውም አይደለሁም!» ብሎ አረፈው።

አገልጋዮች፥ አንሳት፥ እኛ ሰዎች ነን! ለዚያውም የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለብን የተከበርን ሰዎች ነን። ነገር ግን ያለ መዘጋጀት፥ ያለ መጸለይና በድፍረት በመድረክ ላይ በልምድ መቆም ወደ ስሕተት ይመራል። ቀሪውን ዘመናችንን በትጋት፥ በጸሎትና በብዙ ፍርሃት ጌታንና ሕዝቡን ፈርተን አክብረን እንድናገለግል ጌታ ይርዳን። አሜን!

## አራርቆ መውለድ

ሰባኪው «እኛ ሰባኪዎች ወይም አስተማሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል ስናስተምር ግልጽና አሻሚ ባልሆነ አቀራረብ ለአድማጮቻችን ማቅረብ አለብን። ምንም እንኳ ሁሉም ሰው የምንናገረውን ቋንቋ የሚያውቅ ቢሆንም ትርጉም እንደየሰሚው ነው ያልነውን በትክክል እንዲሉና እንዲረዱ ከፈለግን በቀላልና ውስብስብ ባልሆነ አቀራረብ መልእክታችንን ልናቀርብ ይገባናል። ይህ ካልሆነ ግን ከእኛ ጋር ያለው ትክክለኛው የመልእክታችን ትርጉም አድማጮቻችን ጋር ሲደርስ በተቃራኒው ተዛብቶና ተጣሞ እናገኘዋለን። ስለዚህ በጥንቃቄ ያዘጋጀነውን መልእክት መልኩን ሳይለወጥ አድማጮቻችን ልብ ደርሶ ፍሬውን አብረን እንድንበላ በውጤቱም ጌታን እንድናመሰግን መልእክታችንን በሚገባ አቀራረብ ወደ አድማጮቻችን ልናደርስ ይገባል።» የሚለውን ትምህርታቸውን ለማስጨበጥ የሚከተለውን ምሳሌ ተናገሩ።

«በገጠር አካባቢ ለሚገኙ ገበሬዎች ልጆችን አራርቆ ስለመውለድ ትምህርት ተሰጣቸው። ልጅን በላይ በላይ መውለድ መልካም አይደለም፤ ኢኮኖሚ ያናጋል፥ የፈለጉትን በልተውና ለብሰው እንዲያድጉ አያደርግም፥ ቤት የፈለጉትን ካጡና ከተራቡ ጎዳና ይወጣሉ። ስለዚህ ለዚህ ሁሉ መፍትሔው ማሳደግ የምንችለውን ያህል ብቻ እያራራቅን መውለድ ነው።» የሚል ትምህርት ተሰጣቸው። በዚህ ጊዜ አስተማሪዎቹ ትምህርቱ እንደገባቸው አድማጮቻቸውን ሲጠይቋቸው፤ አንድ ገበሬ እጃቸውን አውጥተው እንዲህ ሲሉ መለሱ፥ «ያስተማራችሁን ትምህርት ገብቶናል፤ እኔ እንዷውም ይህ ትምህርት ከመምጣቱ በፊት ፈጣሪም አስመልክቶኝ አራርቄ ነው የወለድኩት። ለምሳሌ ያህል ብጠቅስላችሁ ከአሥሩ ልጆቼ ውስጥ አሁን እኔ ጋ ያሉት ሦስት ብቻ ናቸው። ሌሎቹ አንዱ ጅማ፥ አንዱ ጎንደር፥ አንዱ ወሎ፥ ሁለቱ ወለጋ፥ ሁለቱ መቀሌ በየእናቶቻቸው ቤት ይገኛሉ። አራርቆ መውለድ ማለት ይህ አይደለም።» ብለው አረፉ።

ወገኖቼ፥ የያዝነው መልእክት የምር መልእክት ነው። ይህንንም መልእክት አድማጮቻችን ሁሉ የምር ተቀብለው፥ ተገርመው ተደንቀው ለጌታ መልካም ምላሽ እስኪሰጡ ድረስ በግልጽና በጥበብ እንደ ጌታ ኢየሱስ በብዙ ምሳሌ ማስተማር እንድንችል ራሱ ጌታ ይርዳን። አሜን!

«. . . እስኪገረሙ ድረስ በምኩራባቸው ያስተምራቸው ነበር።» (ማቴ. 13፥14)

# ክፍል አሥር

## እርስ በርስ ይቅር ስለመባባል

## ካቆምንበት እንጀምራለን

ሰባኪው «እርስ በርሳችን በይቅርታ መንፈስ እየተናነጽን ተዋደንና ተከባብረን መኖር እንጂ መኮራረፍ፥ መነካከስና መጠላለት የለብንም። ይህን ማድረግ ለሰይጣን በር ይከፍታል። የጊዜውን ችግር ወዲያው በጊዜ መፍታት አለብን።» የሚለውን ስብከታቸውን ለአድማጮቻቸው ለማስያዝ ይህን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«ባልና ሚስት መረርና ከረር ያለ ጥል እየተጣሉና እየተጨቃጨቁ ሳለ ከውጭ የቤቱ በር ተንኳኳ። ባል ሲከፍት በጣም የሚወዱት የቅርብ ወዳጃቸው ነበርና ሁለቱም ጸባቸውን ደብቀው በፍቅርና በደስታ ተቀበሉት። በተለይ ባል እስቲ ቡና አፍዪ፥ ምሳም አምጪ፥ ከዚህ ስጪው፥ ከዚያም አትርሺው፥ ከዚያም አትንሺው እያለ በደንብ ካስተናገዱት በኋላ እንግዳውም የመጣበትን ጉዳይ ጨርሶ ለመሄድ ሲነሣ ባል ሊሸኘው ወጣ፤ እንደተመለሰም ለሚስቱ እንዲህ አላት፥ «አሁን ካቆምንበት እንጀምራለን።» አዎ ተኮራርፎ ለየብቻ ከመኖር ይልቅ ካቆሙበት ጀምሮ በዛሬው ጀምበር የዛሬውን ችግር በመፍታት በይቅርታ መታደስን የመሰለ ነገር የለም።

«በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት።» (ኤፌ. 4፡27)

አዎን፥ የእግዚአብሔር ቃል «በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ» ነው የሚለው። የእኛ ግን ፀሐይ ገብቶ ጨረቃ ወጥቶበታል። መነካከሳችን፥ መኮራረፋችንና መገፋፋታችን በዝቷል። ይህ ደግሞ አምላካችንን ደስ አያሰኘውምና ኩርፊያችንንና ጥላችንን ወደ ኋላ ጥለን በይቅርታ መንፈስ እርስ በርሳችን ይቅር እንድንባባልና እንድንተቃቀፍ እግዚአብሔር አምላክ ይርዳን። አሜን!

# ወረቀት አፍ የለውም!

ሰባኪው «ኩርፊያ የሕይወት ነቀርሳ ነው። ኑሮን ያቃውሳል፥ ከጽድቅ ጎዳና ያወጣል፤ ውጤቱም ፍሬ የሌለው መንፈሳዊ ክስረትን የሚያስከትል፥ ቤተሰብን የሚበትንና ኪሳራም የሚያደርስ፤ ባጠቃላይ ነፍስን የሚያስጨንቅ ነው። ይህን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች አልፈቀደውም፤ ልንተባበረውም አልተፈቀደልንም።» ለሚለው ትምህርታቸው ይህን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«በአንድ መንደር ውስጥ በጣም የሚዋደዱ ባልና ሚስት ነበሩ አንዳቸውም የአንዳቸውን ሸክም እየተሸከሙ ትዳራቸውን በመተባበር ይመሩ ነበር። በተለይ ባልየው በጠዋት መንቃት አይችልም፤ ባለቤቱ ግን በጠዋት ተነሥታ ቁርስ ሠርታ በሰዓቱ ትቀሰቅሰውና ቁርሱን አብልታ ትሸኘው ነበር። እንዲህ እያሉ ሲኖሩ አንድ ጊዜ ግን ሰይጣን በመካከላቸው ገባና በትንሽ ነገር ተጣልተው ተኳረፉ። ባልየው ተጨነቀ። ጠዋት ማን ይቀሰቅሰኛል ብሎ አሰበና አንድ ትንሽ ወረቀት ወሰደና «እንደተለመደው በጠዋት ቀስቅሽኝ» ብሎ ጽፎበት ጠረጴዛ ላይ አስቀምጦት ተኛ። እርሷም በጠዋት ተነሥታ በዚያው ወረቀት ላይ «እንደተለመደው የሥራ ሰዓትህ ደርሷልና ተነሣ» ብላ ጽፋ ጠረጴዛ ላይ ቁጭ አደረገችለት። ነገር ግን ወረቀት አፍ የለውምና ሰውየው አራት ሰዓት ከሞላ በኋላ ተነሣ። ይህ ነገር ብዙ ጊዜ ስለተደጋገመ ልባቸው እልከኛ ሆነ፥ ሰውየውም ከሥራው ተባረረ።»

«ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ።» (ዕብ. 10፡24)

አዎ፥ የቤት ኩርፊያ አደባባይ ወጥቶ በኑሮአችንም ላይ ችግር ያመጣልና፥ በጓዳችን (በድንኳናችን) ውስጥ ይቅር ለእግዚአብሔር እንድንባባል እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን!

# አህያውን ይዛችሁ እዚህ ቆዩ!

ሰባኪው «የጌታ ባሪያዎች በንጹህ ልብና በቅንነት ባለችን ዕድሜ ጌታችንን ማገልገል አለብን እንጂ በሚጠፉ ጊዜያዊ ጥቅም ተታልለን መነካከስና መበላላት ፈጽሞ የለብንም።» በማለት የሚከተለውን ምሳሌ አጠንክረው ተናገሩ።

«ሁለት የማይስማሙ ወንጌላውያን ነበሩ። እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ የሚጠፉ ሰዎችን ወደ ጌታ መመለስ ሲገባቸው፥ ጊዜያቸውን ግን እርስ በርስ በመገፋፋትና በመነካከስ ያሳልፉ ነበር። ይህ ጉዳይ ያሳሰባቸው የቤተ ክርስቲያናቸው ሽማግሌዎች ብዙ ጊዜ መከሩአቸው፥ አስታረቁአቸውም። ነገር ግን እንደገና መልሰው መላልሰው መጣላት ቀጠሉ። በመጨረሻም ሽማግሌዎች ጥሩ መፍትሔ ይሆናል ያሉት ሁለቱን መለያየት ነውና አንዱን ክፍለ አገር አንዱን አዲስ አበባ እንዲሆኑ አደረጉ። ከመለያየታቸው በፊት ፍጹም ይቅርታ ተደራርገው መሄድ አለባቸው ብለው የሽኝት ፕሮግራም አደረጉላቸው። እነርሱም ፈጽመው ይቅር እንደ ተባባሉ ንግግር አደረጉ። ነገር ግን ወደ ክፍለ አገር የሚሄደው አሁንም በልቡ ቂም አለውና እንዲህ አለ፥ «ወደ ክፍለ አገር ከመሄዴ በፊት አንድ ቃል ልሰጣችሁ እፈልጋለሁ» በማለት ይህን ቃል ተናገረ፥ «እኔና ቤተሰቤ ወደዚያ ሄደን እናገለግላለን፥ እናንተ ግን አህያውን ይዛችሁ ከዚህ ቆዩ!» (ዘፍ. 22፡5)።

ወገኖቼ፥ አህያ ማን ነው? ይህስ ቃል ለዚህ ይሆናል ወይ? እግዚአብሔርን እናገለግላለን፥ ፈሪሀ እግዚአብሔር አለን ለምንለው፥ ለእኛ ለአገልጋዮች መጨረሻችን ይህ ነው ወይ? ስንነካከስና ስንበላላ እንዳንጠፋ ሁላችንንም እግዚአብሔር በምሕረቱ ይመልከተን። አሜን!

## የኢሠፓ አባል ነዎት?

ሰባኪው «እኛ ክርስቲያኖች ማንኛውንም ሰው ማክበር ያለብን በምንነቱ ሳይሆን በማንነቱ መሆን አለበት፤ ሀብታም ስለሆነ ወይም ባለሥልጣን ስለሆነ ወይም የተማረ ስለሆነ ወይም ትልቅ ስለሆነ አይደለም የምናከብረው። ድሀ፥ ወይም መሐይም፥ ያልተማረ ወይም ሥልጣን የሌለው ስለሆነ አይደለም የምንንቀው። ነገር ግን በሁሉም የሰው ልጆች ላይ የታላቁ እግዚአብሔር እስትንፋስ ስላለና ሰው ክቡር የእግዚአብሔር አምሳል ስለሆነ ሰው በመሆኑ ብቻ እርስ በርሱ ሊከባበር ይገባዋል።» የሚለውን ትምህርታቸው ለማስጨበጥና ለማስገንዘብ የሚከተለውን ምሳሌ ተጠቀሙ።

«በደርግ ዘመን አንድ አጭርና ቀጠን ያለ ሰው አውቶቡስ ፌርማታ ላይ ቆሞ አውቶቡስ እየጠበቀ ሳለ አንድ ወፍራምና ረጅም፥ ከሆዱ ገፋ ያለ ቦርጭ ያለው ሰው ጠጋ ብሎ በእግሩ ላይ ይቆምበታል። በዚህ ጊዜ የተረገጠው ሰው ይህ ሰውዬ የደርግ ባለሥልጣን ቢሆን ነው እንጂ እንዴት ደፍሮ ረግጦኝ ይቆማል ብሎ በማሰብ ቀና ብሎ መጠየቅ ጀመረ። «ጌታዬ፥ የቀበሌ ሊቀመንበር ነዎት? አይደለሁም። የአብዮት ጥበቃ ጓድ ነዎት? አይደለሁም። የኢሠፓ አባል ነዎት? አይደለሁም። ምንም ሥልጣን የለዎትም? «አዎን፥ የለኝም።» በዚህ ጊዜ ምንም ሥልጣን እንደሌለው ካረጋገጠ በኋላ የተረገጠው ሰው በቁጣና በጩኸት ቃል «ታዲያ ምን አባህ ቆርጦህ ነው እግሬ ላይ የቆምከብኝ!» ብሎ ገሠጸው።

«. . . በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ. . . ተከባበሩ!» (ሮሜ 12፡9)

አዎ፥ እርስ በርስ ለመከባበራችን ምክንያቱ የእግዚአብሔር አምሳል ሆነን በመፈጠር ከላይ ያገኘነው ባሕሪያችን ይሁን እንጂ ዛሬ ታይቶ ነገ የሚጠፋው ከታች ከምድር ያገኘነው (የሆነው) ማንነታችን አይሁን። ለዚህም ጌታ ይርዳን። አሜን!

# ምሥጋና

ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ራዕዩን በልቤ ጠንስሶ ወደ ፍጻሜ እንዲመጣ ጥበቡን፥ ኃይሉን፥ ክህሎቱንና ጸጋውን በነገር ሁሉ በመስጠት የረዳኝን ልዑል እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

በመቀጠልም በጸሎት፥ በምክር እና በገንዘብ የደገፉኝን በጌታ ወንድሞቼና እኅቶቼ የሆኑትን እንደሚከተለው አመሰግናለሁ።

የአቃቂ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች፥ ወንጌላውያን፥ የጸሎት አገልጋዮችንና ሠራተኞችን፤ የቤከርስን ቤተሰብ /Jeff & Jolene Baker/ እና የሉከንስን ቤተሰብ /Paul & Carol Lukins/፥ አቶ ገላሁን ኢዶን አመሰግናለሁ። እንዲሁም ከውድ ጊዜአቸው ላይ በመሸረፍ ያማከሩኝን እና በእርማት የረዱኝን አቶ ዘነበ ገ/ሐናንና አጋሮቻቸውን፥ የሚክጊንሊን ቤተሰብ /Fred & Dorothy McGinley/ ከልብ አመሰግናለሁ። በተጨማሪም በኮምፒውተር ጽሑፍ የተባበሩኝን እኅት ሕይወት ገብሬን፥ ጥሩወርቅ በቀለንና ዓለምፀሐይ እውነቱን አመሰግናለሁ።

በመጨረሻም ከጎኔ ሆና የጸለየችልኝን፥ በምክሯም የምትደግፈኝን፥ ለአገልግሎቴም ሁሉ መሣካት ምክንያት የሆነችውን ብልኋንና ጥበበኛዋን ባለቤቴን ወ/ሮ የሺወርቅ ሽመልስን አመሰግናለሁ።

# ሥጦታ

አባቴ ከሰው ሁሉ ጋር ተግባቢ፥ ተጫዋች እና ነገሮችን ሁሉ በምሳሌ የሚያስረዳ አንደበተ ርቱዕ፥ በመንደራችን ሰዎች ሁሉ ዘንድ ተወዳጅ ሰው ነበር። እኔም አብዛኛውን ባሕሪዬን የወሰድኩት ከአባቴ ነው። አሁን አባቴ የዚህ ዓለም ሩጫውን ጨርሶ በዘላለም ቤቱ በመንግሥተ ሰማይ ይገኛል። እኔም አንድ ቀን እግዚአብሔር በፈቀደውና በወሰነው ጊዜ ወደ እርሱ ሄጄ እስከምንገናኝ ድረስ የዚህን መጽሐፍ መታሰቢያነት ለአባቴ ለአቶ አበበ አግደው እንዲሆን አበረክታለሁ።

# የምድር ጨው

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት

«እናንተ የምድር ጨው ናችሁ። . . . » ማቴ. 5፡13

ይህ የምክር አገልግሎት የሚሰጠው በደብዳቤ በመጻጻፍ ሲሆን በሚከተሉት ዐበይት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ይሰጣል።

1. በክርስቲያናዊ ጋብቻ (ላላገቡና ላገቡ)
2. መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ለሚነሡ ጥያቄዎች
3. ወንጌልን በደብዳቤ ለሰዎች በማስተማር ዙሪያ
4. ኤች አይ ቪ ኤድስን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክርን ከጤና ባለሙያዎች ጋር በመካከር መስጠት
5. መጽሐፍ ቅዱስን በማስተማር በመስበክ የሚያገለግሉትን አገልጋዮች ማገልገል
   - 5.1 በጥያቄዎቻቸው መሠረት ለሚያስተምሩት ትምህርት የሚጠቅሟቸውን ምሳሌዎች በመላክ
   - 5.2 በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ መጽሐፍ ቅዱስን በመላላክ መማር ለሚፈልጉ ሁሉ ጤናማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ከሚሰጡ ክፍሎች ጋር በአድራሻ ማገናኘት።

ከላይ ባሉት ርእሰ ጉዳዮች እና በሌሎችም ጭምር «እሾክን ሳያደማ እንደሚነቅል ባለመድኃኒት» ላገለግላችሁ፤ በምክሩ ግሩም የሆነው ጌታ ልጆቹን ለማቅናትና ለመፈወስ በሚችለው ቅዱስ ቃሉ እና ቅዱስ መንፈሱ የሚለኝን ሁሉ ላስተላልፍላችሁ ተዘጋጅቻለሁና፤ በሚከተለው አድራሻዬ ጻፉልኝ፤ ደውሉልኝ።

ወንጌላዊ ደመወዝ አበበ

የምድር ጨው
መጽሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር አገልግሎት
ፖ. ሳ. ቁ. 70983
ስልክ 49 23 57
ሞባይል (09) 23 45 16
E-mail: Sebcm2002@yahoo.com
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጡ እውነቶችን ሰዎች ሊረዱት በሚችሉበት መንገድ ለማቅረብ ምሳሌዎችን መጠቀም እጅግ ጠቃሚ ነው። የምንጠቀምባቸው ምሳሌዎች ግን ከመልእክታችን ጋር የሚሄዱና አሳባችንን ሊያብራሩ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል። ይህንን ከጌታችን ከኢየሱስ ትምህርቶች መገንዘብ እንችላለን። ምሳሌዎችን ከየት አገኛለሁ የሚለው ግን የብዙ ሰባኪዎች ጥያቄ ነው።

ወንጌላዊ ደመወዝ ይህንን ችግር በመጠኑም ቢሆን ለመፍታት ይህንን መጽሐፍ መጻፉ እጅግ የሚያስደስት ነው። በዚህ መጽሐፉ ላይ ያቀረባቸው ምሳሌዎች በርእሶች ተከፋፍለው በመቅረባቸው በምንፈልገው ርዕስ ለሰዎች ለማስጨበጥ የሚረዱ በመሆናቸው ትልቅ አስተዋጽዖ ይኖራቸዋል።

ስምዖን ሙላቱ

የኢቲሲ ፕሪንሲፓል

የአገራችን ሥነ ጽሑፍ ዕድገት ይበልጡን የተንተራሰው በሥነ-ቃል ሥነ ጹሑፍ ፈርጅ ሲሆን፥ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ እነኚህን በሕዝብ ዘንድ የተወደዱ ምሣሌያዊ አነጋገሮችን በጽሑፍ ማስፈሩ ባለውለታ ያሰኘዋል። በዚህም ብቻ አይደለም የወንጌል ሰባኪያን በስብከታቸው መሃል እንደ ጣፋጭ ስኳር ጣል የሚያደርጓቸውን መልእክታቸውን ለማጠናከር የሚደግፉቸውን ዕምቅ አሳቦችን አስፈልገው በአጭሩ ለመግለጽ የሚያስችሉ ምሣሌያዊ መግለጫዎችን ተችረዋል። ይህም ባለውለተኛነትን ያስመሰክራል። በአገራችን ክርስቲያን ሥነ ጽሑፍ የመጀመሪያ የሆነው ይህ ሥራ በወንጌል ሰባኪው ሥራ ውስጥ የጣፈጠና የተዋዛ መልእክትን ለማስተላለፍ በጎ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብዬ አምናለሁ።

ደረጀ አበበ

የጊኝ ቃለ ሕይወት መጽሔት ዋና አዘጋጅ